# ምዕራፍ 28

## 1921 ዓመተ ምሕረት

**በአስተማሪነት ሥራ ሳለሁ፣ የአማርኛ ሰዋስው ከሌሎች ጋር እንዳስተዋወቀኝ፣ ሌላ ሥራ ለመያዝ እንደፈተንሁ**

### በአስተማሪነት ሥራ ሳለሁ

በ1921 ዓ.ም. ዘመነ ማቴዎስ ማክሰኞ ባተ። እኔም በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት የአስተማሪነት ሥራዬን እንደቀጠልሁ ነኝ። መስከረም 27 ቀን እሑድ ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ ንጉሥ ተብለው ዘውድ ስለጫኑ የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎችና አስተማሪዎች የሰልፍ ተራ ተሰጥቷቸው ተሰልፈው ነበርና እኔም አብሬ ተሰልፌ ዋልሁ። በዚያውም ቀን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በግቢያቸው ለመኳንንትና ለካህናት ሙሉ ግብር ስላደረጉ እኔም ገብቼ ነበርና የግብሩን ሥነ ሥርዓት ተመለከትሁ። ንጉሥ ተፈሪ ልብሰ መንግሥት ለብሰው በዙፋን ላይ ተቀምጠዋል። ዘውዳቸው በዙፋኑ አጠገብ በጠረጴዛ ላይ ተቀምጧል። መኳንንቱም በዙፋኑ ቀኝና ግራ በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር። ከመኳንንቱም መካከል በዙፋኑ አጠገብ በወንበር የተቀመጡት ልዑል ራስ ካሣ ቅጹ በበርኖስ ዓይነት ሆኖ የተሰፋና በወርቅ ጥልፍ አምሮ የተጌጠ ካባ ለብሰው ነበርና ከሌሎች መኳንንት የተለየ የክብር ግርማ ይታይባቸው ነበር።

የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ጥቅምት 12 ቀን ተከፍቶ ሥራ ጀመርን። ባለፉት ዘመኖች የመክፈቻው በዓል ልዑል አልጋ ወራሽ ባሉበት ሲከበር ቈይቶ ነበር። በዚህ ዓመት ግን ግርማዊ ንጉሥ ስላልተገኙ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉትና የከፈቱት ቴዎድሮስ ወርቅነህና ዲሬክተሩ ሙሴ ቶማሲኒ ናቸው። ዋናው ሹም አዛዥ ወርቅነህ ወደ ዓለም ማኅበር ጉባኤ ተልከው ነሐሴ 9 ቀን 1920 ዓ.ም. ከቢትወደድ ጌታቸው ጋራ ስለሄዱ ቴዎድሮስ ወርቅነህ የእሳቸው እንደራሴ ሆኖ እንደነበረ እዚህ ላይ መግለጽ የተገባ ነው። አዛዥ ወርቅነህ የተመለሱትም በዚህ ዓመት በኅዳር 5 ቀን ነው።

### የአማርኛ ሰዋስው ከሌሎች ጋር እንዳስተዋወቀኝ

ካለፈው ዓመት አንሥቶ የትምህርት ሥራ የተጀመረበት የአማርኛ ሰዋስው ወሬው በየስፍራው ስለተሰማ ከውጭ አገር ሰዎች ጋር ያስተዋውቀኝ ጀመር። ለምሳሌ በፓሪስ ያለው የምሥራቃውያን ቋንቋ ሊቅ ሙሴ ግሬቦና በአዲስ አበባው የፈረንሳይ ሌጋሲዮን ጸሐፊ በኩል በደብዳቤ ተዋወቀኝ። እርሱ ራሱ በአማርኛና በፈረንሳዊኛ የጻፋቸውን ሁለት መጻሕፍት ልኮ አበረከተልኝና እኔም አንድ የሰዋስው ቅጂ እንድልክለት ጠየቀኝ። እኔ ግን ሰዋስዉ ገና



ወደፊት የሚታተም መሆኑንና በታተመ ጊዜ እንደምልክለት በመግለጥ መልስ ከሰጠሁ በኋላ ትምህርተ ሕፃናት የተባለች ትንሽ መጽሐፌን በበኩሌ ስጦታ አድርጌ በቆንስሉ በኩል ላክሁለት።



34 ሞንሲኞር ኒቆላዎስ ከንግሥት ዘውዲቱና ከንጉሥ ተፈሪ ጋር። ከግራ ወደ ቀኝ ልጅ ተምትሜ ወልዴ፣ ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ፣ ልጅ ከበደ ተሰማ፣ ሊቀ መኳስ መንገሻ ውቤ፣ አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ፣ ራስ ካሣ፣ ግሪካዊ ጳጳስ ወይም ቄስ

እንዲሁ ደግሞ ሞንሲኞር ኒቆላዎስ የተባሉ የግሪክ ማኅበር ጳጳስ በዚሁ ዓመት ተዋወቁኝና አማርኛ እንዳስጠናቸው ጠየቁኝ። እኒህ ሰው በኢትዮጵያ ላለው የግሪክ ሕዝብ ሜትሮፖሊታን[185] ሆነው ከሞንሲኞር ሚሊቲዮስ፣ በእስክንድርያ ላይ ተሾመው በዚህ ዓመት በመስከረም 4 ቀን አዲስ አበባ የገቡ ናቸው። ሰውየው ከቋንቋቸው ሌላ ፈረንሳዊኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ላቲን፣ ዐረቢኛና ቱርክኛ ይናገራሉ። አሁንም አማርኛ ለመማርና ለማወቅ ፈልገው ኖሮ በኅዳር ወር የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤትን በጐበኙ ጊዜ አማርኛ ለመማር ያላቸውን ምኞት ለአዛዥ ወርቅነህ ነገሯቸው። እሳቸውም ከእኔ ጋር አገጣጠሟቸውና በትርፍ ሰዓት ወደ ቤታቸው እየሄድሁ እንዳስተምራቸው ተነጋግረን ተስማማን። ሰውየው የቋንቋ ስጦታ ስላላቸው በዕድሜም የ38 ዓመት ሰው ስለሆኑ የአማርኛን ፊደል ለማወቅና ንባቡን ለመከተል ምንም ጊዜ አልወሰደባቸውም፤ በቶሎ ዐወቁትና የሰዋስው ክፍሎችን በማጥናት

---

[185] በኢትዮጵያ ሀገረ ስብከት ለግሪክ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ጳጳስ።

ይለማመዱ ጀመር፡፡ ሁለት ወር ያህል ካስተማርኋቸው በኋላ በእንግሊዝኛ በደብልጥ ሊያስረዳቸው የሚችል ገብረ መድኅን ኃይለ ማርያምን ተክቼላቸው ያስተምራቸው ጀመር፡፡

ሞንሲኞር ኒቆላዎስ በዚያ በጥቂቱ ጊዜያት ተለማምደን ወዳጅ ስላደረጉኝ በግሪክ አገር በመንፈሳዊ ትምህርት እስኮላርሺፕ ፈልገው እንደሚልኩኝ ተስፋ ሰጡኝ፡፡ ከአንድ ዓመት በኋላም እስኮላርሺፕ ያገኙልኝ መሆናቸውን ነገሩኝ፡፡ ነገር ግን እኔ በዚያን ጊዜ ለሥራ ወደ ጅጅጋ ታዝዤ ነበርና አሳቤን የለውጥሁ መሆኔን ገልጬ ምስጋና አቀረብሁላቸው፡፡ ለእኔ በጠየቁትም ስፍራ አንድ ሐማሴናዊ ወጣት የላኩ መሆናቸውን በሌላ ጊዜ ነግረውኛል፡፡

## ስለ ልዩ ልዩ ነገር

የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር ዓመታዊ በዓሉን ታኅሣሥ 16 ቀን 1921 ዓ.ም. ማክሰኞ በፕሬዜዳንቱ በአዛዥ ወርቅነህ ቤት ታላቅ ግብዣ አድርጎ ሲያከብር እኔም በአባልነቱ የበዓሉ ተካፋይ ሆኜ አከበርሁ፡፡ ባለፈው ዘመን በደንበኛ ሥራዬ ላይ ደርቤ ያለ ደሞዝ ይዤው የነበረውን የማኅበሩ ዋና ጸሐፊነትና የተማሪ ቤቱ የሥራ ኃላፊነት ቀርቶልኝ ለአቶ ያሬድ ተሰጥቶ ነበር፡፡ አቶ ያሬድ የማኅበሩ ዋና ጸሐፊና የተማሪ ቤቱ ዲሬክተር ሆኖ በደሞዝ እንዲሠራ በሰኔ 4 ቀን 1920 ዓ.ም. በእኔ ቦታ የተተካው ነው፡፡ ሰውየው በትምህርትም በጠባይም ምስጉንና ትጉህ ሠራተኛ ስለሆነ የተማሪ ቤቱን ሥራ አስፋፍቶት ነበር፡፡

በግብዣው መጨረሻ በሻምፓኝ ጊዜ ፕሬዜዳንቱ አዛዥ ወርቅነህ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ፡፡

> *የተወደዳችሁ ወንድሞቼና ልጆቼ*
>
> *እነዚህን ሦስቱን ዓመቶች በደኅና ስላሳለፍናቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን፡፡ ወደፊትም ለመንግሥታችንና ለወገኖቻችን በፍጹም ልብ አገልጋዮች ለመሆን እግዚአብሔር እንዲባርከን እንጸልያለን፡፡*
>
> *በዚህ ባለፈው ዓመት ውስጥ የተማሪ ቤታችን ሥራ በመልካም ተካሂዶልናል፡፡ ይልቁንም ተማሪዎቹን የሚጠብቅና ለተማሪ ቤታችንም ጥቅም ያለውን ሥራ የሚሠራ ወንድማችንን አቶ ያሬድን ስለማግኘቴ እድለኛ በመሆኔ ደስ ብሎኛልና ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርብለታለሁ፡፡ ደግሞ ሴቶቹንና ልጃገረዶቹን የሚጠብቁትን የልጆቹንም ምግብ እንደሚገባ ዘወትር የሚያሰናዱትን እሜት ደሜን አመሰግናቸዋለሁ፡፡ በዚህም ላይ ደግሞ ለዛሬው በዓላችን ይህን መልካም ምግብ ላዘጋጁልን ወይዛዝር ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንግዲህ ዲሬክተሩ አቶ ያሬድ የተማሪ ቤቱን ወጪና ገቢ የልጆቹንም ሥራ ዝርዝር እንዲነግረን እለምነዋለሁ፡፡ ነገር ግን ከዚህ አስቀድሞ ስለግርማዊት ንግሥታችንና ስለ ግርማዊ ንጉሣችን ጤና ጽዋችንን አንሥተን እንጠጣለን፡፡*

ብለው ተናግረው ሲጨርሱ ተጨበጨበ፡፡



ከዚህ በኋላ አቶ ያሬድ ባደረገው ንግግር ተማሪዎቹ ወንዶችና ሴቶች መሆናቸውንና ቍጥራቸው እስከ ሃምሳ መድረሱን የትምህርቱ ዓይነት በእጅ ሥራ በኩል ሽማኔነትና መኪና ስፌት፣ እናጢነት፣ የጠፍር ስፌነት፣ ብር አፍሳሽነት ሲሆን በቀለም ትምህርት በኩልም የአማርኛ ንባብና ጽሕፈት ሒሳብ መምህር መሆኑን ከገለጸ በኋላ፣ የገንዘብ ገቢና ወጪ ሒሳቡንም በድምር አቅርቦ አመለከተ፡፡ የእርሱ ንግግር ካበቃ በኋላም ማኅበርተኞቹ ሁሉ የመታሰቢያ ፎቶግራፍ በአንድነት ተነሥተን የበዓሉ ፍጻሜ ሆነ፡፡



35 የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር አባላት (መሃል የተቀመጡት ሐኪም ወርቅነህ ሲሆኑ ቀስቱ መርስዔ ኅዘንን ያመለክታል)

መጋቢት 17 ቀን 1921 ዓ.ም. ማክሰኞ የልደቴ ቀን ነበር፡፡ በዚህ ዕለት ሠላሳ ዓመት ስለሞላኝ ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ ዕለቱን በተለይ አከበርሁት፡፡ ምክንያቱም ከጎልማሳነት ወደ ሙሉ ሰውነት የሚያስተላልፈው ዕድሜ ሠላሳ ዓመት ነው እያሉ ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን ይናገሩ ነበርና ንግግራቸውን በማስታወስ ነው፡፡ በእውነትም ከዚህ ዕድሜ በኋላ በገዛ ራስ የመተማመንና የማስተዋል ለውጥ ያለ ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌም ያህል በዚያው ወራት ያጋጠመኝን እጠቅሳለሁ፡፡ በፋሲካ ሰሞን አንድ ቀን በአራዳ ጊዮርጊስ አጠገብ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይን በሩቅ አየሁና ወደ እርሳቸው ቀርቤ እጅ ነሣሁ፡፡ እርሳቸውም የሰላምታ መልስ ሰጡኝና ስለ ተማሪ ቤት ሥራዬ እየጠየቁ ጥቂት አነጋገሩኝ፡፡ ቀጥሎም "ስለ ይኩኖ አምላክ የምታውቀው ታሪክ አለ ወይ?" ስላሉኝ በእሳቸው አንደበት በመጠየቄ ደስ አለኝና በተክለ ሃይማኖት ገድል ያነበብሁትን የአውራ ዶሮ ታሪክ ለመናገር ገና ስጀምር "የዶሮውንስ ታሪክ ተወው ሌላ ታውቃለህ ወይ ማለቴ ነበር" ብለው

አቋረጡኝ። ከዚያም በኋላ "ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ እሑድ ከቤቴ መጥተህ ምሳ እንድትበላ" ብለህ ንገርልኝ አሉኝና "እሺ ጌታዬ" ብዬ እጅ ነሣሁ። ደግሞም ጥቂት ሲያመነቱ ቆዩና "አንተም መጥተህ ምሳ እንድትበላ" ስላሉኝ አሁንም "እሺ ጌታዬ" ብዬ እጅ ነሥቼ ተሰናበትሁ። ከዚህ በኋላ መልእክቱን ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ አደረስሁ። እኔ ግን <u>አንተም</u> የሚለው ዋዌው[186] ስሜቴን ቀሰቀሰብኝና ከግብዣው በመቅረት ስሜቴን ደስ አሰኘሁት። ይህም የዕድሜ ሙሉነት ያስከተለው በገዛ ራስ የመተማመን ነገር ይመስለኛል። እንደ ቀድሞው ጊዜዬ ቢሆን ኖሮ ጥሪያቸውን እንጂ ዋዌውን ባልተመለከትሁም ነበር።

## ሌላ ሥራ ለመያዝ እንደፈተንሁ

በአስተማሪነት ሥራ ከአራት ዓመት በላይ ስለቈየሁና ስለሰለቸኝ በዚህ ዓመት ወደ ሌላ ሥራ ለመዛወር በብዙ መንገድ እፈትን ጀመር። ነገር ግን የተመኘሁትን ለማግኘት ስላልቻልሁ ሐሳቤን ወደ ንግድ ኑሮ አዛወርሁና የሚያዋጣኝን መንገድ አጠና ጀመር።

በሰኔ ወር ትምህርት ቤት ከተዘጋ በኋላ ይህን ሐሳቤን ለወዳጄ ለነጋድራስ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ነገርኋቸውና በጉዳዩ ከተመካከርን በኋላ በእሳቸውና በወንድማቸው በአቶ ፋሲካ ካፒታል ገንዘብ ጅማ ውስጥ አጋሮ ላይ የቡና ንግድ እንዲቆምና እኔ ሥራውን እያስኬድሁ ከእነርሱ ጋር የትርፍ ተካፋይ እንድሆን በበኩላቸው ሐሳብ አቀረቡልኝ። እኔም በነገሩ ስለተስማማሁ የስምምነቱን ረቂቅ በአንድነት ሆነን አዘጋጀን።

ዳሩ ግን ስምምነቱን ከመፈረም በፊት አንድ የሚፈጸም ነገር ነበረ። ይኸውም ከመንግሥት ሥራ ለመውጣት የመቻልና የአለመቻል ነገር ነው። በዚያ ዘመን የመንግሥት ሠራተኛ በፈቃዱ ሥራ ለመተው አይችልም ነበርና እንዴት እንደምተው ምክንያት መፍጠር አስፈላጊ ሆነብኝ። ስለዚህም "በጤና ምክንያት በቈላ አገር ለመኖር ስለፈለግሁ ያሰናብቱኝ" ስል ለአለቃዬ ለአዛዥ ወርቅነህ ማመልከቻ አቀረብሁላቸው። እሳቸውም "አንተን የላኩልኝ ግርማዊ ንጉሥ ስለሆኑ ላሰናብትህ አልችልም" ካሉኝ በኋላ፤ "ሆኖም ማመልከቻህን ለግርማዊ ንጉሥ አቀርብልሃለሁ" ስላሉኝ ማመልከቻዬን ሰጥኋቸውና በሥራዬ ላይ ሆኜ እጠባበቅ ጀመር።

[186] ስምና አንቀጽ መጨረሻ እየተጨመረ የሚነገር ፊደል፤ ይኸውም ም ነው።

# ምዕራፍ 29

## 1922 ዓመተ ምሕረት

**ወደ ሌላ ሥራ ስለመዛወሬ፣ ወደ ጅጅጋ ስለመሄዴ፣ የጅጅጋ ትምህርት ቤት እንደ ተከፈተ፣ የጅጅጋ ኑሮዬ ስለ መጀመሩ፣ ቤተሰቤን ወደ ጅጅጋ ስለማስመጣቴ፣ ስለ አገሩ ሁናቴ፣ በጅጅጋ የማሠልጠኛ ተማሪ ቤት ስለ መቋሙ፣ ስለ ወሰን ጠባቂዎች፣ በወሰን ላይ ስለ ደረሰ ግጭት፣ ስለ ልዩ ልዩ ነገር**

## ወደ ሌላ ሥራ ስለመዛወሬ

1922 ዓ.ም. ዘመነ ማርቆስ ረቡዕ ባተ። ከዚህ በፊት እንደጻፍሁት (ገጽ 194) የአስተማሪነት ሥራ ስለሰለቸኝ ስንብቻ የጠየቅሁበትን ምክንያት በመግለጽ ማመልከቻ ጽፌ ነበር። እርሱንም አለቃዬ አዛዥ ወርቅነህ በዚህ ዓመት በጥቅምት ወር ለግርማዊ ንጉሥ አቅርበውት ኖሮ "ሥራውን የሚተወው ስለጤናው በሙቀት አገር ለመኖር በማሰብ ከሆነ እኛም እንረዳዋለን። ለዚሁም ተስማሚ የሆነ ሥራ እናገኝለታለንና ጥቅምት 27 ቀን ያቅርቡት" የሚል መልስ ስለተሰጣቸው ልጅ በልሁ ደገፉ እንዲያቀርበኝ አሳዝዘው መጥተው ነገሩኝ፤ ስለዚህም በጥቅምት 27 ረቡዕ ወደ ግቢ ሄጄ እጠባበቅ ጀመር። ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በዱክ ቤት ሆነው ባለ ጉዳዮች መኳንንትን ያነጋግሩ ነበር። አምስት ሰዓት ሲሆን ልጅ በልሁ አስጠርቶኝ ገባሁና መሬት ስሜ ከፊታቸው ቆምሁ። በዚህ ጊዜ ነጋድራስ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል እዚያው ስፍራ ስልክ እየደወሉ በራስ ናደው ሕመም ምክንያት ከኢሉባቦር ስልከኞች ጋር እየተነጋገሩ ቃሉን ለግርማዊ ንጉሥ ያመላልሱ ነበርና የተጀመረው ነገር እስኪፈጸም ድረስ ከሐያ ደቂቃ ያላነሰ ወደ ጎን ገለል ብዬ ቆሜ ስጠብቅ ቈየሁ። በየመካከሉም አቶ ታደሰ መሸሻና ብላቴን ጌታ ወልደ ማርያም እየለ ጣልቃ እየገቡ ጉዳይ ያቀርቡላቸው ነበር።

የስልኩ ነገር ካበቃ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ወደ እኔ እያዩ "በሙቀት ስፍራ ለመኖር መፈለግህን አዛዥ ወርቅነህ ነግረውናል፤ ሐሳብህ ይኸው ከሆነ ጅጅጋ የሚስማማህ ነውና እዚያ በአባቴ በልዑል ራስ መኰንን ስም እንዲከፈት ያሰብነውን ተማሪ ቤት አቋቁመህ እንድትሠራ ልንነግርህ ነው የጠራንህ" አሉኝ። እኔም በርኅራኄና በበጎ አሳቢነት የተሞላ ንግግራቸውን ስሰማ ከልብ ደስ አለኝና "ግርማዊ ሆይ ለጤናዬና ለኑሮዬ ግርማዊነትዎ ያሰቡልኝን ተቀብዬ በተቻለኝ ሁሉ አገለግላለሁ" ብዬ መሬት ስሜ ተሰናብቼ ወጣሁ። በሩን ወጥቼ ጥቂት እንደተራመድሁ ባላምባራስ ተክለ ማርቆስ ከተል ብሎ ጠርቶ አቆመኝና "አስፈላጊውን ማዘዣ እንድሰጥህ ነገ ወደ ቢሮዬ እንድትመጣ" ብሎኝ ተመለሰ።

ከዚህ በኋላ ወደ ባላምባራስ ተክለ ማርቆስ ቢሮ መመላለስ ሆነ። ይህ ሰው በግርማዊ ንጉሥ ግቢ ከዋናው የጽሕፈት ሹም ከፊታውራሪ ኃይሉ ወልደ ሩፌ ቀጥሎ የሚገኝ የጽሕፈት ቤቱ ባለሥልጣን ነው። ከእኔም ጋር በሥራ ላይ ባለሁበት ዘመን ሁሉ በቂ ዕውቂያ ነበረን። ነገር ግን በሥራ ብዛት ወይም እኔን ቸል ለማለት በማሰብ እንደሆነ አልገባኝም ሦስት ሳምንት ያህል ስመላለስ እያየኝ ዝም ይለኝ ጀመር።

እኔ ግን ወደ ታዘዝሁበት ስፍራ ለመሄድ ወይም ቁርጡን ዐውቄ የስንብቻ ፈቃድ ለማግኘትና ያቀድሁትን የንግድ ሥራ ለመጨበጥ ቸኩዬ ነበርና በደጅ ጥናት መመላለስ ክፉኛ ሰለቸኝ። ወደ አዛዥ ወርቅነህም ሄጄ ሁናቴዬን ነገርኋቸውና የስንብቻውን ፈቃድ ብቻ እንዲያስጡኝ ለመንኋቸው። አዛዥ ወርቅነህ ቅንነትና ርኅራኄ ከአምላክ የተፈጥሮ ስጦታ የሆነላቸው ደግ ሰው ስለሆኑ የሰውን መጉላላት የማይወዱ ናቸው። የእኔንም ጉዳይ እንደገና ለግርማዊ ንጉሥ አቀረቡት። ባላምባራስ ተክለ ማርቆስ ተጠርቶ ቢጠየቅ "የአውራጃው ዲሬክተር ግራዝማች መስፍን ቀለመ ወርቅ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ስለሚመጣ እንዳገጣጥመው አስቤ ነው" የሚል ምክንያት ስለሰጠ ነገሩ እዚህ ላይ ቆሞ ዐረፈ። አዛዥ ወርቅነህም "እንግዲህ እነርሱ ሲፈልጉህ ይጥሩህ እስከዚያም ድረስ በቀድሞ ሥራህ ላይ ነህ" ስላሉኝ የሥራ መደቤን እንደያዝሁ እጠባበቅ ጀመር። አቅጄው የነበረውንም የንግድ ሥራ በኅዳር 30 ቀን ሠረዝሁት።

## ወደ ጅጅጋ ስለመሄዴ

በታኅሣሥ 8 ቀን ማክሰኞ ነጋድራስ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ፊታውራሪ ተብለው የጅጅጋ አውራጃን ተሾሙ። ዲሬክተሩ ግራዝማች መስፍንም በዚሁ ጊዜ ከጅጅጋ መጥቶ አዲስ አበባ ነበረ። ከዚህ በኋላ የሹመቴ ስያሜ የጅጅጋ ትምህርት ቤት ሹም ተብሎ ማዘዣ ተጻፈና ከአውራጃው ገዥ ጋር ተገጣጠምሁ። የመጓጓዣም ገንዘብ ታዝዞልኝ ለጕዞ እሰናዳ ጀመር። የትምህርት ቤቱን ማኅተም ቋሚ ጸሐፊው አቶ ተክለ ጊዮርጊስ ናቄ ንድፉን አሳምሮ ሠርቶ አቅርቦ ተፈቀደና ተሠራ። በማኅተሙ ውስጥ የተጻፈው ጥቅስ «ጻድቅስ ከመ በቀልት ይፈሪ»[187] የሚል ሆኖ በመካከሉ የዝግባ ዛፍ ተሥሎበታል በዙሪያውም «የልዑል ራስ መኰንን ትምህርት ቤት ጅጅጋ» የሚል ቃል ተጽፎበታል።

እስከ ጥር መጨረሻ የትምህርት ቤት ዕቃዎችን ሳዘጋጅ ቈየሁና በየካቲት 1 ቀን በባቡር ተሣፍሬ ወደ ሐረር ተጓዝሁ። በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት

[187] ጻድቅስ እንደ ዝግባ ያፈራል።



አራት ዓመት ከዓሥር ወር ያሳለፍሁትን ዓረፍተ ዘመን[188] ተራምጄ እንግዲህ ወደ ሌላው መተላለፌ ነው።



36 ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል በ1923 ዓ.ም.

የአውራጃው ገዥ ፊታውራሪ ታፈሰም ከቤተሰቦቻቸው ጋር በዚያው ቀን በባቡር ተሣፍረው ነበርና ድሬዳዋ ስንደርስ እኔ በእግር መንገድ በሐረር ላይ አልፌ በሦስተኛው ቀን ጅጅጋ ገባሁ። እርሳቸው ግን ወደ ጅቡቲ ወረዱና ከዚያ በመርከብ ወደ በርበራ አልፈው ከበርበራም በአውቶሞቢል ሆነው በስምንተኛው ቀን ጅጅጋ ሲደርሱ እኔ ቀድሜ ተቀበልኋቸው።

## የጅጅጋ ትምህርት ቤት እንደተከፈተ

ከዚህ በኋላ ትምህርት ቤቱን ለማቋቋም ያለ ዕረፍት እሠራ ጀመር። የአውራጃው ገዥ ፊታውራሪ ታፈሰ ትጉህ ስለሆኑ በብዙ ወገን ረዱኝ።

[188] የዘመን አንጓ፣ ምዕራፍ።

ጓደኞቼ ልጅ ተስፋ ያየህ ይራድና አቶ መዓዛ ወልደ ሕይወት የሐሳብ ረዳቶቼ ነበሩ።

ትምህርት ቤቱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በነበረ በአንድ ሰፊ ግቢ ውስጥ እንዲቆም ስለተፈቀደ የትምህርት ክፍሎችን ማዘጋጀት ጀመርን። ሥራውም ከ15 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስለተዘጋጀ ተማሪዎችን መቀበል ጀመርን። የመክፈቻውም ሥነ በዓል በመጋቢት 13 ቀን 1922 ዓ.ም. እንዲሆን ስለተወሰነ፣ በዚሁ ቀን በ10 ሰዓት አገረ ገዥው ፊታውራሪ ታፈሰና የአገሩ ታላላቅ ሰዎች ተሰበሰቡ። የሰዎቹም ስም ቀጥሎ ያለው ነው። ካፕቴን ሎንግ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንስል፣ ልጅ ተስፋ ያየህ ይራድ የጅጅጋ ጉምሩክ ሹም፤ አቶ መዓዛ ወልደ ሕይወት የጅጅጋ ማዘጋጃ ቤት ሹም፣ አቶ ዘለሌ የአውራጃው ወምበር[189]፣ አቶ ብሩ ሀብተ ዮሐንስ የአውራጃው ጽሕፈት ቤት ሹም፣ አለቃ ገብረ ጊዮርጊስ የቤተ ክህነት ሹም፣ ግራዝማች ሮባና ቀኛዝማች ተስፋዬ ኃይሌ ናቸው።

ከዚህ በኋላ የአውራጃው ገዥና የተጠሩት እንግዶች በየክፍሉ እየገቡ ተማሪዎቹን ጐብኝተው ለእንግዳ መቀበያ ወደ ተዘጋጀው ስፍራ ገብተው ሲቀመጡ የአውራጃው ገዥ የበዓሉን መክፈቻ ረጅም ንግግር አደረጉ። ከዚያም ቀጥሎ እኔ ከዚህ በታች ያለውን ቃል ተናገርሁ።

*ክቡር ሆይ፣*

*ክቡራን ሆይ፣*

*አዲሱ ትምህርት ቤት በልዑል ራስ መኰንን ስም ተሰይሞ በሚመሠረትበት መታሰቢያው በማይረሳ በዛሬው ቀን ከመካከላችሁ ቆሜ ይህችን ቃል እናገር ዘንድ ክብር በማግኘቱ ለደስታዬ ወሰን የለውም።*

*ትምህርት በአእምሮ ጠባይዕ ውስጥ ተሠውሮ ያለው የዕውቀት ብርሃን የሚገለጽበት የአእምሮ መክፈቻ ስለሆነ፣ የሀገርን ጥቅም ለማስፋት የሕዝብን አንድነት ለማጽናት በመጀመሪያ የሚያስፈልገው ዋና መሣሪያ ትምህርት መሆኑ እያደር ተገልጿል።*

*ይህንንም ሁሉ መርምረው የተረዱት ብልሁ ጌታችን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ሕዝባቸውን በሥልጣኔ ለማደስ የሁልጊዜ አሳባቸው ስለሆነ፣ በዚህም ከተማ ይህን የሥልጣኔ ትምህርት ቤት በመልካሙ አባታቸው በልዑል ራስ መኰንን ስም ሰይመው አቆሙት። ለዚሁም ሥራ ግርማዊነታቸው በታማኝነት ስለላኩኝ ለደስታዬ ወሰን የለውም።*

*ክቡር ሆይ፣ ትምህርትን የሚፈልጉ 47 ሕፃናት ተሰብስበውልን ሥራውን ጀምረናል። አሁን በመጀመሪያው ጊዜ የተማሪዎቹ ቍጥር ይህን ያህል ከሆነ ወደ ፊት ሥራችን እየሰፋ እንዲሄድ የተረጋገጠ ተስፋ ለማኖር እንችላለን።*

[189] ዳኛ።



*እናንተም በዚህ የቆማችሁት የልዑል ራስ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ የሰጧችሁን ምክርና ምሳሌ እያሰባችሁ በትምህርታችሁ ትጉሆች በሥራችሁ ንቁዎች እንድትሆኑ እለምናችኋለሁ።*

*ክቡር ሆይ፣*

*ድካማችንን ወደ ፍሬ ለማድረስ የክቡርነትዎ ዕርዳታ ዋና ደጋፊዬ መሆኑን አተማመናለሁ። እግዚአብሔር ለዳጉ አሳቢያችን ለግርማዊ ንጉሥ ረጅም የጤና ዕድሜ ይስጥልን። ኢትዮጵያ በነፃነትዋ እንደ ተከበረች ትኑር።*

ይህ ንግግር እንዳበቃ የሻይ ግብዣ ሆነና ወዲያው ሻምፓኝ ተከፈተ። በሻምፓኝ ጊዜም አቶ ብሩ ሀብተ ዮሐንስና የእንግሊዝ መንግሥት ቆንስል ካፕቴን ሎንግ በየተራ እየተነሡ ደስ የሚያሰኝ ዲስኩር ተናግረው መረቁ። ከዚያም በኋላ ሥነ በዓሉ ተፈጽሞ በየቤታቸው ተመለሱ።

የተማሪዎች ቍጥር በመጀመሪያው ጊዜ 47 ሲሆን በዓመቱ መጨረሻ 143 ሆኗል። ከዚያ በኋላም ቍጥራቸው እየበዛና ሥራው እየተስፋፋ ሄዷል።

ለሥራው መስፋፋት በመልካም ፈቃድ ተባባሪ የሆኑትና እዚያ በቈየሁበት ዘመን አገልግሎት የሰጡትን የአስተማሪዎች ስም ከዚህ በታች እጽፋለሁ።

አቶ ናደው ደመራ፣ አቶ ሞሲሳ ራባ፣ አቶ ኃይለ መስቀል እንኳለ ጽዮን[190]፣ ሙሴ ሚናሒም እህሮኒ፣ አቶ ገብረ እግዚአብሔር ተድላ፣ አቶ አበበ ወልደ አብ፣ ደብተራ ወልደ ገብርኤል፣ አቶ መንገሻ ኃይሌ፣ አቶ ስለሺ ገብረ ማርያም ናቸው። ሠራተኞችም ጉዳ ሩንዳሳ፣ ታደሰ ወልደ ማርያም፣ ገብረየስ ተገኔ፤ ፋንታ አርዮ የተባሉ ናቸው። የእነዚህ አስተማሪዎችና ሠራተኞች እርዳታ ባይጨመር ኖሮ ሥራው ሊቃና ባልቻለም ነበር እላለሁ።

## የጅጅጋ ኑሮዬ ስለ መጀመሩ

ለትምህርት ሥራ ታዝዤ ወደ ጅጅጋ ስለመሄዴና ትምህርት ቤቱ ተከፍቶ ሥራ ስለ መጀመሩ በገጽ 195 ገልጫለሁ። እንግዲህ የምጽፈውም በጅጅጋ ላይ በነበርሁበት ጊዜና ከዚያም በኋላ በተከታታይ በተንዝሁበት የኑሮ ትዝታዬ ላይ ያጋጠመኝን የታሪክ ትዝታ ከብዙ በጥቂቱ ለመግለጥ ነው።

[190] አቶ ሞሲሳ ራባ በ1904 ዓ.ም. ጥር 8 ቀን ወለጋ በሌቃ ወረዳ ሳሲጋ በሚባለው ቀበሌ ተወለደ። ከ1915 እስከ 1920 ዓ.ም. በስዊድን ኢቫንጂሊካል ሚሲዮን የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማረ። አቶ ኃይለ መስቀል ዕንኳለ ጽዮን በ1904 ዓ.ም. መስከረም 1 ቀን ሸዋ ደብረ ብርሃን ከተማ ተወለደ። ከ1913 እስከ 1916 ዓ.ም. በእንኮበር መድኃኔ ዓለም የንባብ ትምህርት እየተማረ አደገ። ከ1916 እስከ 1922 ዓ.ም. ድረስ በአዲስ አበባ ስዊድን ሚሲዮን ጉለሌ ተማሪ ቤት የእንግሊዝን ቋንቋ ተማረ። በዚህ ጊዜ አቶ ሞሲሳ ራባና አቶ ኃይለ መስቀል ዕንኳለ ጽዮን የ18 ዓመት ወጣቶች ነበሩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እነዚህ ወጣቶች የብላታ መርስዔ ኀዘንና የባለቤታቸው የወይዘሮ እታገኘሁ ቤተሰብ አካል ሆነው፣ ኀዘንንም ደስታንም አብረው ተካፍለው በቤተ ዘመድነትና በፍቅር እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ኖረዋል።

ጅጅጋን ቀድሞ ስለማላውቀው በመጀመሪያው ጉዞዬ ከቤተሰብ ጋር መሄድ ችግር እንደሚያስከትልብኝ ተመለከትሁ:: ስለዚህም ባለቤቴንና ልጆቼን አዲስ አበባ ላይ ትቼ ከአስተማሪው ከአቶ ናደው ደመራና ከዘመዴ ከታፈሰ በየነ ጋር በባቡር ተሣፍሬ በየካቲት ወር 1922 ዓ.ም. ተጓዝሁ:: ጅጅጋ ስደርስ የግዛቱ ዲሬክተር የልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ ቤት ጠባቂ አቶ ሥነ ተቀብሎ ማረፊያ ቤት ሰጥቶ አስተናገደኝ:: ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት በአስተማሪነት ሥራ ላይ ሳለሁ የተዋወቅሁት ወዳጄ ነው:: ከአንድ ዓመት በፊት የጅጅጋ አውራጃ ዲሬክተር ተብሎ ተሾሞ ከዋናው አገረ ገዥ ከፊታውራሪ መዝለቂያ ገብሬ ጋር እየሠራ ጅጅጋ ላይ ቈይቶ ነበር:: በዚህ ዓመት መጀመሪያም ፊታውራሪ መዝለቂያ ጅጅጋን ተሽረው ወደ ሌላ ስለ ተዛወሩ ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ አገሩን በማስተዳደር ላይ ሳለ ባለፈው ኅዳር ወር ወደ አዲስ አበባ ተጠርቶ ወጣ:: እዚያም እንዳለ ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል የጅጅጋ አገረ ገዥ ተብለው በታኅሣሥ 8 ቀን 1922 ዓ.ም. ስለ ተሾሙ ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ ሥራ ለመቀየር ወይም ለመተው በማሰብ ደጅ እየጠና ተቀመጠ:: እኔም ወደ ጅጅጋ መሄዴን ስለነገርሁት ለቤቱ ጠባቂ መልእክት አስተላልፎ ነበርና አሽከሩ አቶ ሥነ የተቀበለኝና ያስተናገደኝ በዚህ ምክንያት ነበር:: በዚህም ሁሉ ለልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ ምስጋና አቀርባለሁ:: ዘመዴ አቶ ታፈሰ በየነም ጅጅጋ ከአደረሰኝ በኋላ ከምስጋና ጋር ወደ አዲስ አበባ ተመልሷል::

በመጋቢት ወር 1922 ዓ.ም. የራስ ጉግሣ ወሌ ድል መሆንና የግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ሞት ተከታትሎ ስለ ተሰማ በንግሥቲቱ ሞት ሕዝቡ አዘነ:: የነገሩም ሁናቴ እንደሚከተለው ነው:: ራስ ጉግሣ ወሌ በመጋቢት 22 ቀን ሰኞ አንቺም በተባለ ሥፍራ ላይ ከጦር ሚኒስትሩ ከደጃዝማች ሙሉጌታ ጋራ ተዋግተው ነበር:: እርሳቸው ድል ስለሆኑም የምሥራች ቃል ከአዲስ አበባ ለያገሩ በቴሌግራም ሲላክ ወደ ጅጅጋም ተላለፈ:: አገረ ገዥው ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል መጋቢት 22 ቀን ረቡዕ የከተማውን ሕዝብ ሰብስበው የተላከውን የምሥራች ቃል በአሰሙ ጊዜ ተጨበጨበ:: የደስታ መግለጫ መድፍም ተተኵሶ በዓል ተደረገ::

ቀጥሎም በማግሥቱ ኀሙስ የግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ መሞትና የአልጋ ወራሽ ተፈሪ በዙፋን መተካት በቴሌግራም ስለ ተሰማ እንዳለፈው ጊዜ አገረ ገዥው ከእኩለ ቀን በኋላ ሕዝቡን ሰብስበው ስለ ንግሥቲቱ ሞት የቴሌግራሙን ቃል በአሰሙ ጊዜ የኀዘን መግለጫ መድፍ ተተኰሰ:: ሕዝቡም ጸጥ ብሎ ቆሞ የኀዘን ስሜቱን ገለጠ:: ንግሥቲቱ ያረፉት ትናንት መጋቢት 24 ቀን መሆኑን ሰምቻለሁ::

ከኀዘኑ ሥነ ሥርዓት ቀጥሎ አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የንጉሠ ነገሥትን ዙፋን ስለ መውረሳቸውና ስመ መንግሥታቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተብሎ መሰየሙ ተነገረና የደስታ መግለጫ ጭብጨባ ተጨበጨበ:: በጠቅላላ አነጋገር ያህ ዕለት የኀዘንና የደስታ በዓል በተፈራራቂ የተከበረበት ታሪካዊ ዕለት ነበር:: እኔም በሥፍራው ተገኝቼ የበዓሉ ተካፋይ ሆኛለሁ::



## ቤተሰቤን ወደ ጅጅጋ ስለማስመጣቴ

በጅጅጋ ነዋሪ ሆነው ከቆዩት ሰዎች ወምበሩ አቶ ዘለሌና ግምጃ ቤቱ አቶ አበበ ፍሬው እንዲሁም የጭንሐሰኑ አቶ ገብረ ማርያም እኔን አገር ለማስለመድ የወዳጅነት ስሜት አሳይተውኛል:: እኔም አገሩን ከተለማመድሁ በኋላ የመሐመድ ዓሊ ኩባንያ ወኪል አስገር ዓሊ በመደዳ ከአሠራቸው ቤቶች አራቱን ክፍል በ20 ብር ተከራይቼ በሚያዝያ ወር አዲስ ንብረት ማደራጀት ጀመርሁ:: በአሁኑ ጊዜ የወር ቀለቤ 80 ብርና ሁለት ዳውላ ማሽላ ስለሆነ የኑሮዬ ደረጃ ተሻሽሏል:: ጥቂት ቈይቶም የወር ቀለቤ እስከ 100 ብር ደርሷል::

ጓደኞቼ ልጅ ተስፋ ያየህ ይራድና[191] መዓዛ ወልደ ሕይወት በእኔ አጠገብ ከመደዳው ቤት እየተከራዩ በየክፍሎቹ ስለገቡ ጉርብትናቸው የሚያስደስት ሆነልኝ:: ልጅ ተስፋ ያየህ ይራድ አዲስ አበባ በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት በትምህርት ላይ የነበረ ወዳጄ ነው:: አሁን ወደ ጅጅጋ የወጣውም የጅጅጋ ጉምሩክ ሹመት ተሰጥቶት ነው:: አቶ መዓዛ ወልደ ሕይወትም የአዲስ አበባ ጊዮርጊስ ትክለኛ የነበረ ወጣት ደብተራ ከመሆኑ በላይ በአዲስ አበባ ጉምሩክ የመንግሥት ሠራተኛ የነበረ ምሁር ሰው ነው::

ቤት ተከራይቼ የቤት ዕቃዎችን ከአደራጀሁ በኋላ ባለቤቴ ወይዘሮ እታገኘሁ ባዬ ልጆቻችንን ይዛ በቶሎ እንድትመጣ ጻፍሁላት:: እርስዋም በግንቦት ወር ሁለቱን ልጆቻችንን ገብረ ክርስቶስንና ውብሸትን ይዛ አቶ ታደሰ ወልደ ማርያምንና የሴት ልጅ ዓለምን[192] አስከትላ በሚከተለው አኳኋን ተጕዛ መጣች::

ከአዲስ አበባ በባቡር ተሣፍራ ድሬዳዋ ስትደርስ ወዳጄ ባላምባራስ አሸኔ ኪዳነ ማርያም አደራ ብያቸው ነበርና ከጣቢያው ተቀብለው አስተናገዷት:: በማግሥቱም በኪራይ በቅሎዎች ወደ ሐረር እንድትጓዝ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ረዷት:: በዚያ ዘመን የመኪና መንገድ ስላልነበረ መንገዱ አስቸጋሪና አድካሚ ነበር:: በቅሎ አከራዩም እስከ ሥፍራው ድረስ ተከትሎ ስለሚሄድ በመንገድ ላይ አደገኛ ነገር እንዳያደርግ በታማኝነት የታወቀውን ሰው መምረጥ አስፈላጊ ነበር:: ባላምባራስ አሸኔ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ረዷት ያልኩትም ይህን በመሰለው ጉዳይ መርዳታቸውን ለመግለጥ ነው::

---

[191] የባላምባራስ ግርማ ያየህ ይራድና የልጅ መንበረ ያየህ ይራድ ወንድም:: በማይጨው ዘመቻ ሞቷል::

[192] ከታሪክ ጸሐፊው ባለቤት ከወይዘሮ እታገኘሁ ጋር ያደገች አገልጋይ:: የታሪክ ጸሐፊው ልጆች እንደ እናት የሚመለከቷት እስከ መጨረሻው ቤተሰብ ሆና የኖረች::



37 ልጅ ተስፋ ያየህ ይራድ

ከድሬዳዋ እስከ ሐረር በእግር መንገድ ርሕቀቱ 55 ኪሎ ሜትር ያህል ስለሆነ ለገሥጋሽ የአንድ ቀን ጕዞ ሲሆን በዝግታ ለሚሄድ ግን የሁለት ቀን መንገድ ነው። ባለቤቴም በሐረማያ ሐይቅ አጠገብ ከሆቴሉ አደረችና በማግሥቱ ሐረር ስትደርስ የአደራ ቃል በስልክ ያሳለፍሁለት ወዳጄ ልጅ ውብሸት ወልደ ዮሐንስ ተቀብሎ አስተናገዳት። እርሱ በዚያን ጊዜ የሐረር ግምጃ ቤት ሹም ነበር። በማግሥቱም ከአክስትዋ ከወይዘሮ አስካለ ጣሴ[193] ጋራ ስለተገናኘች አንድ ሳምንት ያህል ከእርሳቸው ዘንድ ዐርፋ ድካምዋን አቃለለች። በዚህ ጊዜ አቶ እሸቱ ተከተለውና ባለቤታቸው ወይዘሮ ቅጅነሽ የወዳጅነት አድራጎት ስለፈጸሙላት ባላውለታችን ሆነዋል።

[193] ወይዘሮ አስካለ ጣሴ የደጃዝማች ተፈሪና የቀኛዝማች እምሩ ሽሩባ ሠሪ ነበሩ። ባለቤታቸው አዛዥ ጣሴ የራስ መኰንን አጋፋሪ ነበሩ። "ወይዘሮ አስካለ የሚጠሩት በባላቸው ስም ነበር። በጡረታ አዲስ አበባ ከብላታ መርስዔ ኀዘን ጋር ሲኖሩ ቈይተው በ97 ዓመታቸው ዐርፈው ቀበና አቦ በወይዘሮ እታገኘሁና ብላታ መርስዔ ኀዘን መካነ መቃብር ተቀብረዋል።



ልጅ ውብሸት ወልደ ዮሐንስ ከዚህ በኋላ ለጅጅጋ ጕዞዋ በላይኛው አኳኋን የኪራይ በቅሎዎች አዘጋጅቶላት ከሐረር ስትነሣ ለእኔም በስልክ ስለ አስታወቀኝ በኪራይ በቅሎ እስከ ፋኛንቢራ ተጕዤ ተቀበልኋት። ከሐረር እስከ ጅጅጋ በእግር መንገድ ርሕቀቱ 100 ኪሎ ሜትር ያህል ስለሆነ የሁለት ቀን ጕዞ ነው ነጋዴዎች በፋኛንቢራና በጅጅጋ መካከል የሚገኘውን የሰንተላ ሸለቆ ከፀሐይ ትኩሳት ለማምለጥ ሲሉ ሌሊት በጨረቃ ብርሃን ያቋርጡት ነበርና እኛም ከእነርሱ ጋር በሌሊት ተጕዘን በረሃውን አቋረጥነው። ከነጋም በኋላ በካራመራ ላይ አልፈን አምስት ሰዓት ያህል ሲሆን ጅጅጋ ደረስንና ከአዲሱ ቤታችን ገባን። በዚህ ጊዜ ታላቁ ልጃችን ገብረ ክርስቶስ የ5 ዓመት ዕድሜ ሲኖረው ተከታዩ ውብሸትም የ3 ዓመት ዕድሜ ነበረው። ባለቤቴ ከዘመዶቿ ተለይታ እኔን ስትል ወደማታውቀው አገር ስትጓዝ ብዙ ድካም ስለደረሰባት ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀረብሁላት።

## ስለ አገሩ ሁናቴ

የጅጅጋን ከተማ የቆረቆሩ ራስ መኰንን ናቸው። ዘመኑም ከአድዋ ዘመቻ ቀደም ብሎ ነው ሲሉ ሰምቻለሁ። በመጀመሪያ ጊዜ ራስ መኰንን ለዚህ አገር አስተዳዳሪ ያደረጉት አብደላ ጠሃ የተባለውን አሽከራቸውን ነበር። ከሰገሌ ዘመቻ በኋላም ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያትና ቀኛዝማች ገድለ ጊዮርጊስ፣ ፊታውራሪ መዝለቂያ በየተራ ተሾመውበታል። አሁንም ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል እነሆ ይገኙበታል። ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት አገሩን ለማልማት ብዙ ጥረት ያደረጉ ስለመሆናቸው የከተማው ነዋሪዎች በብዙ ይተርኩላቸዋል።

ጅጅጋ (በሱማሌዎች አነጋገር ጅግጅጎ) በሜዳ ላይ የተሠራ ከተማ ነው። ባሁኑ ጊዜ ከ12 ሺህ ያላነሰ ሕዝብ ይኖርበታል። አውራጃው በወረዳና በቀበሌ የተመደቡ ክፍሎች አሉት። ወረዳዎቹ በርቷራ፣ ግሪ፣ ገደቡርሲ፣ ሐበር አወል፣ አበስጉል ይባላሉ። ቀበሌዎቹም የበሬ፣ ሡሪር ገራድ፣ መከኒሳ፣ አውበሬ የተባሉና ሌሎችም ናቸው። በአሁኑም ጊዜ ውጋዴን ወደ ጅጅጋ ስለ ተጨመረ ከድሮው የበለጠ ሆኖ ግዛቱ ተስፋፍቷል። የጅጅጋ ከተማ ከፍታው ከባሕር ወለል በላይ እስከ 1696 ሜትር ይደርሳል ይባላል። አየሩም በመጠኑ ሞቃት ነው። ሕዝቡ ለራሱ ወይም ለከብቶቹ የመጠጥ ውሐ የሚያገኘው ከተቆፈረ ጕድጓድ ነው። ከከተማው በስተደቡብ ምሥራቅ፣ የክረምት ጐርፍ በሚያልፍበት ወንዝ ላይ እያሌ የውሐ ጕድጓዶች ይገኛሉ። ባላገሩ ኤላ ይላቸዋል። መሬቱ አሸዋማ ስለሆነ በቀላሉ ሲደረመሱ ይታያል። ጅግጅጎ ማለት ተደርማሽ ማለት ነውና ጅጅጋ የሚለው ስም ከዚህ የመጣ ነው ብለው ተርከውልኛል።

በከተማው ዳር በስሜን በኩል የሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ይህ ቤተ ክርስቲያን ከከቢሬ ጦርነት በኋላ ራስ መኰንን የተከሉት ነው። ስለ ከቢሬ ከሰማሁትም ጥቂት ቃል እጽፋለሁ። የዚህ ሰው ደንበኛ ስሙ ሰይድ መሐመድ

ኢብን አብደላ ሐሰን[194] ነው። እንግሊዞች ስለ እርሱ በጻፉት መጽሐፍ ላይ ማድ ሙላህ ብለውታል።

ራስ መኰንን በ1891 ዓ.ም. በሐረር ግዛታቸው ላይ ደርበው ትግሬን በተሾሙ ጊዜ ለሐረር ግዛታቸው ግራዝማች ባንቴን እንደራሴ አድርገው ወደ ትግሬ ሄደው ነበር። ግራዝማች ባንቴም ለአገር ጥበቃ ደጃዝማች ብሩ ኃይለ ማርያምን ሐረር ላይ ትተው ግብር ለማስገበር ከጥቂት ወታደሮች ጋር በየካቲት 23 ቀን 1892 ዓ.ም. ወደ ውጋዴን ዘመቱ። ውጋዴን ደርሰው የግብሩን ከብት ከሰበሰቡ በኋላ ከብቱን እያስነዱ ሲመለሱ ከቢራ ከብዙ ሰው ጋር በስተኋላቸው ተከተላቸው። ባደሩበት እያደረ ሲከታተላቸው ሳለ ግራዝማች ባንቴ ጅጅጋ ደረሱና እንደ ምሽግ የሆነ ሥፍራ ይዘው ተዘጋጅተው ጠበቁት። ከቢራም በመጋቢት 12 ቀን 1892 ዓ.ም. ጅጅጋ ደርሶ ዙሪያውን ከበባቸው። የከቢራ ሠራዊት ብዙ ነበርና ምሽጉን ከቦ ብርቱ ውጊያ ከተዋጋ በኋላ ድል ስለሆነ ወደ ውጋዴን ተመለሰ። እንግዲህ የሚካኤል ታቦት የተተከለበት ምክንያት በዕለተ በዓሉ የተገኘውን የድል ረድኤት ለማዘከር ነው ይባላል። ውጊያ የተደረገበትም ሥፍራ አሁን የልዑል ራስ መኰንን ትምህርት ቤት በተከፈተበት ላይ መሆኑን ሰምቻለሁ።

## በጅጅጋ የማሠልጠኛ ተማሪ ቤት ስለ መቋሙ

*ስለ አውሮፕላን ነጂዎች*

አውሮፕላን በ1920 ዓ.ም. በነሐሴ ወር ከጅቡቲ መጥቶ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ ላይ ከዐረፈ በኋላ የአውሮፕላን ነጅነት ትምህርት አዲስ አበባ ላይ ተጀመረ። እንዲሁ ደግሞ በዚህ ዓመት (1922 ዓ.ም.) በሰኔ ወር ትምህርት ቤቱ ወደ ጅጅጋ ከተማ ተዛውሮ የትምህርቱ ሥራ እንዲቀጥል ተደረገ። ምክንያቱም የአዲስ አበባ ዝናሙና ጭቃው አስቸጋሪ መሆኑን፤ ጅጅጋ ግን የተመቸ ሥፍራ መሆኑን በመመልከት ነው። ስለዚህም አስተማሪው ሙሴ ቤዴልና ሚካኒሲዬው ሙሴ ፒካፔር ክረምቱን ሙሉ ሲያስተምሩና አውሮፕላን ሲያስነዱ ጅጅጋ ላይ ከረሙ። ተማሪዎቹ ብዙዎች ሲሆኑ በእነርሱ መካከል ሚሽካ ባቢቻፍና አስፋው ዓሊ የተባሉ እንደ ነበሩ አስታውሳለሁ።

---

[194] ሰይድ መሐመድ ኢብን አብደላ ሐሰን (ማድ ሙላህ) ስሙ የታወቀና የተጠራ ነው። ትውልዱ ውጋዴን ባሐ ግሬ ሲሆን የተወለደው ግን በእንግሊዝ ሶማሌ ግዛት ዱልበሐንቴ ላይ ነው። በልጅነቱ ወራት በሼኾች ዘንድ ቁርአን እየተማረ ካደገ በኋላ ወደ ሱዳንና ወደ ዐረብ አገር ሄዶ ዐረቢኛና እንግሊዝኛ ተምሮ ብዙ መጽሐፍ ስለ ጻፈ ሙላህ (ማኡላ) ተባለ። ሊቅ ወይም ምሁር ማለት ነው። እንግሊዞችም ማድ ሙላህ (እብዱ ሙላህ) እያሉ ስለ እርሱ ብዙ መጻሐፍ ጽፈዋል። ሐበሾችም ከቢራ በሚል ስም ጠርተውታል። ከቢራ የእስላም ሊቅ የሚጠራበት የተለመደ የክብር ስም ነው። ከመርስዔ ኅዘን ወልደ ቂርቆስ *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ* መጽሐፍ ገጽ 238-239 የተወሰደ።





38 ፊታውራሪ ታፈሰ፣ ሙሴ ቤዴል፣ ካፒቴን ዊድሜር

*ስለ ጦር መኰንኖች*

አዲስ አበባ ላይ በተቋቋመው የጦር ትምህርት ቤት ቤልጅኮች የክብር ዘበኞችን ማሠልጠን ጀምረው ነበር። ይህም ሥራ በይበልጥ እንዲስፋፋ የመንግሥት ፍላጎት ስለሆነ ካፒቴን ዊድሜር የተባለ አንድ ፈረንሳዊ ተቀጥሮ መጥቶ በጅጅጋ ከተማ ኢትዮጵያውያን የጦር መኰንኖችን ሲያስተምርና ሲያሠለጥን ከረመ። የጦር መኰንኖቹ በመጪው ዓመት በጥቅምት 23 ቀን ስለሚደረገው የዘውድ በዓል ክብር ከውጭ አገር የሚመጡትን እንግዶች በክብር ለመቀበል የተዘጋጁና የበቁ ሆነው መገኘት ነበረባቸውና ክረምቱን ያለ ዕረፍት በትጋት ሲማሩ ከረሙ። በዚህ ጊዜ ዘውድነህ ቅጣው የተባለ ፈረንሳዊኛ ዐዋቂ ወጣት ለካፒቴኑ አስተርጓሚ ሆኖ አብሮ በትጋት ሲሠራ እንደ ከረመ አስታውሳለሁ።

## ስለ ወሰን ጠባቂዎች

ቀድሞ የክብር ዘበኛን ያሠለጠኑት ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ ለውጋዴን ጠረፍ ጠባቂ የሚሆን ጭፍራ እያስተማሩ እንዲያሠለጥኑ ስለታዘዙ ከአንድ ሻምበል ጦር ጋራ ከአዲስ አበባ ወደ ጅጅጋ በግንቦት ወር 1922 ዓ.ም. መጥተው ይሠሩ ጀመር። እኒህ ሰው ጎረቤቴ ስለሆኑ በምሥራቅ አፍሪካ ሳሉ የጦር ትምህርት ለመማር የቻሉበትን ሁናቴ ስለ ተረኩልኝ ትጋታቸው ያስደንቀኝ ነበር።

## በወሰን ላይ ስለ ደረሰ ግጭት

በጅጅጋ በኩል ባለው ወሰን ላይ በእንግሊዝ ኢላሎችና[195] በኢትዮጵያ ወታደሮች መካከል በሰኔ መጨረሻ ግድም ግጭት ሆኖ አራት የጅጅጋ ወታደሮች ተገደሉ። በዚህም ምክንያት ሁለቱ መንግሥታት (እንግሊዝና ኢትዮጵያ) በየበኩላቸው ያዘዙዋቸው ሹማምንት ወደ ሥፍራው ሄደው ነገሩን ይመረምሩ ጀመር። የግጭቱ አነሣሥና የነገሩ ሁናቴ እንደሚከተለው ነበር።

በጅጅጋ በኩል ያለው የሁለቱ መንግሥታት ግዛት የወሰን መስመር በግንቦት 7 ቀን 1889 ዓ.ም. በተፈረመ ውል ተጠቅሶ ከመጻፉ በስተቀር በመሬት ላይ የተከለለ የወሰን ምልክት አልነበረውም። ስለዚህም የገደቡርሲን ጎሣዎች በያመቱ ግብር የሚያስገብሩ የጅጅጋ ወታደሮች በገደቡርሲ ወረዳ እስከ ፍሉንፋል ኮረብታ እየሄዱ ግብር ሲቀበሉ ይኖሩ ነበር። በዚህም ዓመት ግብር ለማስገባት ከጅጅጋ የተላኩ ዓሥር ወታደሮች ወደ ገደቡርሲ ሄደው፣ የቈየውን ልማድ በመከተል እስከ ፍሉንፋል ኮረብታ ድረስ ሄዱና ከዘላኖቹ የግብር ከብት ተቀብለው እየነዱ ወደ ሜራሌ ተመለሱ። ይህን ነገር የእንግሊዝ ኢላሎች በሰሙ ጊዜ ከቦረማ ከተማ ተነሥተው ወዲያው ዕለቱን ተከታተሉዋቸው። በማግሥቱም የጅጅጋ ወታደሮች ወደ ሠፈሩበት ወደ ሜራሌ ደርሰው "በእንግሊዝ ግዛት ውስጥ ገብታችኋልና እጃችሁን ስጡን" ብለው ጠየቁዋቸው። ወታደሮቹም "ይህ ያለንበት ሥፍራ የኢትዮጵያ ግዛት ስለሆነ እጃችንን አንሰጥም" በማለት እንቢ ስላሉ ጠብ ተነሥቶ ተኩስ ተጀመረና አራት የጅጅጋ ወታደሮች ተገደሉ። የቀሩትም ሸሽተው ጅጅጋ ገብተው የደረሰባቸውን ነገር ለአለቆቻቸው አስታወቁ።

ይህ ግጭት በሁለቱ መንግሥታት ዘንድ ስለ ተሰማ ሹማምንታቸው ወደ ሥፍራው ሄደው ነገሩን በኮሚሲዮን እንዲመረምሩ በየበኩላቸው አዘዙ። በእንግሊዝ መንግሥት በኩል የታዘዘው የእንግሊዝ ሱማሌላንድ ዋና ጸሐፊ ሜጀር ሎሬንስ ሲሆን፣ በኢትዮጵያም መንግሥት በኩል የጅጅጋ አውራጃ ገዥ ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ታዘዙ። በሐርጌሣ ተቀማጭ የሆኑት የኢትዮጵያ ቆንስል አቶ ዘውዴ ታደሰም በተጨማሪ ታዘዙ።

ከዚህ በኋላ ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል በጅጅጋ ካሉት ሹማምንትና ሠራተኞች አንዳንዶችን አስከትለው በሐምሌ 7 ቀን 1922 ዓ.ም. ወደ ገደቡርሲ ተጓዙ። የጦር መኰንኖችን ለማሠልጠን የመጣ ካፕቴን ዊድሜርና እኔ የጉዳዩ ተካፋይ በመሆን አብረን ተጓዝን። እንግዲህ ከጅጅጋ በተነሡበት በመጀመሪያ ቀን ሸበሌ ከተማ አደሩና በማግሥቱ ጕግቲ ደርሰው ሠፈሩ። ጕግቲ ለገደቡርሲዎችና ለኢሣዎች አማካይ ሥፍራ ከመሆንዋ በላይ ለወሰንም

[195] ኢላሎ ማለት ደንበኛ ወታደር ሳይሆን የአገርን ጸጥታ የሚጠብቅ ዘበኛ ማለት ነው። (መ.ኀ.ወ.ቂ.)



የቀረበች ናት። ከጅጅጋም 80 ኪሎ ሜትር ያህል የምትርቅ ይመስለኛል። ስለዚህም ጕግቲ የሕዝብ መሥፈሪያ ከተማ እንድትሆን በዚሁ ጊዜ በፊታውራሪ ታፈሰ ለከተማነት ተቆረቆረች። ስለ ጸጥታ ጥበቃም አንድ የመቶ አለቃ ከነጭፍራው እንዲቀመጥበት ተደረገ።

ከዚህ በኋላ ፊታውራሪ ታፈሰ ከጕግቲ ተነሥተው ጕዞአቸውን ወደ ምሥራቅ ቀጠሉና አውቡባ ላይ ሠፈሩ። አውቡባ በሜራሌና በትልቁ የደረብሌ ተራራ መካከል የሚገኝ የእስላሞች ቅዱስ ሥፍራ ነው። የጥንት መስጊድ ፍርስራሽ ይታይበታል። ደረብሌ የተባለው ተራራ ከጫፉ ላይ ሆኖ ሌሊት ወደ ህንድ ውቅያኖስ ለሚመለከት ሰው የመርከቦችን መብራት የሚያሳይ ከፍተኛ ተራራ ነው።

ከእንግሊዝ መንግሥት በኩል የታዘዘው ሜጀር ሎሬንስ ሠፈሩን ለአውቡባ አቅራቢያ በሆነች በቆልጭድ ኮረብታ ሥር አደረገ። ከዚያም በኋላ የኮሚሲዮኑ ስብሰባ በየተራ በሁለቱም ሠፈር በአውቡባና በቆልጭድ ላይ እየተደረገ የነገሩ ምርምራ ተጀመረ። ጠብ ወደ ተደረገባቸውም ሥፍራዎች ወደ ፍሉንፋልና ወደ ሜራሌ እየሄዱ አገሩን ተመለከቱ። የአራቱን ወታደሮችም መቃብር በሜራሌ ላይ ጐበኙ።

የምርመራውና የጕብኝቱ ሥራ ዓሥራ አምስት ቀን ያህል ቀጥሎ ከተፈጸመ በኋላ ግጭት ሊደርስ የቻለው የወሰን ክልል ባለመኖሩ ምክንያት መሆኑ ስለታወቀ የምርመራው ውጤት ይኸው ሆነ። ምክንያቱም ፍሉንፋልንና ሜራሌን እንግሊዞችም ኢትዮጵያውያንም በበኩላቸው የእኛ ግዛት ናቸው ስለሚሉ ወሰን አልፎ የገባው የትኛው ወገን እንደሆነ ለመለየት ስላልተቻለ ነው።

ስለዚህ በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ሱማሌላንድ ግዛት መካከል ያለው ወሰን በውሉ መሠረት በመሬት ላይ በቶሎ እንዲከለል ሁለቱም ወገኖች ለየመንግሥታቸው እንዲያሳስቡ፣ እስከዚያም ድረስ በየጊዜው ግጭት እንዳይፈጠር በቆልጭድ ኮረብታ ሥር አድርጎ ወደ ሐሪራድ ወንዝ የሚወስደው የእግር መንገድ ለሁለቱም ወገኖች ሠራተኞች ጊዜያዊ የወሰን ምልክት ሆኖ እንዲቈይና የሁለቱም ወገኖች ሠራተኞች እንዳይተላለፉት ስምምነት ተፈርሞ ስብሰባው ተፈጸመ። ይህ ጊዜያዊ ወሰን ትልቁን ተራራ ደረብሌን ወደ ኢትዮጵያ አስቀርቶ በሥሩ የሚያልፍ ነው።

ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያውያኑ ሹማምንት ከአውቡባ ሠፈር ተነሥተው ሱተዋ የሚባለውን ወንዝ ተሻግረው እርሻ ባለበት በደበቡር ላይ ሠፈሩ። ከዚያም ተነሥተው ጕዞአቸውን ቀጠሉና የእንግሊዞችን ከተማ ቦረማን በስተ ምሥራቅ እየተመለከቱ በሰው ጋራ ሥር አልፈው ተፈሪ በር ከተማ ገቡ። እርሱም ባላገሩ አውበሬ እያለ የሚጠራው ነው። ከጕግቲ እስከ አውበሬ (ተፈሪ በር) ርሕቀቱ 70 ኪሎ ሜትር ያህል ነው። ፊታውራሪ ታፈሰ በተፈሪ በር

ባላባቶቹን እና ግራዝማች ዶዲን እያነጋገሩ ጥቂት ቀን ከቆዩ በኋላ ወደ ጅጅጋ ተመልሰዋል። ተፈሪ በር ከጅጅጋ 73 ኪሎ ሜትር ያህል የሚርቅ ነው።

በዚህ ግጭት ምክንያት የተገኘው የምርመራ ውጤት፣ ለወሰን ክልል ሥራ ምክንያት ሆኖ እንዳገለገለ ወደፊት ልንመለከት ነው። እኔም ይህን ግጭት ታሪክ የጻፍሁት ወደፊት ለሚከተለው የወሰን ክልል ሥራ መነሻ የሆነውን ሰበብ በቅድሚያ መግለጽ ጠቃሚ መስሎ ስለ ታየኝ ነው።

## ስለ ልዩ ልዩ ነገር

የጅጅጋ ከተማ በዚህ ዓመት ስለ ተስፋፋና ልዩ ልዩ ድርጅቶች ስለ ተቋቋሙበት በሐምሌ ወር 1922 ዓ.ም. በልዕልት የሺ እመቤት ስም የተሰየመ አንድ ሆስፒታል በከተማው መካከል ተከፈተ። ዋናው ሐኪም ዶክቶር ሾትዚንገር የተባለ ጀርመናዊ ሲሆን ረዳቶችም ነበሩት።

የሆስፒታሉም ዲሬክተርነት ለትምህርት ቤቱ ሹም በተጨማሪ ስለተሰጠው ከሐምሌ 26 ቀን 1922 ጀምሮ እስከ ኅዳር 27 ቀን 1923 ዓ.ም. አስተዳዳሪ ሆኖ ሠርቷል።

ከዚህ በፊት የከተማው ሕዝብ የሕክምና እርዳታ የሚያገኘው አባ አንገር የተባሉ ካቶሊካዊ መነኵሴ በሚሲዮናቸው አጠገብ ካቆሙት ከአንድ ትንሽ ክሊኒክ ብቻ ነበር። አሁን ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ይህ ሆስፒታል ተከፍቶለታል።

የአክስቴ የእመዬት በሰሙ አልታመን ሞት በሰኔ ወር ተነገረኝና ኀዘን አደረግሁ። እመዬት በሰሙ አልታመን የአባቴ ታላቅ እኅት ናት። ከዚህም በላይ በሕፃንነቴ በብዙ ድካም ስላሳደገችኝ እምዬ የምላት እናቴ ነበረች። በ87 ዓመት ዕድሜዋ ግንቦት 26 ቀን 1922 ዓ.ም. ዐርፋ ጅሩ በበደበጅ መግደላዊት ተቀበረች።

ባለቤቴ ወይዘሮ እታገኘሁ ባዬ በነሐሴ 12 ቀን 1922 ዓ.ም. ሴት ልጅ በደህና ስለ ተገላገለች ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረብሁ። አያትዋ ወይዘሮ ብርቱ ነፍሰ ጡር መሆኑዋን ስለሚያውቁ እርስዋን ለመርዳት ቀደም ብለው በሐምሌ ወር ከሸዋ መጥተው ነበርና ከፍ ያለ እርዳታ አደረጉላት። 20 ቀን ያህል ከቆዩ በኋላም ወደ ሸዋ ተመልሰዋል። ይህች ልጅ በኋላ ጊዜ ሮማን ወርቅ ብለን ስም ያወጣንላት ልጃችን ናት። በተወለደች በ80 ቀን ሥርዓተ ጥምቀትዋ የተፈጸመው በጅጅጋ ቅዱስ ሚካኤል ሆኖ የክርስትና ስምዋ ሥርጉተ መድኅን ተባለ። የክርስትና ልጅነትዋንም ለታቦቱ ስለ ሰጠን የቤተ ክርስቲያኑ ዓቃቢት ጣትዋን ይዛ ክርስትና እንሥታታለች።





39 መርስዔ ኀዘን ጅጅጋ ከቤተሳቦቻው ጋር። ከግራ ወደ ቀኝ ወይዘሮ እታገኘሁ፣ ገብረ ክርስቶስ፣ ውብሸት፣ መርስዔ ኀዘን

ፊታውራሪ ገብረ ማርያም ጋሪ[196] በግንቦት 20 ቀን 1922 ዓ.ም. ደጃዝማች ተብለው የሐረርን እንደራሴነት ስለተሾሙ የደስታ መግለጫ ደብዳቤ ልኬላቸው ነበር። አሁንም ወደ ሹመታቸው ወደ ሐረር መምጣታቸውን ስለ ሰማሁ በሐምሌ መጨረሻ ወደ ሐረር ሄጄ እንኳን ደስ ያልዎት ብያቸው ተመለስሁ። ደጃዝማች ገብረ ማርያም ጋሪ የወዳጄ የልጅ ተፈራ አባት ከመሆናቸው በላይ የፍቅርና አገልግሎት ማኅበር አባል በመሆናቸው በወዳጅነት ተቀራርበናልና በሹመታቸው ተደስቼ ነበር።

[196] ፊታውራሪ (ደጃዝማች) ገብረ ማርያም ጋሪ የጉራጌ ተወላጅ ናቸው። የደጃዝማች ባልቻ አሽከር ነበሩ። ከዚያም የአልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ አጋፋሪ ሆኑ። ሐረርጌን በእንደራሴነት ተሾመው አስተዳድረዋል። በመጨረሻም ወደ አዲስ አበባ ተዛውረው የአገር ግዛት ሚኒስትር ሆኑ። በጠላት ወረራ ጊዜ ከራስ ደስታ ጋር ሆነው ሲዋጉ በ1929 ዓ.ም. በጥይት ተመትተው ሞቱ። ምንጭ - ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል (ብላቴን ጌታ)፣ *የኢትዮጵያ ባህል ጥናት፣ ቸ በለው።*



40 ወይዘሮ እታገኘሁ ጅጅጋ ከወዳጆቻቸው ጋር፡፡ ከግራ ወደ ቀኝ የቆሙ መንገሻ ኃይሌ፣ ሞሲሳ ራባ፣ ኃይለ መስቀል እጓለ ጽዮን፡፡ የተቀመጡ ወይዘሮ እታገኘሁ ባዬ፣ ወይዘሮ ብርሃኔ አዳሙ (የአቶ ኃይለ መስቀል ባለቤት)

# ምዕራፍ 30

## 1923 ዓመተ ምሕረት

በአውሮፕላን ነጅነት ስለ ተመረቁ ወጣቶች፣ ስለ ጦር መኰንኖች፣ ስለ ልዩ ልዩ ነገር፣ ስለ ዘውድ በዓል፣ ስለ አዲሱ የጅጅጋ አገረ ገዥ፣ ስለ ትምህርት ቤት በዓል፣ ስለ ሕገ መንግሥት በዓል፣ ስለ ውጋዴን፣ ስለ ልዩ ልዩ ነገር

### በአውሮፕላን ነጅነት ስለ ተመረቁ ወጣቶች

አዲሱ ዓመት 1923 ዓ.ም. ገሙስ ባተ፡፡ ዘመኑም ዘመነ ሉቃስ ነው፡፡ ባለፈው ዘመን ጅጅጋ ላይ የተቋቋመው የአውሮፕላን ነጅነት ማሠልጠኛ ድርጅት በአሠልጣኙ በሙሴ ቤዶል መሪነት ሥራውን በትጋት ቀጥሎ ከርሞ ነበርና አሁን በመስከረም የአሠልጣኝነቱን ውጤት ማሳየት ሊጀምር ነው፡፡

ከተማሪዎቹ መካከል አስፋው ዓሊና ሚሽካ ባቢቼፍ[197] በቶሎ ሠልጥነው ለነጅነት ስለ በቁ ችሎታቸው በአስተማሪውና የመንግሥት ተመልካቾች በሆኑ ሹማምንት ተፈትኖ እንዲረጋገጥ በአገረ ገዥው በኩል ትእዛዝ ተሰጠ፡፡ በዚህ መሠረት ሦስት ሹማምንት በመስከረም 14 እና 15 ቀን 1923 ዓ.ም. ከእያንዳንዳቸው ጋራ በየተራ በአየር ላይ በመብረር ፈተና አድርገው ነጅዎቹ ያለ መሪ ወይም ያለ አስተማሪ ብቻቸውን አውሮፕላን ከመሬት ለማስነሣትና ለማሳረፍ፣ በአየር ላይ ለማብረር መቻላቸውን ተመለከቱ፡፡

ከዚህ በኋላ በከተማው ላሉት ታላላቅ ሰዎች ጥሪ ተደርጎ አገረ ገዥው ባሉበት በአውሮፕላን ሜዳ የምረቃ በዓል ተደረገ፡፡ በዚያም ዕለት ሁለቱ ተመራቂዎች በየተራ አውሮፕላን እያስነሡና እያሳረፉ ሞያቸውን ለሕዝቡ ከአሳዩ በኋላ ሻምፓኝ ተከፍቶ ተጨበጨበላቸው፡፡ ቀጥሎም ፈታኞቹ ሹማምንት የበረራ ምስክር ወረቀት ጽፈውና ፈርመው ስለ ሰጧቸው ወረቀቱን ይዘው እነርሱ ራሳቸው አውሮፕላን እየነዱ ወደ አዲስ አበባ ወጡ፡፡

አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ የነጅነት ችሎታቸውን በሥራ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አሳይተው የኒሻን ሽልማት ተቀበሉ፡፡ የተሰጣቸውም የበረራ ምስክር

[197] አባቱ ፊታውራሪ ባቢቼፍ የሚባሉ ሩሲያዊ ነበሩ፡፡ ፊታውራሪ ባቢቼፍ ከወይዘሮ ተነበች ወልደ ጻድቅ ሚሽካንና ሌሎችንም ልጆች ወልደዋል፡፡ የሚሽካ እኅት እፀደ የከንቲባ ነሲቡ ዘማኤል ሚስት ነበረች፡፡ የከንቲባ ነሲቡና የወይዘሮ እፀደ ልጅ የሆነችው ማርታ ነሲቡ የቤተሰቡን ታሪክ Memorie di una Principessa Ethiope በሚል ርእስ እ.ፈ.አ. በ2005 በኢጣልያንኛ አሳትማ አውጥታለች፡፡

ወረቀቱም በግርማዊነታቸው ታይቶ ስለ ጸደቀ «ለኢትዮጵያውያን ነጅነት ተቀዳሚ ሆኑ» እየተባሉ ተመሰገኑ። ቃሉ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።



10 የበረራው የምስክር ወረቀት

*እኛ ከዚህ በታች ፊርማችንን የፈረምን ልጅ ተሰፋ ያየህ ይራድ አቶ መርስዔ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ አቶ መዓዛ ወልደ ሕይወት የአሮፕላን ተማሪዎች አስፋው አሊና ሚሽካ ባቢቼፍ ትምርታቸውን ጨርሰው ፈተና ያደረጉበት በመስከረም ፲፱ ና ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት በክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ቃል የመንግሥት ተመልካቾች ሆነን ሄደን አስተማሪያቸው ሙሴ ቤዴል የሰጡዋቸውን ፈተና ሁሉ በያይነቱ መፈጸማቸውን አይተናል እኛ ም እራሳችን እያንዳንዳችን ከያንዳንዳቸው ጋራ ወደአየር ወጥተን ያመለከትናቸው አኳያ ሁሉ እየሄዱ በደኅና ማብረራቸውንና ሊያስነሱም ሊየሳርፉም ያለ አንዳች ችግር ለመሥራት መቻላቸውን እንመሰክራለን*

*መስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት ጅጅጋ*

የሚል ሆኖ ሦስቱ የመንግሥት ተመልካቾች ፈርመውበታል። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም የነጅነት ችሎታቸውን አይተው ከተረዱ በኋላ በወረቀቱ እግርጌ የሚከተለውን ቃል በመጻፍ አረጋገጡላቸው።

*አስፋውና ሚሽካ ባቢቼፍ በኢትዮጵያ መጀመሪያ አውሮፕላን መንዳት ስለተማሩ ፈተናቸውን ፈጽመው መንዳታቸውን አይተናል። ስለዚህም ዕውቀት ተቀዳሚ በመሆናቸው ምስጋና ይገባቸዋል።*

*ጥቅምት 3 ቀን 1923 ዓ.ም.*

*ቀ. ኃይለ ሥላሴ ን.ነ.*

በተጨማሪም ልዑል አስፋ ወሰንና ልዑል መኰንን ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴና አስተማሪዎቹ ፈርመውበት ለነጅዎቹ ተሰጠ።





41 አስፋው ዓሊ በልምምድ ላይ

## ስለ ጦር መኰንኖች

ካፕቴን ዊድሜር የተባለ ፈረንሣዊ ባለፈው ክረምት በጅጅጋ ከተማ ያስተማራቸውና ያሠለጠናቸው የጦር መኰንኖች በመስከረም መጨረሻ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱና ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፊት በሰልፍ ቀርበው ሰላምታ ሰጡ። እነዚህ የጦር መኰንኖች ለዘውድ በዓል ክብር ከውጪ አገር የሚመጡ የመንግሥታት መልእክተኞችን ለመቀበልና የበዓሉን ሥነ ሥርዓት ለማክበር በሚገባ የሠለጠኑ ስለሆኑ ወዲያው በየተመደበላቸው ሥራ ተሰማርተው ይሠሩ ጀመር።

## ስለ ዘውድ በዓል

የቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል ጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ.ም. እሑድ እንደሚከበር ቀደም ብሎ በፕሮግራም ስለ ተገለጸ እንደሌላው ከተማ ሁሉ በጅጅጋም አስፈላጊው ነገር ሲዘጋጅ ሰነበተ። ለምሳሌ እኔ ባለሁበት በትምህርት ቤቱ በኩል ተማሪዎች በነጭ ልብስና መለዮ ተሰልፈው በበዓሉ ሥፍራ እንዲገኙና መዝሙር እንዲዘምሩ ተደረገ። ሌላውም ክፍል እንዴት እንደሚሰለፍ ሥነ ሥርዓት ተበጅቶለት ሲሰናዳ ሰነበተ።

ከበዓሉ ቀን በፊት በጥቅምት 20 ቀን ሁለት የእንግሊዝ አውሮፕላኖች ከእንግሊዝ ሱማሌላንድ ግዛት እየበረሩ መጥተው በጅጅጋ የአውሮፕላን ሜዳ

ስላረፉ ያለፈቃድ መጥተዋል ተብለው አውሮፕላኖቹ በወታደር ተከበቡና ጥቂት ጭቅጭቅ ተፈጠረ። የነገሩም ሁናቴ እንደ ሚከተለው ነበር።



42 የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንግሥ በዓል

እንግሊዞች የኢትዮጵያን መንግሥት ደስ ለማሰኘትና የወዳጅነት ስሜት ለመግለጽ ስለፈለጉ "በዘውድ በዓል ቀን በአየር ላይ እየበረሩ በዓሉን የሚያደምቁ አውሮፕላኖች እንላክ" ብለው የኢትዮጵያን መንግሥት ጠይቀው ኖሮአል። ጥያቄያቸው ስለመፈቀዱም ለእንግሊዞች መልስ ተሰጥቷል። ወደ ጅጅጋ ግን የተላለፈ አንዳች ነገር አልነበረም።

እንግዲህ የእንግሊዝ አውሮፕላኖች መጥተው ጅጅጋ ላይ ሲያርፉ ያለፍቃድ መጣችሁ ተብለው ባገሩ ባለሥልጣን ተያዙ። እንግሊዞቹ በፈቃድና በወዳጅነት ብንመጣ እንዴት ተደፈርን ብለው ቢበሳጩም በፈቃድ መምጣታችሁን አናውቅም ተብሎ ተመለሰላቸው። የሆነ ሆኖ አውሮፕላኖቹ በወታደር ዘብ እንዲጠበቁ ተደረገና ሰዎቹ ለእንግሊዝ ቆንስል ለካፕቴን ሎንግ ተላለፉ። በጅጅጋና በአዲስ አበባ መካከል የቴሌግራም ልውውጥ ከተደረገ በኋላም የስሕተት ነገር መሆኑ ለእንግሊዞቹ ተገለጸላቸው። ነገሩ በዚህ ታለፈ። ይህም በዘመኑ የሥራ አመራር ላይ የነበረውን ደካማነት የሚያመለክት ነው።



ከዚህ በኋላ አውሮፕላኖቹ ተለቅቀው በማግሥቱ ወደ አዲስ አበባ ተጓዙ። በበዓሉም ቀን እሑድ ወደ አየር መጥቀው በመብረርና በመዘዋወር በዓሉን ሲያደምቁ መዋላቸውን ሰምቻለሁ።

ጥቅምት 23 ቀን እሑድ ጅጅጋ በአገረ ገዥው መኖሪያ ግቢ ሕዝቡ ተሰብስቦ በዓሉን አከበርን። ዋናው ጸሐፊ አቶ ብሩ ንግግር አድርጎ እንዳበቃ የደስታ መግለጫ መድፍ ተተኰሰ።



43 ሐረር ላይ የንግሡ በዓል ሲከበር። ከግራ ወደ ቀኝ የተቀመጡ ቢሾፕ ዣሩሶ፣ ማዳም ፕላውማን፣ ደጃዝማች እምሩ ኃይለ ሥላሴ፣ ሚስተር ፕላውማን (የእንግሊዝ ቆንስል)፣ ማዳም አሞ

የዘውዱ በዓል በአዲስ አበባ ላይ ደምቆ እንደ ተከበረ ሰምቻለሁ። የዓሥራ አንድ መንግሥታት መልክተኞችም የበዓሉ ተካፋይ ሆነው ተገኝተው ነበር። መልክተኞች የላኩት የነገሥታትና የፕሬዜዳንቶች ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው።

የእንግሊዝ ንጉሥ
የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ፕሬዜዳንት
የጃፓን ንጉሠ ነገሥት
የሆላንድ ንግሥት
የኢጣልያ ንጉሥ
የፈረንሳይ ሬፑብሊክ ፕሬዜዳንት
የግሪክ ሬፑብሊክ ፕሬዜዳንት
የስዊድን ንጉሥ
የጀርመን ሬፑብሊክ ፕሬዜዳንት
የቤልጅክ ንጉሥ
የግብጽ ንጉሥ
የእስክንድርያ ፓትሪያርክ

የበዓሉ አከባበርና የሥርዓተ ንግሡ አፈጻጸም እጅግ ከፍ ያለ ስለመሆኑ በዘመኑ የተበተኑትን ጽሑፎች በማንበብና በሥፍራው የነበሩትን ሰዎች በመጠየቅ የተረዳሁትን ያህል በዝርዝር ጽፌ በማስታወሻዬ አስቀመጥሁት። እርሱም የዘመን ታሪክ በጻፍሁበት በሌላው ክፍል መጽሐፍ የሚገኘው ነው። አሁንም የዘውዱን በዓል ታሪክ እዚህ ላይ አቁሜ ስለ ራሴ የማስታውሰውን ትዝታዬን እቀጥላለሁ።

## ስለ አዲሱ የጅጅጋ አገረ ገዥ

የጅጅጋ አገረ ገዥ ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል የዘውድ በዓል ለማክበር በጥቅምት መጀመሪያ ላይ ወደ አዲስ አበባ ስለ መውጣታቸው በገጽ 221 በጻፍሁት ገልጫለሁ። ከበዓሉም በኋላ ወደ ጅጅጋ አልተመለሱም ነበርና ሦስት ወር ያህል እንደቆዩ በጥር 7 ቀን 1923 ዓ.ም. አዲስ አበባ ላይ በተደረገው ሹም ሽር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል የሥራ ሚኒስቴርን መሾማቸው፣ ፊታውራሪ መዝለቂያ ገብሬ የጅጅጋ አገረ ገዥ ሆነው መሾማቸው በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተገለጠ። ከዚህም በኋላ አዲሱ አገረ ገዥ ፊታውራሪ መዝለቂያ በየካቲት ወር ወደ ጅጅጋ መጥተው ሥራቸውን ጀምረዋል።

አቶ መዓዛ ወልደ ሕይወትም አዲስ አበባ ላይ ቈይቶ ነበርና በጉምሩክ ክፍል ሌላ ሥራ ተሰጥቶት መቅረቱ ተሰማ። ስለዚህም እኔ ወኪል የሆንሁበት የጅጅጋ ማዘጋጃ ቤት ሹመቱ ከዚህ በኋላ ለባሻ ዳምጤ ተላልፎአል።

## ስለ ትምህርት ቤት በዓል

የጅጅጋ ትምህርት ቤት በቆመው በውስጥ ደንቡ መሠረት ትምህርት ቤቱ ለአንድ ወር ስለ ዕረፍት የሚዘጋው በያመቱ በመጋቢት 13 ቀን ነው። እንዲህ የሆነበትም ምክንያት አገሩ በረሃማ ነውና የሙቀቱን ወራት በዕረፍት ላይ ማሳለፍ ለአስተማሪም ሆነ ለተማሪ የተመቸ መሆኑን በመመልከት ነው።

ትምህርት ቤቱ ለዕረፍት የሚዘጋበትን በዓል ለማክበር መጋቢት 13 ቀን 1923 ዓ.ም. ቅዳሜ አገረ ገዥውና ጥሪ የተደረገላቸው ሰዎች ተሰበሰቡ። ተማሪዎቹም በዚያ በባለ ነጭ መለዮ ልብሳቸው ተሰልፈው መዝሙር እየዘመሩ እንግዶቹን ተቀበሉ። የተማሪዎቹ ቊጥር 143 ነበር።

ከዚህ በኋላ ዲስኩር ተናግሬ ሳበቃ አገረ ገዥው አጭር ቃል ተናግረው መልስ ሰጡ። ከዚያ ቀጥሎም ስልፍ አስተማሪው አቶ መንገሻ ኃይሌ በእንግሊዝ የምሥራቅ አፍሪካ ግዛት በኬንያ የወታደርነት ትምህርት የተማረና የሠለጠነ እንደ መሆኑ መጠን ለተማሪዎቹ ልዩ ልዩ ጅምናስቲክ አስተምሯቸው ነበርና በዚህ ቀን የጅምናስቲክ ሞያቸውን በማሳየት አገር ገዥውንና እንግዶችን ደስ አሰኙ። በመጨረሻም ከፍተኛ የትምህርት ማርክ ላገኙት ልጆች ከየክፍሉ እስከ



ሦስተኛ ደረጃ ድረስ የመጽሐፍ ሽልማት ተሰጣቸውና የሻይ ግብዣ ተደርጎ ሥነ በዓሉ አለቀ።



11 ስለ ትምህርት ቤቱ በዓል ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ የወጣ

የአንዱ ወር ዕረፍት ከአለቀ በኋላም ትምህርት ቤቱ በሚያዝያ 12 ቀን 1923 ዓ.ም. ሰኞ ተከፍቶ ሥራ እንደ ጀመረ አስታውሳለሁ።

የአውራጃው ተወላጅ የሆኑት ሱማሌዎች ልጆቻቸውን ወደ ተማሪ ቤት እንዲያስገቡና ከሌሎች ልጆች ጋራ አብረው እንዲማሩ ብርቱ ጥረት አድርገን ነበር። ስለዚህም ባለፈው ዘመን በትምህርት ከነበሩት ከ143 ተማሪዎች ውስጥ ዓሥሩ የሱማሌዎች ልጆች ነበሩ። ወደፊትም ቊጥራቸው እንደሚጨምር ተስፋ አድርገናል።

የቀሩት ተማሪዎች አብዛኞቹ ከልዩ ልዩ ሥፍራ መጥተው በመንግሥት አገልግሎት ላይ ያሉ የወታደሮችና የሠራተኞች ልጆች ሲሆኑ ጥቂቶቹም የነጋዴዎችና የገበሬዎች ልጆች ናቸው:: በዚያ ዘመን የትምህርት ፍላጎት ስለ ተነሣሣ የትጋት መንፈስ በተማሪዎች ዘንድ ነበረ:: ሆኖም በወታደሮቹ ልጆች በኩል ትምህርትን የሚያደናቅፍ ችግር በአንዳንዶች ላይ ሲደርስ ታይቷል:: ምክንያቱም የልጆቹ ወላጆች (ወታደሮች) ለሥራም ሆነ ለዘመቻ ታዝዘው ሲሄዱ ወይም ሲሞቱ ወጣቶች በኑሮአቸው በኩል ይቸገሩ ስለነበረ ነው:: ለምሳሌም በቅርብ ጊዜ ውስጥ የተደረገውን የአንዱን ወጣት ችግር እዚህ ላይ ለመጥቀስ ምክንያት አግኝቻለሁ::

ታዬ ወልደ ጻድቅ የተባለ የ7 ዓመት ዕድሜ ልጅ ነበረ:: አባቱ ወታደር ወልደ ጻድቅ ባለፈው ዓመት ለሥራ ፍለጋ ከጨርጨር ወደ ጅጅጋ ሲመጣ ልጁን ይወዳልና ከእናቱ ነጥሎ ይዞት መጥቶ በወታደርነት ተቀጠረ:: ልጁም እንዲማርለት ወደ ልዑል ራስ መኮንን ትምህርት ቤት አስገብቶት ይማር ጀመር:: ወታደር ወልደ ጻድቅ ባለፈው ኅዳር ወደ ውጋዴን ጠረፍ ለጸጥታ ጥበቃ ታዝዞ ሲሄድ ከወር ቀለቡ እየተቀነሰ ለልጁ እንዲሰጥለት ለአለቆቹ አስታውቆ አገባጠመውና ጅጅጋ ላይ ትቶት ዘመተ:: ሁለት ወር ያህል እንደቈየ ወታደር ወልደ ጻድቅ ከሱማሌ ጋር ሲዋጋ ሞተ:: ከዚያ በኋላ የወር ቀለቡ ስለ ተቋረጠ ወጣቱ ታዬ ወልደ ጻድቅ በችግር ላይ ወደቀ:: በዚህ ጊዜ አስተማሪዎቹ እነ አቶ ሞሲሳ ራባና እነ አቶ ኃይለ መስቀል አዝነውለት በየተራ መብል እየሰጡት ቀን ሲማር ይውል ጀመር:: ነገር ግን የሚያድርበት ሥፍራ ቸግሮት ኖሮ ቀን ሲማር በዋለበት ክፍል ውስጥ ሌሊት ገብቶ እንደሚያድር አስተማሪዎቹ ተመለከቱ:: ይህንኑም ከኀዘን ጋር ስላስታወቁኝ ልቤ ተነካና ወድያው ወደቤቴ ሄጄ ለባለቤቴ አማከርኋት:: እርስዋም በጣም አዝና "ግድ የለም ለነፍሳችን ይሆነናልና ወደ ቤታችን ያምጡት! ከልጆቻችን ጋር እየተማረ አብሮ ያድጋል" ብላ ስለመለሰችልኝ ታዬ ወልደ ጻድቅ ከቤታችን ገብቶ ከዚያ ቀን ጀምሮ ቤተሰባችን ሆነ:: ይህ ወጣት አድጎ ቤት ንብረት ለመያዝ የበቃ ስለሆነ ስለ ሁናቴው ወደፊት ከሥፍራውና ከጊዜው ላይ ስደርስ ስለ እርሱ እንደምጽፍ ተስፋ አደርጋለሁ::[198]

## ስለ ሕገ መንግሥት በዓል

በዚህ ዓመት ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም. ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ላይ ታላቅ በዓል አድርገው ለመጀመሪያ ጊዜ ሕገ መንግሥት ለሕዝብ መስጠታቸው እየተጋነነ ይነገር ነበር:: ይኸውም ለያገሩ በቴሌግራም ተላልፎ በዓል

[198] ታዬ ወልደ ጻድቅ ከጠላት ወረራ በኋላ ሥራ ይዞ፣ ሚስት አግብቶ ይኖር ነበር:: በወጣትነት ዕድሜው በሕመም ምክንያት ሞቷል::



ተደርጎበታል:: የሕገ መንግሥቱን ጽሑፍ በሌላ ጊዜ አግኝቼ ዝርዝሩን ተመልክቼዋለሁ:: በስድስት ምዕራፎች የተከፈለና 55 አንቀጾች ያሉበት ነው::

አዲስ አበባ ላይ የተከበረው የሕገ መንግሥት በዓል በከፍተኛ ደረጃ ሥነ ሥርዓት እንደ ነበረ በጋዜጣና በሌላም ጽሑፍ ስለ ተመለከትሁ ታሪኩን ቀርጾ ለማቈየት ስል ከጽሑፎች በማንበብና በሥፍራው የነበሩትን በመጠየቅ በዝርዝር በማስታወሻ አስቀመጥሁት:: እርሱም *የዘመን ታሪክ* በተባለው በሌላው ክፍል የሚገኝ ነው[199]::

የሕገ መንግሥት በዓል በተከበረበት ሰሞን የሐረር ጉምሩክ ሹም ባላምባራስ እሸቴ ተክተለው የጅጅጋ ዲሬክተር ሆነው ተሾመው ሐምሌ 12 ቀን ወደ ጅጅጋ መጡ:: በሐምሌ 18 ቀን ትምህርት ቤታችንን ጐብኝተው 45 የትምህርት መጻሕፍት በእርዳታ መስጠታቸውንም አስታውሳለሁ::

## ስለ ውጋዴን

ውጋዴን ከጅጅጋ አውራጃ በስተ ደቡብ የሚገኝና የግዛቱ ታላቅ ክፍል የሆነ ሰፊ አገር ነው:: የሐረር እንደራሴ ደጃዝማች ገብረ ማርያም ጋሪ በሐምሌ ወር ኢጋማሽ ላይ ወደ ውጋዴን ወርደው ዋና ዋና ሥራ ሲያቋቁሙ መክረማቸውን ሰማን:: ይህም እንደሚከተለው ነው::

አገሩን በየወረዳ እየከፈሉ 12 ከተሞች አቋቋሙበት:: በየከተሞቹም ጸጥታ ጠባቂ ወታደርና አስተዳዳሪ ሹም እየመደቡ አስቀመጡባቸው:: የተቋቋሙት ከተሞች ስም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሲሆን ለአንዳንዶቹ አዲስ ስም አወጡላቸው:: ይኸውም እንደሚከተለው ነው::

1. ኤል ጉበያ:: አሁን ጎረቤት ብለውታል::
2. ፊቅ
3. ገላልቻ
4. ወረሂርሴ
5. ደጋሃመዶ:: አሁን ታመነ ብለውታል::
6. በለምበል
7. ጣናን
8. ሳሰበኔ
9. ቆራሄ:: አሁን እርጎ ብለውታል::
10. ቀልቀሎ
11. ቡስሌ:: አሁን ፋሲካ ብለውታል::
12. ጀድሌ:: አሁን መትረየስ በር ብለውታል::

[199] በትርቡ የሚታተመው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ክፊል የዘመን ታሪክ::

ስያሜ ስለተሰጠበት ስለ ቃሉ ትርጓሜም የሰማሁት እንደሚከተለው ነው:: «ጎረቤት» መባሉ ለሐረር የሚቀርብ በመሆኑ፤ «እርጎ» መባሉ እየሩ ጥሩ በመሆኑ፤ «ፋሲካ» መባሉ በምቾት የሰነበቱበት በመሆኑ፤ «መትረየስ በር» መባሉ ኢጣልያኖች ወሰን ገፍተዋል በሚባልበት ክፍል ስለሚገኝ ክርክር ያለበት በመሆኑ ነው ተብሎ ተነግሮኛል::




3 ውጋዴን



ደጃዝማች ገብረ ማርያም ከተሞችን ከአቋቋሙ በኋላ አንዱን ከሌላው ጋራ ለማገናኘት እንዲቻል መንገዱን እያስቀየሱ ሲያስጠርጉና በትጋት ሲያሠሩ ክረምቱን በውጋዴን ከአሳለፉ በኋላ በመስከረም ጅጅጋን ጉብኝተዋል::

በዚህ ዓመት የመኪና መንገዶች ሥራ በትጋት ስለታያዘ ከድሬዳዋ እስከ ሐረር የመኪና መንገድ ተሠርቶ ወደ ሐረር መኪና ገብቷል:: እንዲሁም ደግሞ ከሐረር ወደ ጅጅጋ የመኪና መንገድ ተጀምሮ በሥራ ላይ ይገኛል::

## ስለ ልዩ ልዩ ነገር

በጅጅጋ ከተማ የሴቶች ትምህርት ቤት እንዲከፈት መፈቀዱን በመግለጽ አገር ገዥው ትእዛዝ ስለ ሰጡ ጥቅምት 2 ቀን 1922 ዓ.ም. ቅዳሜ ሥነ በዓል ተደርጎ ትምህርት ቤቱ ተከፈተ:: እርሱም በንጉሠ ነገሥቱ እናት በልዕልት የሺ እመቤት ስም ተሰየመና ልጃገረዶች ገብተው ይማሩበት ጀመር:: ትምህርቱ ለጊዜው የአማርኛ ንባብና ጽሕፈት ብቻ ስለሆነ መምሬ መኩሪያ የተባሉ ሽማግሌ ቄስ ተቀጥረው ማስተማር ጀመሩ:: ወደፊት ግን እንደ ስፌትና ጥልፍ የመሰለውን የሞያ ሥራ የምታስተምር ሴት እንድትቀጠር ታስቦበት ቈይቷል::

የልዕልት የሺ እመቤት ትምህርት ቤት የሥራው አመራር የሚካሄደው ከልዑል ራስ መኰንን ትምህርት ቤት ጋራ በአንድነት ተቀላቅሎ ስለሆነ በአስተዳደር በኩል ልዩ አቋም አልነበረውም::

አገረ ገዥው ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል በንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ በዓል ቀን ከሥፍራው ለመገኘት ጥቅምት 3 ቀን 1923 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ ስለ ወጡ የግዛቱ አስተዳደር በዋናው ጸሐፊ በአቶ ብሩ ሀብተ ዮሐንስ ጠባቂነት የሚካሄድ ሆነ::

የጅጅጋ ዲሬክተር የነበረው ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ ባለፈው ዓመት በኅዳር ወር ወደ አዲስ አበባ እንደ ወጣ አልተመለሰም ነበር:: በዚህ ዓመትም በመስከረም 18 ቀን የጨርጨርን ዲሬክተርነት ስለ ተሾመ ጅጅጋን መልቀቁ ተረጋግጦ ነበርና እኔ በተጠባባቂነት እንዳስተዳድር የታዘዝኩት ይህ ከታወቀ በኋላ ነበር::

የጅጅጋ ማዘጋጃ ቤት ሹም አቶ መዓዛ ወልደ ሕይወትም ፈቃድ አግኝቶ ከአገረ ገዥው ጋር ወደ አዲስ አበባ ስለ ወጣ እኔ ለጊዜው በወኪልነት እንድሠራ ታዘዤ በተጨማሪ በማዘጋጃ ቤት እሠራ ጀመር::

ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ጅጅጋ ላይ በቆዩበት ጊዜያት የአገሩን የንግድና የሥራ እንቅስቃሴ ለማነቃቃት በትጋት ሠርተዋል:: ከጅጅጋ እስከ ገርቢሐድሌ ድረስ ያለውን ርዝመቱ 75 ኪሎ ሜትር ያህል የሆነውን የመኪና መንገድ ባለፈው ዓመት አስጠርገው ስለ ከፈቱ የንግድ ዕቃዎች ከእንግሊዝ

ሱማሌላንድ ከበርበራና ከሐርጌሣ በመኪና እየመጡ የንግድ ሥራ ተከፍቶ ነበር። እንዲሁ ደግሞ በአገር ውስጥ በጅጅጋ እስከ ደጋሃቡር ድረስ ያለው 180 ኪሎ ሜትር ያህል የሚሆነው የመኪና መንገድ የተጠረገውና የስልክ መስመር የተዘረጋው በፊታውራሪ ታፈሰ ትጋት ነበር። በነዚህ ምክንያቶች ሁሉ ሕዝቡ ስማቸውን በምስጋና ሲያነሣው እንደ ነበረ አስታውሳለሁ።



12 የታሪኩ ጸሐፊ በሥራቸው ላይ የጅጅጋ ዲሬክተርነትን የተሸሙበት

እንግዲህ በጅጅጋና በወሰን ክልል ሥራ ሳለሁ በፈጸምሁት አገልግሎት የማስታውሰውን የራሴን ታሪክ እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደፊት ለመቀጠል ተስፋ አደርጋለሁ[200]።

ስለራሴ የማስታውሰው በእግዚአብሔር ፈቃድ እነሆ ደረሰ ተፈጸመ። ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው።

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ።

[200] በወሰን ክልል ሥራ የፈጸሙት አገልግሎትና የወሰን ክልል ስራ ታሪክ ወደፊት የሚታተመው የመርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፊል የዘመን ታሪክ ውስጥ ይገኛል።

# ምዕራፍ 31

## ማሳረጊያ

(በመጽሐፉ አዘጋጅ በአምኃ መርስዔ ኀዘን የተጻፈ።)

የመርስዔ ኀዘን ታሪክ 1923 ዓ.ም. ላይ ይቆማል። የእግዚአብሔር ፈቃድ አልሆነም፤ ከዚያን በኋላ ያለውን ታሪካቸውን መርስዔ ኀዘን በመጽሐፍ መልክ አላዘጋጁትም። አንባቢው ከ1924 ዓ.ም. በኋላ የነበረው የመርስዔ ኀዘን ሕይወት ምን ይመስል እንደነበር ለማወቅ ይፈልጋል ብዬ ስለገመትሁ እነሆ ከዚያ በኋላ ያለውን ታሪካቸውን በአጭሩ አቀርቤአለሁ። ዝርዝር ታሪኩን ከዘመኑ ታሪክ ጋር በማዛመድ በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደፊት የምጽፈው ይሆናል።

### ከጠላት ወረራ በፊት

በ1924 ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር አቶ መርስዔ ኀዘን የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ሱማሌላንድ የወሰን ክልል ኮሚሽን ዋና ጸሐፊ ሆኑ። በዚህም ሥራ ኮሚሽኑ ሥራውን እስካብቃበት እስከ 1927 ዓ.ም. የካቲት ድረስ ሦስት ዓመት ከሁለት ወር አገልግለዋል።

ኢጣልያኖች በውጋዴን ውስጥ ወልወል ላይ ኅዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም. ረብሻ አደጋ በጣሉ ጊዜ አቶ መርስዔ ኀዘን በስፍራው ላይ ነበሩ፤ ከወሰን ተካላዮቹ ጋር ሆነውም በውጊያው ላይ ተሳትፈዋል፤ የግጭቱንም ዝርዝር ታሪክ መዝግበውታል። ይኸውም ታሪክ በቅርቡ የሚታተመው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፊል የዘመን ታሪክ ውስጥ ይካተታል።

በ1927 ዓ.ም. ሰኔ 10 ቀን አዲስ አበባ የትልቁ ወህኒ ቤት ዲሬክተር ሆነው ተሾመው እስከ ጦርነቱ መጀመሪያ ድረስ አገልግለዋል።

### የጠላት ወረራ ዘመን

መርስዔ ኀዘን አምስቱን የጠላት ወረራ ዘመናት በአዲስ ዓለም፣ በጅሩና በአድአ በሌላም ስፍራ እየተዘዋወሩ ሕይወታቸውን አትርፈዋል። በዚያን የመከራ ዘመን አብዛኞቹን መጻሕፍታቸውን ለማዳን ባይችሉም የተወሰኑ ሰነዶችና መጻሕፍትን ከዝርፊያ በማዳናቸው ለታሪካቸው መሠረት ለትውልድም ቅርስ ሆነዋል። አንዳንዶቹንም መጻሕፍትና ጽሑፎቻቸውን ተማሪዎቻቸውና ወዳጆቻቸው ከመጥፋት አድነውላቸዋል። ለምሳሌ ያህል

የሰዋስው ጽሑፋቸውን ቅጂ አቦሴ ዱፌራ የተባለ ተማሪያቸው አስቀምጦት የነበረውን በ1934 ዓ.ም. ሰጥቷቸዋል።

## ከጠላት ወረራ በኋላ የመንግሥት ሥራ አገልግሎት

ከጠላት ወረራ በኋላ የተሰማሩባቸው የሥራ ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው።

| | |
|---|---|
| የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ | 1933 - 36 ዓ.ም. |
| የጋዜጣና ማስታወቂያ ጽሕፈት ቤት ዋና ዲሬክተር | 1936 ዓ.ም. |
| የታሪክና የቤተ መንግሥት ዜና ማሰናጃ ጽሕፈት ቤት ዲሬክተር | 1936 - 46 ዓ.ም. |
| የብላታ ማዕርግ ሲያዝያ | 1936 ዓ.ም. |
| የፍርድ ሚኒስቴር ም/ሚኒስትር | 1941 - 50 ዓ.ም. |
| የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ዓቃቤ ጉባኤ | 1950 - 54 ዓ.ም. |
| የሕግ መወሰኛ ም/ቤት አባልና የሕግ ኮሚቴ ሊቀ መንበር | 1950 - 63 ዓ.ም. |
| የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ም/ፕሬዜዳንት | 1954፣ 56፣ 60 - 61 ዓ.ም. |
| የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ተጠባባቂ ፕሬዜዳንት | 1960 ዓ.ም. |
| የታሪካዊ ቅርሶች አስተዳደር አማካሪ | 1963 - 66 ዓ.ም. |

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በመደበኛ ሥራቸው ላይ ደርበው የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሹም ሆነው ለ14 ዓመታት፣ የሕዝብ ጤና ሚኒስቴር ተጠባባቂ ሹም ሆነው ለአንድ ዓመት ሠርተዋል።

እንዲሁም በአያሌ ቦርዶች በአባልነትና በሊቀ መንበርነት አገልግለዋል። ከነኚህም ዋኖቹ የሚከተሉት ናቸው። የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ቦርድ ሊቀ መንበር፣ 1946-54 ዓ.ም.፤ የትምህርትና የሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ቦርድ አባል፣ 1940 - 54 ዓ.ም.፤ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ቦርድ አባልና ምክትል ሊቀ መንበር፣ 1942 - 66 ዓ.ም.፤ የወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር (ወ.ወ.ክ.ማ) ቦርድ አባልና ምክትል ፕሬዜዳንት 1941 - 1966 ዓ.ም.።

## በልዩ ትእዛዝ የፈጸሟቸው አገልግሎቶች

ብላታ ከመደበኛ ሥራቸው ደርበው አያሌ ልዩ ልዩ ሥራዎችን እየታዘዙ አከናውነዋል። ከነኚህም ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

_የኢትዮጵያና የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ድርድር_

ኅዳር 1 ቀን 1940 ዓ.ም. ብላታ መርስዔ ኀዘን ኢትዮጵያ የራሷን ፓትሪያርክ እንድትሾም በኢትዮጵያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያናት መካከል በሚደረገው ድርድር ተካፋይ እንዲሆኑ ተመረጡ። ብላታ መርስዔ ኀዘን እስከ ድርድሩ ፍጻሜና የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ፣ የአቡነ ባስልዮስ



ሢመት እስኪፈጸም ድረስ ተሳታፊ ሆነው አገልግለዋል። ዝርዝር ታሪኩንም «ሢመተ ሊቀ ጳጳሳት ኢትዮጵያዊ» እና «የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትሪያርክ» በሚል ርእስ ባዘጋጇቸው መጻሕፍት ጽፈውታል።

_የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ማረም ኮሚቴ_

የካቲት 27 ቀን 1939 ዓ.ም. የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ማረም ኮሚቴ ሊቀ መንበር ሆኑ። ለዚህ ሥራ ተመርጠውና ታዝዘው በልዩ ልዩ ጊዜ የሥራ ተባባሪ የሆኑት ሊቃውንት ብዙ ነበሩ ። ነገር ግን እስከ ሥራው መጨረሻ ድረስ ምንም ሳይለዩ ሥራውን በመቀጠል ላይ የነበሩት፤ በብሉይ ኪዳን ክፍል ሚስተር ግራሃምና ብላታ መርስዔ ኀዘን፤ በሐዲስ ኪዳን ክፍል ቀሰ ማቲውና አቶ አርአያ ሥላሴ ወርቃ ነበሩ። የተሻሻለው የአማርኛ ሐዲስ ኪዳን በብርሃንና ሰላም ማታሚያ ቤት በ1947 ዓ.ም.፤ ጠቅላላው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ (ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን) ሐምሌ 16 ቀን 1952 ዓ.ም. በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታትሞ ወጥቷል።

_የፍትሐ ነገሥት ኮሚሲዮን_

መጋቢት 17 ቀን 1946 ዓ.ም. በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትእዛዝ የፍትሐ ነገሥት ኮሚሲዮን (የኮዲፊኬሽን ኮሚሲዮን) ሲቋቋም የኮሚሲዮኑ ፕሬዜዳንት የጽሕፈትና የፍርድ ሚኒስትሩ ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ነበሩ። በኋላ ግን የኮሚሲዮኑ ሊቀ መንበር የፍርድ ምክትል ሚኒስትሩ ብላታ መርስዔ ኀዘን ሆነው ነበር። የኮሚሲዮኑ አባላት ሦስት የታወቁ የአውሮጳ የሕግ ፕሮፌሰሮችና የበሰለ የባህልና የሕግ ዕውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ነበሩ።

የኮሚሲዮኑ ዓላማ በፍትሐ ነገሥትና በኢትዮጵያ የነበሩትን ልማዶችና ባህሎችን መሠረት በማድረግ የወንጀል፣ የፍትሐ ብሔር፣ የንግድና የባሕር ሕጎችን ማዘጋጀት ነበር። የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በ1949 ዓ.ም.፣ የፍትሐ ብሔር ሕግ በ1952 ዓ.ም. የንግድና የባሕር ሕጎች በ1953 ዓ.ም. በፓርላማ ጸድቀው ንጉሠ ነገሥቱም አጽድቀዋቸው ሕግ ሆነው ወጥተዋል። እነኚህ ሕጎች እስካሁን በመሠረቱ እልተቀየሩም፤ ከአንዳንድ ማሻሻያዎች በስተቀር አሁንም በኢትዮጵያም በኤርትራም እየተሠራባቸው ናቸው።

_መጽሐፈ ቅዳሴ_

በ1918 ዓ.ም. 14ቱ መጽሐፈ ቅዳሴ ታትሞ ወጥቶ ነበር። በ1942 ዓ.ም. የወጣውን መጽሐፈ ቅዳሴ ያዘጋጁት ብላታ መርስዔ ኀዘን ናቸው። በ1942 ዓ.ም. ተሻሽሎ የታተመው መጽሐፈ ቅዳሴ ውስጥ ሊጠን፣ መስተብቍዕና ዘይነግሥ ተጨምረውበታል። እንዲሁም የግዕዝና የአማርኛው አካሄድ እንዲስማማ ተደርጎ ቀርቧል፣ ለያንዳንዱ ቅዳሴ ተራ ቍጥርም ለኃይለ ቃሉ እንዲስማማ ሆኖ ተከፋፍሏል።

አላታሚው ግርማዊት እቴጌ መነን ሲሆኑ የመጽሐፉን መቅድም የጻፉት ብላታ መርስዔ ኀዘን ናቸው። ከመጽሐፉ ሽያጭ የሚገኘው ጥቅም የኢጣልያ ጦር በ1929 ዓ.ም. ሕፃዋን (ጃንደረባ) ላደረጋቸው ድኾች ልጆች ለሚያድጉበት መንፈሳዊ ትምህርት ቤት እንዲሰጥ ተደርጎ ነበር።

*<u>የፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜ ሥራ</u>*

በ1960 ዓ.ም. የፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜ የሚሠራ ኮሚቴ ተቋቋመ። የኮሚቴው ሰብሳቢ ብላታ መርስዔ ኀዘን ሲሆኑ፤ አባላቱ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (በኋላ አቡነ መልከ ጼዴቅ)፣ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፣ መልአከ ሰላም ሳሙኤልና መልአከ ብርሃን አድማሱ ነበሩ። ሥራው አንድ ዓመት ተኩል ወስዶ በ1962 ዓ.ም. ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታትሞ ወጥቷል።

*የአማርኛ መርሐ ልሳን*

ሰኔ 20 ቀን 1964 ዓ.ም. የአማርኛ መርሐ ልሳን (አካዳሚ) ሲቋቋም ብላታ መርስዔ ኀዘን አባል ሆነው ተመረጡ። የመርሐ ልሳኑ ዓላማ የመንግሥቱን ቋንቋ አማርኛን ማዳበርና የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ እንዲስፋፋ ማበረታታት ነበር። ጡረታ እስከወጡበት ዘመን ድረስ በመርሐ ልሳኑ አባልነት አገልግለዋል።

## የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ሽልማት

በ1964 ዓ.ም. ብላታ መርስዔ ኀዘን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ሽልማት ተሸላሚ ሆኑ። ድርጅቱ ስለ ብላታ መርስዔ ኀዘን ሥራዎች የሚከተለውን መግለጫ አውጥቶ ነበር።

> . . . በተለይም የአማርኛን ሰዋስው በዘመኑ አውሮጳዊ አቀራረብ ተመሳሳዩን ቃል አሳክተው አዋጁን አስማምተው የደረሱት መጽሐፍ ሦስት የተማሪዎች ትውልድ የተቀባበለው ሲሆን እነሆ እስከ ዛሬ በ1ኛ በ2ኛ ደረጃ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ማስተማሪያ ነው።
>
> በሐቅና በጥንቃቄ የተዘጋጀ የዘመናቸው ታሪክና የሕይወታቸው ትዝታ በተጣራ አማርኛ ተጽፈው ይገኛሉ። ታትመው በቅርቡ ጊዜ የማወቅና የማስታወስ ንዳድ ለሄሮዶቱስ ብቻ የተሰጠ ጸጋ አለመሆኑን አንባቢ ሊገነዘበው ይችላል።
>
> ስለዚህ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት በተርጓሚነት፣ በአዘጋጂነትና ይልቁንም በደራሲነት ቍጥራቸው ከ36 በላይ የሆኑ መጻሕፍት በእርሳቸው አማካይነት የታተመ መሆኑ ለታወቀላቸውና የአማርኛን ቋንቋ ከዘመናዊ ከኪነታዊ አነጋገር በማስማማት ከሁሉም የተሻለ አገልግሎት ላበረከቱ ለክቡር ብላታ መርስዔ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ የ1964 ዓ.ም. የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ሽልማት የወርቅ ኒሻንና የምስክር ወረቀት ከ10 ሺህ የኢት. ብር ጋር እንዲሰጣቸው በሙሉ ድምጽ ኮሚቴው ወስኗል። . . .





44 የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ሽልማት ሲቀበሉ። ከግራ ወደ ቀኝ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ፣ ብላታ መርስዔ ኀዘን



45 ብላታ መርስዔ ኀዘን ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር ሲነጋገሩ። በመሃል የሚታዩት ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ ናቸው



በገጽ 227 ቍጥር 45 የሚገኘውን ፎቶግራፍ ያገኘሁት የካቲት ወር 2001 ዓ.ም. ከልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ ነው ። ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ "ይህ ፎቶግራፍ ከቤተ መንግሥታችን ሰዎች አድነው፣ አስቀምጠው ወደ ኢትዮጵያ ስመለስ የሰጡኝ ነው። ለአንተ ለልጃቸው መስጠት እወዳለሁ" ብለው ያበረከቱልኝ ነው። በዚህ አጋጣሚ ለልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ ያለኝን ታላቅ አክብሮትና ምስጋናዬን ለመግለጽ እወዳለሁ።

### የወይዘሮ እታገኘሁ ዕረፍት

ግንቦት 17 ቀን 1965 ዓ.ም. የብላታ መርስዔ ኀዘን ባለቤት ወይዘሮ እታገኘሁ ባዬ በመኪና አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሥርዓተ ቀብራቸውም ግንቦት 18 ቀን 1965 ዓ.ም. ንጉሣውያን ቤተሰብ በተገኙበት በአዲስ አበባ አቦ መካነ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ።

የ50 ዓመት ያህል የትዳር ጓደኛቸውን፣ አሳቢያቸውን ማጣት ለብላታ መሪር ኀዘን አድርሶባቸው ነበር።

### ጡረታ

ብላታ መርስዔ ኀዘን በ1966 ዓ.ም ጡረታ ወጡ። ከጠላት ወረራ በፊት 16 ዓመት ከ4 ወር ከጠላት ወረራ በኋላ 32 ዓመት ከ10 ወር በድምሩ 49 ዓመት ከ2 ወር በቅንነትና በታማኝነት ሀገራቸውንና መንግሥታቸውን አገልግለዋል።

### አብዮት

በ1966 ዓ.ም. አብዮቱ ተጀመረ። በአብዮቱ የብላታ መርስዔ ኀዘን የቅርብ ወዳጅ ደጃዝማች ክፍሌ ዕርገቱ ሌሎችም ካለ ፍርድ ታሰሩ፣ በኋላም በግፍ ተገደሉ። ሌሎችም ብዙዎች ወዳጆቻቸው፣ ልጃቸው ውብሸት መርስዔ ኀዘንም ጭምር ለእስራት ተዳረጉ።

በትምህርት ያነጿቸው የኢትዮጵያ ወጣቶች በቀይ ሽብርና በነጭ ሽብር በሺዎች ረገፉ። ብላታ የተማሩ የኢትዮጵያ ወጣቶችን እልቂት ለሁለተኛ ጊዜ ማየታቸው ሆነ። የመጀመሪያው በ1929 ዓ.ም. የካቲት 12 ቀን በግራዚያኒ ላይ የቦምብ አደጋ በተጣለ ጊዜ ግራዚያኒ ለብቀላ ወጣት ኢትዮጵያውያንንና ሌሎችንም ዜጎችን የፈጀበት ጊዜ ነበር። በዚያን ጊዜ የብላታ ዘመድ የመምህር ራስ ወርቅ ልጅ፣ ሻለቃ ዮሐንስ ራስ ወርቅ፣ ከተገደሉት ወጣቶች አንዱ ነበር። በአብዮቱም የብላታ መርስዔ ኀዘን እኅት፣ የወይዘሮ ፊትለ ወርቅ፣ የልጅ ልጆች ልብሰ ወርቅ ሽፈራውና ጫንያለው ካሣ ለሞት ተዳርገዋል።





46 ብላታ መርስዔ ኀዘን ከመጽሐፉ አዘጋጅ ከልጃቸው ከአምኃ ጋር 1962 ዓ.ም.

እንዲሁም ለሃምሳ ዓመታት ያህል ያገለገሏት ኢትዮጵያ ለክፉ አደጋ ተጋልጣለች። የሶማሌው ጦር የኢትዮጵያን ድንበር ጥሶ ገብቶ ጅጅጋን ይዟል፣ ሐረርና ድሬዳዋ ተከበዋል።

የብላታ መርስዔ ኀዘን የሕይወት ዘመናቸው መጨረሻ ይህን ይመስል ነበር። ብላታ መርስዔ ኀዘን ስለዚያን ዘመን በጽሑፍ የተዉልን አንዳችም ማስታወሻ የለም። እኔም በዚያን ጊዜ ለትምህርት አሜሪካ ስለነበርሁ ልጠይቃቸውና ስሜታቸውን ለመረዳት ዕድል አላገኘሁም። በአጠቃላይ በሀገራችንና በሕዝባችን ላይ የደረሰው መከራ ሳያሳስባቸውና በብርቱ ሳያሳዝናቸው እንዳልቀረ እገምታለሁ።

## የአማርኛ ሰዋስው 50ኛ ዓመት

ጥቅምት 1969 ዓ.ም. - ብላታ መርስዔ ኀዘን 78 ዓመት ዕድሜ ደርሰዋል:: ጡረታ ከወጡም ሦስት ዓመት ሆኗቸዋል:: ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት አስተማሪ በነበሩበት ጊዜ ያዘጋጁት የአማርኛ ሰዋስውም 50 ዓመት ሞልቷታል:: በዓሉን ለማክበር ዶክቶር ሥርግው ሀብለ ሥላሴ በቤተ መጻሕፍት ወመዘክር አንድ ዝግጅት አዘጋጅተው ነበር:: ዶክቶር ሥርግው ለብላታ ቅርብ ከመሆናቸውም በላይ በሙያቸውና በችሎታቸው ከሚያደንቁዋቸው ወጣት ምሁራን አንዱ ነበሩ::

ብላታ መርስዔ ኀዘን በዝግጅቱ ላይ ያደረጉት ንግግር ከዚህ በታች ቀርቧል::

*የተወደዳችሁ ወንድሞችና እኅት*

*በዚህ ሰዓት ይህ ስብሰባ የተደረገበትን ምክንያት እንድገልጽ ፈቃዳችሁ ይሆን ዘንድ እየጠየቅሁ አጭር ቃል እናገራለሁ::*

*ከፊታችን ተዘርግቶ የምናየው ይህ የአማርኛ ሰዋስው በሥራ ላይ ውሎ አገልግሎት የጀመረው የዛሬ አምሳ ዓመት በ1919 ዓ.ም. ነበር:: ዕለቱም የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ልክ በዛሬው ዕለት ነበር::*

*እኔም በዚያ ጊዜ (ማለት እርሱን በጻፍሁበት ጊዜ) የ28 ዓመት ጕልማሳ ነበርሁ:: ዛሬ ግን እንደ እርሱ አምሳ ዓመት ጨምሬበት እነሆ አብረን እንገኛለን:: ይህን ያደረገ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን::*

*ስለ ሰዋስው በምናገርበት ጊዜ የቀድሞዎቹን አባቶች ምስጋና ሳላወሳ እንዳላልፍ ሕሊናዬ ያስገድደኛል:: የትምህርቱ መሥራቾች የሆኑት አባቶች ይህን ትምህርት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፉ የኖሩት፤ ረኀቡንና ጽምዑን ችለው፣ እየተቸገሩ ተምረው ነው:: እንዲሁ ደግሞ ትምህርቱን ያለምንም ዋጋ በነፃ እየሰጡ እነሆ አቈይተውልናል:: ዛሬ እኛ ባለሞያ መስለን የምንታየውም እነርሱ በመሠረቱት ላይ አንዳንድ የአሠራር መልክ በመስጠት ብቻ ስለ ሠራን ነው:: ይኸውም «ነቢያት በመደመዱ ሐዋርያት ገደገዱ» እንደሚባለው ሆኖ ነው እንጂ፤ የጥበቡ ምንጭና መሠረት አባቶቻችን ናቸው:: ስለዚህ ለእግዚአብሔር የባሕርዩን ምሥጋና በማቅረብ ለአባቶቻችንም የጸጋ ምስጋናን በመስጠት ንግግሬን እወስናለሁ::*

*ደግሞም ይህን ዕለት ምክንያት በማድረግ የዛሬ አምሳ ዓመት በመጀመሪያው ዕለት በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት የነበሩትን የሰዋስው ተማሪዎች ሁሉ በናፍቆት አስታውሳቸዋለሁ:: በዛሬው ጊዜ በሕይወት ለሚገኙትም ያንኑ የሚያውቁትን የአማርኛ ሰዋስው ለያንዳንዳቸው ለመላክ እነሆ አዘጋጅቻለሁ:: ይህን ሰዋስው በዓል ለመሳተፍ ከዚህ የተገኛችሁት እናንተም ለመታሰቢያ ያቀረብሁላችሁን እንድትቀበሉልኝ እለምናለሁ::*

*በመጨረሻም ዶክተር ሥርግው ሀብለ ሥላሴ ይህን የሻይ ግብዣ በበጎ ፍቃድ አዘጋጅተው እንድንሰበሰብና እንድንገናኝ ዕድል ስለ ሰጡን ከልብ አመሰግናቸዋለሁ::*

*ጥቅምት 1969 ዓ.ም.*

*እግዚአብሔር ይስጥልኝ*



## ፍጻሜ

ጥቅምት 19 ቀን 1971 ዓ.ም. ብላታ መርስዔ ኀዘን የቀኑን ሥራቸውን ጨርሰው ወደ መኝታቸው ሄዱ:: ከዚያም በተኙበት በ79 ዓመታቸው ካለ ምንም ጻዕር ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ሥርዓተ ቀብራቸው ጥቅምት 21 ቀን 1971 ዓ.ም. በአዲስ አበባ አቦ መካነ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ::

ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ከባለቤታቸው ከወይዘሮ አታገኘሁ ባዩ የሚከተሉትን ልጆች አፍርተዋል፤ ገብረ ክርስቶስ፣ ውብሸት፣ ሮማን፣ ቅድስት፣ አልማዝና አምኃ:: እንዲሁም ብላታ መርስዔ ኀዘን አንዲት ሴት ልጅ መክሊትን ወልደዋል::



47 የወይዘሮ አታገኘሁና የብላታ መርስዔ ኀዘን የቤተሰብ መካነ መቃብር

ተፈጸመ::

ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን::

# አባሪ ሀ

## የትውልድ ሐረግ



የደብርቼን የትውልድ ሐረግ በከፊል የሚያሳይ

## ቄስ ደፈር ከሞረት ጥዱ የሚዛመድበት የትውልድ ዘርፍ







የመርስዔ ኀዘን የእናታቸው የትውልድ ሐረግ (የግንድ አባቱ አዲሱ)

## የወይዘሮ እታገኘሁ የትውልድ ሐረግ በእናታቸው በኩል






## የወይዘሮ እታገኘሁ የትውልድ ሐረግ በአባታቸው በኩል



## አባሪ ለ

# የቤተ ክህነት ትምህርት መግለጫ

### ለብሔራዊ ትምህርት ኮሚሺን የቀረበ

የቤተ ክህነት ትምህርት እንዴት እንደነበረ ወይም ምን ዓይነት እንደሆነ ከአባሎች መካከል ለማወቅ ስለፈለጉና ስለጠየቁ፤ ቀጥሎ ያለውን አጭር መግለጫ እናቀርባለን።

### ስለ ትምህርቱ ዓይነት

የትምህርቱ ዓይነት በአራት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል። ይኸውም፣ «የንባብ ትምህርት፤ የዜማ ትምህርት፤ የቅኔ ትምህርት፤ የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት» ነው።

### አንደኛ፣ የንባብ ትምህርት

የንባብ ትምህርት ከፊደል አንሥቶ ዳዊት እስከ መድገም ድረስ የሚሰጠው ትምህርት ነው። ተማሪው ፊደላትን ለይቶ ካወቀ በኋላ ወደ ፊደለ ሐዋርያ ይተላለፋል። በዚህ ጊዜ ፊደላት ተገጣጥመው እንዴት ቃላት እንደሚሆኑና እንዴትስ እንደሚነበቡ ይለማመዳል። ከዚያም ቀጥሎ ወደ ገበተ ሐዋርያ[201] ይተላለፋል። ገበተ ሐዋርያ የንባብን ስልት የሚለማመድበት የትምህርት ደረጃ ነው። በዚህ ጊዜ የሚጠብቀውንና የሚላላውን ተናባቢውንም ጭምር ጠንቅቆ ያጠናል። ይህን ሲጨርስ ዳዊት ይጀምራል። ዳዊት ተምሮ ከደገመ በኋላ የንባብ ክፍል የትምህርት ደረጃ ይፈጸማል።

የንባብ መማሪያዎች የግዕዝ መጻሕፍት ናቸው። ባሁኑ ጊዜ ግን በከተማ ከሚገኙት አስተማሪዎች አንዳንዶቹ በገበተ ሐዋርያ ስፍራ የአማርኛ መጻሕፍትን ሲቀላቅሉና ሲያስነብቡ ይታያሉ።

የንባብ ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ሕፃናት ናቸው። ይሁን እንጂ ሽማግሌዎችም ትምህርትን ከፈለጉ አይከለከሉም።

በንባብ ትምህርት ቤት አስተማሪው በልዩ ልዩ መንገድ የግብረ ገብነትን መንፈስ በሕፃናቱ ሕሊና ይቀርጻል። ይኸውም ቀጥሎ ያለው ነው።

እግዚአብሔርን መፍራት  
አባትንና እናትን ማክበር፤ አስተማሪንም መውደድ።  
ሽማግሌዎችን ማፈርና ማክበር

---

[201] ወይንም ገበተዋርያ። ከፊደል ቀጥሎ ንባብ የሚጠናበት ትምህርት።

በጠቅላላም በጎ ምግባርን ሁሉ ያስጠናቸዋል።

## ሁለተኛ፤ የዜማ ትምህርት

የዜማ ትምህርት ሦስት ክፍል ሆኖ ይገኛል። ይኸውም

ሀ) ጾመ ድጓና ድጓ፤ ምዕራፍ
ለ) መዋሥዕትና ዝማሬ
ሐ) ቅዳሴ ማለት ነው።

እነዚህም በአንድነት ሲጠቃለሉ ፀዋትወ ዜማ የሚባል ስም ያገኛሉ። ዜማ ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት የሚፈለግ የመዘምራን ሞያ ነው።

ተማሪው የዜማን ትምህርት በውዳሴ ማርያም ይጀምርና ቀስ በቀስ እየተለማመደ የቃል ትምህርት ወደሚባለው ክፍል ይደርሳል። ቀጥሎም ጾመ ድጓ የተባለውን የዜማ መጽሐፍ ይማራል። ጾመ ድጓን ሲጨርስ ምልጣን እንዲያመለጥን ይፈቀድለታል። ይህም ከአንድ የትምህርት ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያስታውቅለት ምልክት ነው። ሆኖም ገና ዜማ አልጨረሰም፤ ወደ መዝገበ ድጓ ገብቶ ይማራል። መዝገበ ድጓ ሲጨርስ ከፀዋትወ ዜማ አንዱን ክፍል አጠናቀቀ ይባላል። በሙሉ ለመማር ሲፈልግም መዋሥዕትና ዝማሬ ቅዳሴ መጨመር አለበት። ከዚህ በላይ ደግሞ አቋቋም የሚባለውን ዜማ (ዝማሜ፣ መረግድ፣ ጽፋት) በየስልቱ ይማራል። ይህን ሁሉ ሙሉ በሙሉ የተማረ ከሆነ የፀዋትወ ዜማ ሊቅ ይሆናል። በከፊልም ቢማር ለዚያው ለተማረው ዐዋቂ ሆኖ ይጠራበታል። የዜማ ትምህርት እጅግ አድካሚና ጊዜ አባካኝ ነው።

የዜማ ትምህርት እስከዛሬ የሚሰጠው በግዕዝ ቋንቋና በግዕዝ መጻሕፍት ነው። በአማርኛ ቋንቋና በአማርኛ መጽሐፍ የዜማ ትምህርት አልነበረም። በአሁኑ ጊዜ ግን የአማርኛውን ግጥም በዜማ መልክ ማዜም ተጀምሯል። ስሙም መዝሙር ተብሏል።

የዜማ መምህር እሱ ራሱ ምሳሌነትን እያሳየ ለተማሪዎች ግብረ ገብነትን ያስተምራል። ይኸውም ቤተ እግዚአብሔርን ለማገልገል ቀዳሚ እየሆነ ያሳያቸዋል ማለት ነው። ከዚህም በላይ ፈሪሀ እግዚአብሔርንና ኀፈረ ገጽን፣ አትሕቶተ ርእስን፣ ገቢረ ሠናይን[202] በግብር ያስተምራቸዋል። እነዚህን ነገሮች የተከተሉት ተማሪዎች በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ መንገድ መልካም ጠባይንና መልካም የኑሮ እድልን ሲያገኙ፤ ያልተከተሉት ግን ወደ ጉዳት ይደርሱ ነበር።

[202] ፈሪሀ እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔርን መፍራት፤ ኀፈረ ገጽ፣ አንገትን ሰበር አድርጎ መሄድ፤ አትሕቶተ ርእስ፣ ራስን ዝቅ አንገትን ደፋ ማድረግ፣ ገቢረ ሠናይ፣ በጎ አድራጎት።



## ሦስተኛ፤ ስለ ቅኔ ትምህርት

የቅኔ ትምህርት የግዕዝን ቋንቋ ለማወቅና በቅኔ ስልት ለመራቀቅ የሚያገለግል ነው። አስተማሪው መጀመሪያ የግዕዙን ቃል በአማርኛ እየተረጐመ ለተማሪዎቹ ግሥ ይገሠሥላቸዋል። ቀጥሎም ቅኔውን በየክፍሉና በየቤቱ እያዘጋጀ ይዘርፍላቸዋል። ተማሪዎች ግሡንና ቅኔውን እየተቀባበሉ በአስተማሪያቸው ፊት ያጠናሉ። በማግሥቱም እነርሱ ራሳቸው በየትምህርት ደረጃቸው መጠን ቅኔ ቈጥረው ለአስተማሪያቸው ያቀርባሉ። አስተማሪውም የጐደለውን በመሙላት የጠመመውን በማቃናት እያረመ ያስረዳቸዋል።

ለቅኔ ትምህርት ሰባት ክፍሎች አሉት። እነርሱም፣ ጉባኤ ቃና፤ ዘአምላኪየ፤ ሚበዝኁ፤ ዋዜማ፤ ሥላሴ፤ ዘይእዜ፤ መወድስ የተባሉ ናቸው። ከእነዚህም በላይ ኀህልከ[203]፣ ሕንቄሄ፣ አጭር ዋዜማ፣ አጭር መወድስ የተባሉ ተደራቢዎች ይገኛሉ። እነዚህም የቅኔ ክፍሎች መዘምራን ቤተ እግዚአብሔርን በያሬድ ዜማ በሚያገለግሉበት ጊዜ በየዜማው ክፍል እየገቡ የሚነገሩ ናቸው። የቅኔ ሥርዓት ይህ ብቻ ሳይሆን ሌላም አለ።

የቅኔ ተማሪ ትምህርቱን በጉባኤ ቃና ይጀምራል። አስተማሪው የቅኔ ችሎታውን አይቶ ሲፈቅድለትም ወደ ዘአምላኪየ ይተላለፋል። በዚህም ዓይነት ከደረጃ ወደ ደረጃ እየተላለፈ ከመወድስ ይደርሳል። ይህ ሥርዓት ከዘመኑ ትምህርት ጋር ሲነፃፀር ከክፍል ወደ ክፍል መዘዋወርን የመሰለ ነው። ተማሪው ከመወድስ ደረጃ ከደረሰ በኋላ አስተማሪው ችሎታውን ሲረዳለት ቅኔ እንዲቀኝ ይፈቅድለታል። ተማሪውም በክብረ በዓል ቀን በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ክብር ይእቲና እጣነ ሞገር ሰጥቶ ቅኔ ይቀኛል።

የቅኔ ትምህርት አእምሮን ለማነጽና በምሥጢር ለመራቀቅ የሚያገለግል ነው። ተማሪው በዚህ ጊዜ ግዕዙን ብቻ ሳይሆን አማርኛንም እግረ መንገዱን ለመማር ዕድል ያገኛል። ምክንያቱም ግሡን ወይም ቅኔውን የሚተረጕመውና የሚፈታው በአማርኛ ስለሆነ ነው። ቅኔ ከተቀኘ በኋላም ሰዋስው የተባለውን የቅኔ አገባብ ይማራል። ይህም ትምህርት በቋንቋ ጥበብ በጣም እንዲራቀቅ ያደርገዋል።

የቅኔ መምህር ለተማሪዎቹ የዘረፈላቸውን ቅኔ በሚፈቱበት ጊዜ አንዳንድ የታሪክ ቃል ጣልቃ እያስገባ ይተርክላቸዋል። ይህም ታሪክን እንደ ማስተማር የመሰለ ነው። ከዚህም በላይ ፈሪሀ እግዚአብሔርንና ገቢረ ሠናይን ሁልጊዜ ያስተምራቸዋል።

[203] በተለይ ለነገሥታት የሚሰጥ ሦስት ቤት ያለው ቅኔ።

## አራተኛ፣ ስለ ትርጓሜ መጻሕፍት

ትርጓሜ መጻሕፍት የሚባለው የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል በሐተታ መግለጽና በምሥጢሩ መራቀቅ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትም አራት ጉባኤያት ተብለው ይጠራሉ። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) መጻሕፍተ ብሉያት። እነርሱም 46 መጻሕፍት ናቸው።

ለ) መጻሕፍተ ሐዲሳት። እነርሱም 35 መጻሕፍት ናቸው። ብሉያትና ሐዲሳት ከአንድ ላይ ሲደመሩ 81 ስለሚሆኑ ሰማንያ ወ አሀዱ የሚል ስያሜ አላቸው።

ሐ) መጻሕፍተ ሊቃውንት። እነርሱም ሃይማኖተ አበው፤ ፍትሐ ነገሥት፤ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፤ ቄርሎስ፤ ቅዳሴያት፤ የቍጥር መጻሕፍት እና አቡሻክር ናቸው።

መ) መጻሕፍተ መነኮሳት። እነርሱም ማር ይስሐቅ፤ ፊልክስዩስ፤ አረጋዊ መንፈሳዊ ናቸው።

የመጻሕፍት መምህራን ለደቀ መዛሙርታቸው ነገረ እግዚአብሔርን በማስረዳትና የመጻሕፍትን ምሥጢር በመመርመር ጊዜአቸውን ሁሉ ያሳልፋሉ። እግዚአብሔርን በመፍራትና በጎ ሥራ በመሥራት ምሳሌነታቸውን ለተማሪዎቻቸው ያተርፋሉ።

ዋነኞቹ የትምህርት ዓይነቶችና ለነዚያው የሚያስፈልገው የዘመኖች ግምት እነሆ ከዚህ በታች ተመልክቷል[204]። የማጥናቱ ጊዜያት እንደ ሰውየው ትጋትና እንደ አእምሮው ስፋት፤ መቀልጠፍ ወይም መዘግየት አለበት።

አንደኛ የንባብ ትምህርት።

ሀ) የጀማሪዎች ትምህርት ከፊደል እስከ ገበተዋርያ ከ6 ወር እስከ 1 ዓመት ያህል።
ለ) የከፍተኞች ትምህርት ከገበተዋርያ እስከ ዳዊት መድገም (ከነቃል ትምህርቱ) ከ1 ዓመት እስከ 1 ዓመት ተኩል።

[204] ከዚህ በታች የቀረበው የትምህርት ዘመኖች ግምት የተወሰደው ብላታ መርስዔ ኀዘን ሐምሌ 26 ቀን 1937 ዓ.ም. ስለሚመጣው ዘመን ቤተ ትምህርት ለአማርኛና ለግዕዝ ትምህርት የሚያስፈልገውን አቅድ ለመመርመርና ለማስታወቅ ለተመረጠ ኮሚቴ ካቀረቡት ሪፖርት በከፊል የተወሰደ ነው።



ሁለተኛ የዜማ ትምህርት።

ሀ) የጀማሪዎች ትምህርት (ከውዳሴ ማርያም እስከ ሠለስት የቃል ትምህርት)፤ ከ1 ዓመት እስከ 1 ዓመት ተኩል።
ለ) ጾመ ድጓና ምዕራፍ፤ ከ1 ዓመት እስከ 2 ዓመት።
ሐ) ድጓ እስከ አንቀጹ፤ ከ2 ዓመት እስከ 3 ዓመት።
መ) ዝማሬና መዋሥዕት፤ ከ1 ዓመት እስከ 1 ዓመት ተኩል።
ሠ) 14 ቅዳሴ፤ ከ1 ዓመት እስከ 1 ዓመት ተኩል።
ረ) አቋቋም (ዝማሜ፣ መረግድ፣ ጽፋት፣ ዚቅ)፤ ከ2 ዓመት እስከ 4 ዓመት።

ሦስተኛ የቅኔ ትምህርት።

ሀ) የጀማሪዎች ትምህርት (እስከ መቀኘት)፤ 1 ዓመት።
ለ) የከፍተኞች ትምህርት (ቅኔን ማስፋፋት)፤ 1 ዓመት።
ሐ) የአስተማሪነት ትምህርት (አገባብ)፤ 1 ዓመት።

አራተኛ የትርጓሜ ትምህርት።

ሀ) የመጻሕፍተ ብሉያት ትርጓሜ፤ ከ4 እስከ 5 ዓመት።
ለ) የመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ፤ ከ3 እስከ 4 ዓመት።
ሐ) የመጻሕፍተ ሊቃውንት ትርጓሜ፤ ከ3 እስከ 4 ዓመት።
መ) የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ፤ ከ2 እስከ 3 ዓመት።
ሠ) የቍጥር መጻሕፍት፤ ከ1 ዓመት እስከ 1 ዓመት ተኩል።

## ማጠቃለያ

ስለ ቤተ ክህነት ትምህርት እነሆ ይህ አጭር መግለጫ ቀርቧል። ኮሚሺኑ ከዚህ የበለጠ ዝርዝር መግለጫ ለማግኘት የሚፈልግ ቢሆን ግን በቤተ ክህነት ውስጥ ስለ ትምህርት የተቋቋመውን ክፍል እንዲጠይቅ እናሳስባለን። ምክንያቱም ዛሬ በአዲሱ ዘመን ምናልባት የተሻሻለ የትምህርት አቋም እንዳለ በጊዜው ያለውን ሊያስረዳ የሚችል እርሱ ስለሆነ ነው።

ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ

26-8-63

## አባሪ ሐ

## የአለቃ ገብረ መድኅን አጭር ታሪክ

አለቃ ገብረ መድኅን በአሰቦት ገዳም በጾምና በጸሎት ተጸምደው 40 ቀን ከቈዩ በኋላ መስከረም 4 ቀን 1918 ዓ.ም. ሞተው እዚያው እገዳሙ ተቀበሩ። የነህ ታላቅ ሰው ታሪክ እንደሚከተለው ነው።

አገራቸው ትግሬ ውስጥ ሽሬ ሲሆን በትምህርት ምክንያት አብዛኛውን ዘመናቸውን በበጌምድርና በጐጃም በሸዋ ያሳለፉ፤ በሊቅነታቸው የታወቁ መምህር ናቸው። ትምህርት ለመማር ያልሄዱበት ደብርና ያልቀጸሏቸው መጻሕፍት አይገኙም። ሐዲሱን ከቡልጌው ከአለቃ ወልደ አማኑኤል፣ ሊቁን ከተጕለቴው ከአለቃ ወልደ ሥላሴ ማንመልሶህ ተምረው ማስተማር በጀመሩ ጊዜ ደቀ መዛሙርት በዙላቸው፤ ጉባኤ ሰፋላቸው፤ በዜማና በቅኔም እጅግ ምስጉን ነበሩ።

ከአድዋ ዘመቻ በኋላ መጀመሪያ ደብረ ብርሃን ሥላሴን ሦስት ዓመት፣ ሁለተኛ አራዳ (አዲስ አበባ) ጊዮርጊስን ሦስት ዓመት፣ ሦስተኛ እንከብር ሚካኤልን ሦስት ዓመት ተሾመውታል። ከዚያ በኋላም ሹመቱን በፈቃዳቸው ትተው በ1900 ዓ.ም. በነሐሴ ወር በሐረርና በጅቡቲ በኩል ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው በ1901 ዓ.ም. በጥር ወር በጅቡቲ በኩል ተመለሱና ሐረር ላይ ከደጃዝማች ባልቻ ዘንድ ተቀመጡ።

ከዚህም በኋላ ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን በ1902 ዓ.ም. የካቲት 24 ቀን ሐረርጌን ተሾመው ወደ ሐረር በወረዱ ጊዜ አለቃ ገብረ መድኅንን ሐረር ላይ ስላገኟቸው እዚያው ሆነው እንዲያስተምሩ ጠይቀው አስቀሯቸው። ቀጥሎም አደሬ ጢቆ ላይ የሥላሴን ቤተ ክርስቲያን ሚያዝያ 7 ቀን 1903 ዓ.ም. ቅዳሜ በተከሉ ጊዜ ለዚሁ ደብር አለቃ አድርገው ሹመው በክብር አስቀመጧቸው።

አለቃ ገብረ መድኅን የደብሩን ሥርዓት በሚገባ አቋቍመውና ምሁራን ደቀ መዛሙርት እነ አለቃ ዘውገን፣ እነ አለቃ ሠርዌን፣ እነ አለቃ ለማ ወልደ ታሪክን፣ እነ አለቃ አርአያ ሥላሴ ወሮታን ሰብስበው የደብሩን ስም አስመሰገኑት። ከሰባት ዓመት በኋላ በሰገሌ ዘመቻ ዘመን ሹመቱን በፈቃዳቸው ለቀው አለቃ ገብረ ክርስቶስ ወልደ ዮሐንስን አሾሙብትና እርሳቸው በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን አጠገብ ሆነው በምክርና በልዩ ልዩ ሌላ ሥራ እየረዱ፣ መጻሕፍትንም እያስተማሩ በአዲስ አበባ ተቀመጡ። ልዑል አልጋ ወራሽ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ለማጻፍ በ1910 ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር አንድ ድርጅት ባቋቋሙ ጊዜ የዚህ ድርጅት መሪ አለቃ ገብረ መድኅን ነበሩ።

ከዚህም በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ በአዳል በረሃ ውስጥ በአሰቦት ያለውን ጥንታዊ ገዳም እንደገና ለመገደምና ታቦተ ሥላሴን ለመትከል ስለፈለጉ፣ ለዚሁ ሥራ አለቃ ገብረ መድኅንን አዘዟቸውና በ1911 ዓ.ም. የካቲት 7 ቀን አሰቦት ገቡ። በዚያም መቃኞ አሠርተውና በየካቲት 27 ቀን የሥላሴን ታቦት

አስገብተው፤ ከአባ ገብረ አብና ከሌሎች ሁለት መነኰሳት ጋር በመተባበር ገዳሙን አቋቋሙ። ይህ አሰቦት በቀድሞ ጊዜ «ደብረ ወገግ» የተባለ የአቡነ ሳሙኤል ገዳም የነበረበትና በግራኝ ወረራ ጠፍ ሆኖ የኖረ ነው።

አለቃ ገብረ መድኅን ካለፈው ዓመት ወዲህ መኖሪያቸውን በዚህ በአሰቦት ገዳም አድርገው የሃይማኖተ አበውን ትርጓሜ እያጻፉ ተቀምጠው ነበር። በግንቦት ወር 1917 ዓ.ም. የቤተ ክርስቲያኑን መሠረት አስጀምረው በማሠራት ሳሉ በነሐሴ መባቻ ለፍልሰታ ጾም ቤት ዘግተው ከሰው ተለይተው ሱባዔ ገቡ። ስለ ምግብ ነገር ለደቀ መዛሙርታቸው የሰጡት ትእዛዝ፣ የታጠበ ጥቂት ሽምብራና ትንሽ ውሐ ብቻ እንዲያቀርቡላቸው ስለ ሆነ ሽምብራውንና ውሐውን በቀን አንድ ጊዜ በግድግዳ ቀዳዳ እያሾለኩ ያስቀምጡላቸው ጀመር። እሳቸውም በፊተኞቹ ሁለት ሱባዔዎች ከሽምብራው በጥርኝ እየለኩ ከውሐው ጥቂት እየከፈሉ ይወስዱ ነበር። በኋላ ግን ምግብ እየቀነሱ ቈዩና በመጨረሻ ከእህልና ከውሐ በፈቃዳቸው በፍጹም ተከለከሉ።

ደቀ መዛሙርታቸውም ያቀረቡላቸውን እህልና ውሐ እንዳልቀመሱት በተረዱ ጊዜ እባክዎ ስለ እግዚአብሔር ብለው እህል ውሐ ይቅመሱ እያሉ ቢለምኗቸው እንቅፋት አትሁኑብኝ ብለው ገሥጸው መለሷቸው፤ በዚያን ሰሞን ጸሎት ሲያደርጉ ድምፃቸው ጥቂት ጥቂት ይሰማ ነበር። በኋላ ግን ድምፃቸው ስለ ጠፋባቸው ደቀ መዛሙርታቸው በሩን ሰብረው ቢገቡ በጾም ብዛት ደክመው ወድቀው አገኟቸው። ውሐ ለማቅመስ ቢፈትኑም የማይቀበሉ ሆኑና ሱባዔ በገቡ በ40ኛው ቀን መስከረም 4 ቀን 1918 ዓ.ም. ዐረፉ። ደቀ መዛሙርታቸውም እየተላቀሱ አንሥተው እዚያው እገዳሙ ቀበሩዋቸው። ዕድሜያቸው 73 ዓመት ያህል ነበር።

ከዚህ በኋላ የሞታቸው መርዶ በመስከረም 13 ቀን ለልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ተነገራቸውና በግቢያቸው ኀዘን አደረጉ። የአዲስ አበባ አድባራት ካህናትም የመታሰቢያ ጸሎት ሊያደርጉላቸው ስለ ወሰኑ፣ መስከረም 14 ቀን 1918 ዓ.ም. ኀሙስ በአራዳ ጊዮርጊስ ውሎ ሆነና የሬሣ ምሳሌ ቃሬዛ ተደርጎ፣ ልዑል አልጋ ወራሽና እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ባሉበት መኳንንቱና ሊቃውንቱ በተሰበሰቡበት እየተለቀሰና የጕዞ ፍትሐት እየተፈታ መታሰቢያቸው በሚገባ ተከበረ።

በፍትሐቱ ላይ የክስተት አርያም ድርሰት ተደርሶ ነበርና ክብራቸውን በመግለጽ ሊቃውንቱ ከተቀኙት ሥላሴ ቅኔ የማስታውሰውን ከዚህ በታች ጽፌዋለሁ፤

*አንደኛ አለቃ መርሻ ዘገነት ኪዳነ ምሕረት የተቀኙት*

ኃያላን ድኅረ ሞኡ እንዘ ኢይፈርሁ ብዙኃነ፣
ክልኤቱ አኃው ዘሰይፈ ሃይማኖት ቀነቱ፣
እምግብጽ ወኢትዮጵያ ዝንጉኃ ያእትቱ፣
አይቱ ኃለፉ ቅኑታነ ሰይፍ እሙንቱ፣
እንዘ ብዙኃን በበፍኖቱ፣



አኮኑ ሞቶሙ ለክልኤቱ፣
እመ በጽሐ ለዋሕድ ሞቱ።

### የቅኔው ትርጓሜ

ኃያላኑ ሳይፈሩ ብዙዎችን ድል ካደረጉ በኋላ፣
የሃይማኖት ሰይፍን የታጠቁ ሁለቱ ወንድማማች፣
ከግብጽና ከኢትዮጵያ ሽሙጥን ያስወግዱ ዘንድ፣
እነዚያ ሰይፍን የታጠቁ ወዴት ሄዱ፣
ብዙዎች በየመንገዱ ሳሉ፣
የአንዱ ሞት ቢደርስ፣
የሁለቱ ሞት ነውና።

### የቅኔው ምሥጢር

የጦር መሣሪያ የታጠቁ ጀግኖች የሀገር ጠላትን ድል አድርገው ከሀገር ላይ ስድብና ውርደትን ሊያስወግዱ እንደሚችሉ ሁሉ በጦር መሣሪያ የተመሰለ ቃል እግዚአብሔርን በጥልቀት የሚያውቁ ስመጥሮች ሊቃውንት አለቃ ገብረ መድኅንና አለቃ ወልደ ማርያም በኢትዮጵያና በግብጽ የሃይማኖት ክርክር ቢከሠት እንዳይከላከሉልን "ወዴት ሄዱ" በማለት ባለቅኔው የሁለቱን ሊቃውንት ሞት ያረዳሉ።

*ሁለተኛ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ዘራጕኤል የተቀኙት*

ለፍሡሕ ገብረ መድኅን፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ ኢይደሉ፣
ሕንፃ ኑኃሚን ትንቢት፣ ደኅረ ተፈጸመ ሎቱ፣
መቃብረ አምጣነ ረሰያ ለገዳም ርስቱ፣
ባሕቱ ይደሉ ለወልደ ማርያም ባሕቲቱ፣
ሰቆቃወ ድንግል ለለዕለቱ፣
እምጣነ በአፍኣ ተቀብረ እምትእይንቱ፣
ወውእቱ እንግዳ በቤቱ።

### የቅኔው ትርጓሜ

ለደስተኛው ገብረ መድኅን የኤርምያስ ልቅሶ አይገባውም፣
የኑኃሚን ሕንፃ/ ትንቢት ከተፈጸመለት በኋላ፣
ገዳም/ርስቱን መቃብር አድርጓታልና፣
ነገር ግን ለወልደ ማርያም ብቻ፣
የድንግል ልቅሶ በየቀኑ ይገባል፣
ከከተማው በውጭ ተቀብሯልና፣
በቤቱም እንግዳ ነበርና።

### የቅኔው ምሥጢር

ቅኔው በአጭሩ የሚያስረዳው ነቢዩ ኤርምያስ ለንጉሥ ኢዮስያስ (2 ዜና መዋ 35:25) እንዳለቀሰው ያለ ልቅሶ ለአለቃ ገብረ መድኅን ሊለቀስላቸው እንደማይገባ ነው። ምክንያቱም ኑኃሚን የተባለችው እስራኤላዊት ከተሰደደችበት ሀገር ተመልሳ በሀገርዋ በርስቷ እንደተቀበረች (ሩት 1:16-17) እርሳቸው እንደ ርስት አድርገው በአቀኑት በአሰቦት ገዳም በክብር ተቀብረዋል።

አለቃ ወልደ ማርያም ግን ከኖሩበት ቦታ ውጭ ስለተቀበሩ ድንግል ማርያም በስደትዋ ጊዜ ያለቀሰችው ልቅሶ ሊለቀስላቸው እንደሚገባ በቅኔው ተመሥጥሯል።

*ሦስተኛ አለቃ ወልደ ተክሌ ዘቦሩ ሜዳ የተቀኙት*

ይቤለነ በመልእክቱ፣ መተርጉመ ጳውሎስ ገብረ መድኅን፣
ከመ ምስለ ክርስቶስ አሀሉ ይእዜ፣ በመዓዛ ገነት ጾም፣
እፈቱ ተፈልጦ እምዝንቱ ዓለም፣
ወምስለ ወልደ አብ ለወልድ አካሉ፣ ዘገብረ መድኅን ሕማም፣
ከመ ቃለ ቄርሎስ መተርጉም፣
በተዋሕዶ ሞት ከብረ ወልደ ማርያም፣
እስመ ዝንቱ ሃይማኖት ፍጹም።

የቅኔው ትርጓሜ

የጳውሎስ ተርጓሚ ገብረ መድኅን በመልእክቱ እንዲህ አለን፣
ዛሬ ከክርስቶስ ጋር እኖር ዘንድ፣
በገነት/ ጾም መዐዛ ከዚህ ዓለም መለየትን እወድዳለሁ፣
የገብረ መድኅን ማኅተም የሆነ የአካለ ወልድ/አብ ልጅ ሲሆንም፣
እንደ ተርጓሚው ቄርሎስ ቃል፣
ወልደ ማርያም በሞት/ተዋሕዶ ከበረ፣
ይህ ፍጹም ሃይማኖት ነውና።

የቅኔው ምሥጢር

ቅኔው በአጭሩ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ከክርስቶስ ጋር ለመኖር ይመኝ እንደነበረ (ፊል 1:23) ጾምን ያዘወትሩ፣ የቅዱስ ጳውሎስን የመልእክታት ትርጓሜ ያመሠጥሩ የነበሩ አለቃ ገብረ መድኅን ሞትን ያለመሳቀቅ በደስታ ለመቀበል ከሚያስችል የዕድሜ ደረጃ መድረሳቸውን ያስረዳል።

"ወልደ አብ ወልደ ማርያም ክርስቶስ በተዋሕዶ ከበረ" እንደሚባለው በትምህርት የመምህር አካለ ወልድ ልጅ በዕውቀት የአለቃ ገብረ መድኅን ማኅተም አምሳያ የነበሩት አለቃ ወልደ ማርያም በሞት ከበሩ ማለት ከአለቃ ገብረ መድኅን ጋር በማኅሌትና በቅኔ የክብር ፍትሐት ተደረገላቸው ማለት እንደሆነ ከቅኔው ምሥጢር ይስተዋላል።

*አራተኛ አለቃ ወልደ ሚካኤል ዘአዲስ አበባ ቂርቆስ የተቀኙት*

አርመመ ገብረ መድኅን፣ ማዕበለ ንባብ ወትርጓሜ፣
ወእምኔሁ ቀደመ ተንሥአ ወልደ ማርያም በከር፣
በሞት እስመ ተአተተ ሕይወቱ እምድር፣
በምንት ይበቍል ባሕቱ ዘምስለ ሐመልማል ሣዕር፣
እምከመ ተኃጥአ ማየ ባሕር፣
እስመ ጌሠ ሞት ሐንካሳ እእጋር፣
በክልኤቱ ሊቃውንት አብትር።



የቅኔው ትርጓሜ

የንባብና ትርጓሜ ማዕበል/ገብረ መድኅን ጸጥ አለ፣
ወልደ ማርያም በኩርሞ መነሣትን ከእርሱ ቀደመ፤
ሕይወቱ ከምድር በሞት ተወግዷልና፣
ነገር ግን የባሕር ውሐ ከታጣ፣
ሣር ከልምላሜ ጋር በምን ይበቅላል፣
እግረ አንካሳ/ሞት፣
ሁለቱን ሊቃውንት/በትሮች ተመርኩዟልና።

የቅኔው ምሥጢር

ነፋስ በሌለበት ጊዜ የባሕር ማዕበል ጸጥ እንደሚል ለመጻሕፍት ንባብና ትርጓሜ ትምህርት እንደ ማዕበል ኃይለኛ የነበሩት አለቃ ገብረ መድኅን ነፍሳቸው ከሥጋቸው በተለየች ጊዜ የዘለዓለም ጸጥታ ማድረጋቸውን ቅኔው ያስረዳል። በኩር ክርስቶስ ከሙታን አስቀድሞ እንደ ተነሣ ከአለቃ ገብረ መድኅን ቀድመው የሞቱት አለቃ ወልደ ማርያም ስማቸው እንደ ሞታቸው ቅደም ተከተል ከአለቃ ገብረ መድኅን ጋር መነሣቱ በቅኔው ተገልጿል። የውሐ ዕጥረት ሲኖር የዕፀዋት ልምላሜ ሊኖር አይችልም፤ በሊቃውንት መታጣት ምክንያትም ዕውቀት ይጠፋል። የአካል ጉዳት ያለበት ሰው ሁለት በትር ሊመረኰዝ ይችላል፤ እንዲሁም በአንካሳ የተመሰለው ሞት ሁለቱን ሊቃውንት በአንድ ወቅት መውሰዱ በቅኔው ተብራርቷል።

አባሪ መ

## የሐኪም ወርቅነህ የሕይወት ታሪክ

ሐኪም ወርቅነህ እንደ ፈረንጅ አቈጣጠር በ1858 ዓ.ም. (1865 እ.ፈ.አ.) ጥቅምት 11 (22 ኦክቶበር) በጐንደር ከተማ ተወለዱ፤ አባታቸው ነጋድራስ እሸቴ ይባላሉ። እናታቸው ወይዘሮ ደስታ ወልደ ማርያም ይባላሉ። የክርስትና ስማቸው ኪዳነ ማርያም ነው። እናትና አባታቸው ወርቅነህ ብለው የዓለም ስም አወጡላቸው። የእኅታቸው ልጅ፣ ላቀች ኪዳነ ማርያም አሁን በቦታቸው አሉ። ዘለለው እሸቴ ታላቅ ወንድማቸው ነው።

አጼ ቴዎድሮስ በ1860 ዓ.ም. (1868 እ.ፈ.አ.) አእምሮዋቸው በቊጣ በተበላሸ ጊዜ የጐንደርን ካህናትና ታላላቅ ሰዎች እያሠሩ በግዞተኛነት ወደ መቅደላ መላክ ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ነጋድራስ እሸቴም ታስረው ወደ መቅደላ ተወስደው ነበር፤ ሚስታቸውም ወይዘሮ ደስታ አንድ ልጃቸውን ወርቅነህን ይዘው ወደ ባላቸው መቅደላ ሄደው አብረው ተቀመጡ። 1860 (1868 እ.ፈ.አ.) ዓ.ም. በሚያዝያ ወር እንግሊዞች አጼ ቴዎድሮስን ወግተው መቅደላን ሲይዙ ወርቅነህ እሸቴ ዕድሜያቸው ሁለት ዓመት ከመንፈቅ ሆኖ የምትጠብቃቸው የእናታቸው ታናሽ እኅት ነበረች።

እንግሊዞች በመቅደላ ክረብታ ሲገቡ ሽብር ሆነና ሁሉም ራሱን ለማዳን ሽሽት ሆነ። በዚህ ጊዜ ወርቅነህ እሸቴ ብቻቸውን በአንድ ቤት ውስጥ ቀሩ። የእንግሊዝ ወታደሮች ባገኟቸው ጊዜ አዝነው ወደ ጦሩ አለቃ ወስደው አስረከቧቸው። የአጼ ቴዎድሮስንም ልጅ፣ ዓለማየሁን እንደዚሁ አግኝተውት በሕፃንነቱ አዝነው፤ ደግሞም የንጉሥ ልጅ መሆኑን ዐውቀው፤ ወደ ጦር አለቃው ወሰዱትና ከወርቅነህ ጋራ አብረው አስቀመጧቸው።

እንግሊዞች ከመቅደላ ወደ አገራቸው የሚመለሱበት ቀን በደረሰ ጊዜ እቴጌ ጥሩ ወርቅንና ልጃቸውን ዓለማየሁ ቴዎድሮስን እንዲሁም ወርቅነህ እሸቴን እነዚህን ሦስቱን ይዘዋቸው ተጓዙ። እቴጌይቱ ገና ከጠረፍ ሳይደርሱ ታመው ሞቱ። ዓለማየሁና ወርቅነህ ግን ከጠረፍ በደኅና ደረሱ። ጀኔራል ሮበርት ናፒየር ምጥዋ ሲደርስ ወደ እንግሊዝ አገር ስለ ተጠራ ዓለማየሁን ይዞ በመርከብ ሄደ። ዓለማየሁ ሎንዶን ደርሶ በመልካም ሁናቴ ተቀምጦ እየተማረ አደገ። በ19 ዓመት ዕድሜ በ1872 ዓ.ም. ሞቶ ዊንድሶር በተባለ ቤተ መንግሥት ግቢ በሚገኘው ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ።

ወርቅነህ እሸቴን ግን ኮሎኔል ቻምበርሌን የተባለ ሰው ይዟቸው ወደ ህንድ አገር ሄደ። ወርቅነህ እሸቴ ፐንጃብ ላይ እየተማሩ ካደጉ በኋላ በመንግሥት ክፍል ሲቪል ዶክቶር ሆነው ይሠሩ ጀመሩ። በ1889 ዓ.ም. ወደ እንግሊዝ አገር ሄደው በዋናው ዩኒቨርሲቲ በኤደንብራና በግላስጎው ሕክምና ተምረው ዋናውን የምስክር ወረቀት ተቀብለው ዶክቶር ተብለው ወጡ። ከዚያም ወደ

ህንድ አገር ተመልሰው በሲቪል ሥራ በበርማ[205] አገር በክብር ይቀመጡ ጀመር።

በ1896 ዓ.ም. (እ.ፈ.አ.) ኢትዮጵያና ኢጣልያ በተዋጉበት ዘመን[206] አገራቸውን ለማየት ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት አስበው እስከ ዘይላ ድረስ መጥተው ነበር። ነገር ግን በዘይላ የነበሩት አገረ ገዥ ሚስተር ሀሪንግቶን አሁን በኢትዮጵያ የጦርነት ሰዓት ስለሆነ ከዚህ ማለፍ አይቻልም ብለዋቸው ወደ ህንድ ተመለሱ። ከአድዋ ድል በኋላ የኢትዮጵያ ነፃነት በአውሮጳ ነገሥታት ሁሉ ተረጋግጦ ከታወቀ በኋላ ሚስተር ሀሪንግቶን በአዲስ አበባ የእንግሊዝ መንግሥት ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ፤ በዚህ ጊዜም የሐኪም ወርቅነህን ነገር ለዳግማዊ ምኒልክ አንሥተው አጫውተዋቸው ነበርና በቶሎ ይምጣልኝ ሲሉ ለመኗቸው። ሚስተር ሀሪንግቶንም በጃንሆይ ቃል መጠሩታቸውን ስለጻፉላቸው በ1891 ዓ.ም. (1899 እ.ፈ.አ.) በመስከረም ወር አዲስ አበባ መጡ። በዚህ ጊዜ ከዘመዶቻቸው ጥቂቶቹን አግኝተው ተዋወቁ። በልቅሶ በዕንባ ተቀበሏቸው።

እናታቸው ከመቅደላ ጦርነት በኋላ ምንም ያህል ሳይቆዩ ሞቱ። አባታቸው ነጋድራስ እሸቴ ግን ሌላ ሚስት አግብተው ልጅ ወልደው ሲኖሩ በኋላ ሞቱ። ሐኪም ወርቅነህ በዚህ ጊዜ ያገኟቸው፤ የእናታቸውን እናት ይቶት አለምነሽ ወልደ ተክሌን፣ በመቅደላ ስትጠብቃቸው የነበረችውን አክስታቸውን፣ የእናታቸውን ታናሽ እኅት፣ ተዋበችን ነው።

ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ እስከ 1894 (1902 እ.ፈ.አ.) ዓ.ም. ሚያዝያ ወር ድረስ ቆይተው ወደ በርማ አገር ተመለሱ። በዚያም ቆይተው በኅዳር 1901 ዓ.ም. (1908 ኖቬምበር እ.ፈ.አ.) ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱና በእንግሊዝ ሌጋሲዮን ሐኪም ሆነው ዘጠኝ ወር ተቀመጡ። በዚያን ጊዜም ዳግማዊ ምኒልክ ታመው ነበርና ግርማዊነታቸውን እንዲያክሙ ስለተለመኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ሐኪም ሆነው ጃንሆይን ለማስታመም ነሐሴ 1901 ዓ.ም. (ኦገስት 1909 እ.ፈ.አ.) ወደ ቤተ መንግሥት ገቡ። በዚህ ክፍል ሥራ እስከ 1905 ዓ.ም. (1913 እ.ፈ.አ.) ቆይተው በሰኔ ወር ወደ በርማ ተመለሱ። ወዲያው ትልቁ የዓለም ጦርነት ስለተነሣ እስከ 1919 ዓ.ም. (እ.ፈ.አ.) ቆይተው ሦስተኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ በ1920[207] (እ.ፈ.አ.) ተመለሱ። በዚህ ጊዜ የ55 ዓመት ዕድሜ ሆነው ነበር። ከእንግሊዝ መንግሥት የሚገባቸውን ጡረታ ተቀብለው ለኢትዮጵያ መንግሥት ማገልገል ጀመሩ። እስከ 1923 ዓ.ም. (እ.ፈ.አ.) የተወሰነ ሥራ ሳይዙ በልዩ ልዩ አገልግሎት ለመንግሥት እያገለገሉ ከቆዩ በኋላ በ1923

[205] አሁን ሚያንማር የሚባለው።

[206] የአድዋ ጦርነት።

[207] ዶክተር ፒተር ጋሬትሰን ዘንድ በሚገኙት የሐኪም ወርቅነህ የግል ማስታወሻዎች መሠረት ለሦስተኛ ጊዜ ሐኪም ወርቅነህ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት እ.ፈ.አ. ኦክቶበር 1919 ዓ.ም. ነው።



ዓ.ም. (እ.ፈ.አ.) [1916 ዓ.ም.] የአዲስ አበባን ፍልውሐ መልካም አድርገው እንዲያቋቁሙ ተሾሙ። ሥራውንም በሚገባ አቋቋሙት።



48 አዛዥ ወርቅነህ በርማ በነበሩ ጊዜ

በ1917 ዓ.ም. (1925 እ.ፈ.አ.) በሚያዝያ ወር የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ሹም ሆነው ተሾሙ። ከዚህም ጋር የቤተ ሳይዳን ሆስፒታልና[208] የጅማን መንገድ ሥራ፣ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤትን ሥራ ለመምራት የበላይነትና ዋናው ኃላፊነት ተሰጥቷቸው ነበር።

[208] በኋላ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል፣ አሁን የካቲት 12 የተባለው ሆስፒታል።

በ1927 (እ.ፈ.አ.) [1919 ዓ.ም.] ስለጣና ባሕር ጉዳይ ወደ አሜሪካ መንግሥት ተልከው ሄደው መልእክታቸውን በመልካም ሁናቴ ፈጽመው ተመለሱ።

በ1920 ዓ.ም. (1928 እ.ፈ.አ.) በጥር ወር አዛዥ ተብለው በልዩ በቈመው ፍርድ ቤት ተሾሙ። በ1929 ዓ.ም. (እ.ፈ.አ.) [1922ዓ.ም.] ወደ ህንድ ሄደው ከቦምቤይ በአስተማሪነትና በልዩ ልዩ ሙያ የሚያገለግሉ 21 ህንዳውያን አመጡ። በ1931 ዓ.ም. (እ.ፈ.አ.) የጨርጨርን አውራጃ ግዛት ተሾሙ።

በ1927 ዓ.ም. (1935 እ.ፈ.አ.) በሎንዶን የኢትዮጵያ መንግሥት ልዩ መልእክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሆነው ተላኩ፤ በዚያም ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ ሲከራከሩ ቈይተው በ1928 ዓ.ም. (1936 እ.ፈ.አ.) ኢትዮጵያ በጠላት እጅ ወድቃ ንጉሠ ነገሥቷ ወደ ሎንዶን በተሸገሩ ጊዜ ተቀባይ ሆነው አብረው ሲሠሩ ቈዩ።

በ1933 ዓ.ም. በመስከረም ወደ ህንድ አገር፣ ዩናይትድ ፕሮቪንስስ[209]፣ ዴራዱን ወደሚባለው ከተማ ሄደው ተቀመጡ፤ በዚያም ልጆቻቸውን እያስተማሩ ቈይተው፤ ኢጣልያ ከኢትዮጵያ ከወጣች በኋላ በ1934 ዓ.ም. (1942 እ.ፈ.አ.) በሚያዝያ ወር ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ[210]።

መስከረም 1938 ዓ.ም.
ከሐኪም ወርቅነህ ከቃላቸው ሰምቼ የጻፍሁት።

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ

[209] በኋላ አተርፕራዴሽ፣ አሁን አተርካንድ የሚባለው።

[210] አዛዥ ወርቅነህ እ.ፈ.አ. 1907 ዓ.ም. ኤለን ፋብረከስ የሚባሉትን እንግሊዛዊት ሎንዶን አግብተው ቴዎድሮስ የተባለውን ልጃቸውን እ.ፈ.አ. ሴፕቴምበር 22 ቀን 1908 (መስከረም 12 ቀን 1901 ዓ.ም) ወለዱ። በ1903 ዓ.ም. ከወይዘሮ ሰብይፋት ወንዳፍራሽና ከፊታውራሪ ቱሉ ጅማ የሚወለዱትን ወይዘሮ ቀጸላን አግብተው ስድስት ወንድ ልጆችና ሰባት ሴት ልጆችን ወልደዋል። ሁለቱ ልጆቻቸው ብንያምና ዮሴፍ በ1929 ዓ.ም. ግራዚያኒ ላይ በምብ በተጣለ ጊዜ በኢጣልያኖች ተገድለዋል። አዛዥ ወርቅነህ ጥቅምት 11 ቀን 1945 ዓ.ም. ዐርፈው ሥርዓተ ቀብራቸው በየካ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል። ምንጭ ወይዘሮ ዕሴኒ መኮሪያ፣ ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ።

# አባሪ ሠ

## መተርጒመ ቃል

| | |
|---|---|
| ሃይማኖተ አበው | ከዐረቢኛ የተተረጐመ፣ ከሐዋርያት ጀምሮ በየጊዜው የተነሡት ታላላቅ አበው ያዘጋጇቸውን ትምህርት ጠቀስ ጽሑፎችን የያዘ መጽሐፍ። |
| ለምድ | ከግምጃ ከሐር ከተለፋ የአንበሳ፣ የነብር፣ የግስላ፣ ከበግ ቆዳ በደበሎ ዓይነት ተበጅቶ የተሰፋ የጦር ሠራዊት መደረቢያ ልብስ፣ ከጥንት ጀምሮ የተለመደ። |
| ለዘብ | በበዓል ቀን በቅኔ ማኅሌትና በዑደት ጊዜ ታቦት ሲነግሥ በጸናጽልና በከበሮ እየተመላለሰ የሚዜም ረዥም ዜማ። |
| ልብሰ ተክህኖ | ለጸሎትና ለቅዳሴ ካህናት በቤተ መቅደስ የሚለብሱት ግምጃ። |
| መርሐ ዕውር | የመርሐ ዕውር ትምህርት በኢትዮጵያ ሊቃውንት ዘንድ እራሱን የቻለ የቍጥር ትምህርት (የዘመን አቈጣጠር ስልት) ነው። በ17ኛው ምዕት አጼ ሱስንዮስ የካቶሊክን ትምህርት ከተቀበለ በኋላ መርሐ ዕውር መጽሐፍ እንዲጠፋ አዝዞ ነበር። ዓቃቤ ሰዓት አቦሞ የሚባል ሊቅ መጽሐፉን ይዞ በረሃ በመሄድ እዚያ ትምህርቱን እያሰላሰለ ጊዜው እስኪያልፍ ድረስ ቈይቷል። አጼ ፋሲለደስ ከነገሠ በኋላ የእስክንድርያ ሃይማኖት ሲመለስ ከበረሃ ወጥቶ የመርሐ ዕውርን ትምህርት አስፋፍቶታል። |
| መስተጋብእ | ከያሬድ የተደረሰ የዜማ ትምህርት። |
| መቀጸል | ማጥናት። |
| መቃኞ | ትልቅ ቤት ከመሠራቱ አስቀድሞ ለጊዜው ማገልገያ እንዲሆን የሚሠራ ትንሽ ቤት። |
| መባቻ | የወር መግቢያ፣ የወር የመጀመሪያው ቀን። |
| መወድስ | ምስጋና ወይም ማመስገኛ ማለት ነው። መወድስ የሚባለው ወይም የሚደረሰው በዕለተ ሰንበት ነው። በመወድስ ጊዜ ቅኔ በብዛት ይደረሳል፣ የዳዊት መዝሙር በልዩ ልዩ ዜማ ይደረሳል። |
| መጋዣ | እራሹ ለባለርስት የሚያካፍለው ድርሻ። |
| መፀው | ዘመነ መኸር፣ መስከረም 26 ቀን ዠምሮ እስከ ታኅሣሥ 25 ቀን ድረስ ያሉ ዘጠና አንድ ቀኖች። |
| ሚበዝኁ | ሦስት ቤት ያለው ቅኔ። |
| ማኅሌተ ጽጌ | ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋና አባ ጽጌ ብርሃን የሚባለው ከአይሁድ ሃይማኖት ወደ ክርስትና በአባ ዜና ማርቆስ የተመለሰውና አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታ አብረው የደረሱት መዝሙር። |
| ማኅሌት | ከበሮ የሚመታበት የወር በዓል፣ የዓመት በዓል ዜማ። |
| ማደሪያ መሬት | ጉልት፣ ርስት። |
| ማፈጣጠም | ማዋዋል፣ ማፈራረም። |

| | |
|---|---|
| ምልጣን | 1ኛ በመሪውና በተመሪው፣ 2ኛ ግራና ቀኝ በሁለት አንሺዎች (ተቀባባዮች) የሚዜም መዝሙር:: |
| ምስባክ | በፍታት፣ በቅዳሴ ወይም በጸሎት ጊዜ ወንጌል ከመነበቡ በፊት፣ ዲያቆን ከዳዊት መዝሙር ውስጥ መርጦ የሚያዜመው ሦስት ስንኝ ያለው ጥቅስ:: |
| ምስንጅር | ምስንጅር የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ ሜሴንጀር ከሚለው ቃል የመጣ ነው:: ሜሴንጀር ማለትም መልእክተኛ ማለት ነው:: ይህ የበቅሎ ዘር ፖስታና የጦር ዕቃ ለማመላለስ የተመረጠ ነው:: |
| ምዕራፍ | በእሑድና በዓበይት በዓላት፣ በዓቢይ ጾም ዘወትርም ከቃል ትምህርት፣ ከእንቀጸ ብርሃን ጋር የሚነገር ጸሎት:: |
| ሥላሴ | ስድስት ቤት ቅኔ:: |
| ሥዕል ቤት | ጸሎት ቤት:: |
| ረሞጫ | በፀሐይ ነበልባል የተቃጠለ አሸዋ:: |
| ረጋ ሠራሽ | መናኛ፣ ብዙ ጥበብ የማይታይበት ተራ ሥራ:: |
| ሩብ | አጼ ምኒልክ በ1901 ዓ.ም. ከብር አሠርተው ያወጡት ገንዘብ:: አንድ ብር በ2 አላድ፣ በ4 ሩብ፣ በ8 ተሙን፣ በ16 መሐለቅ ይመነዘር ነበር:: |
| ርስት | ሪም፣ ማደሪያ ሆኖ የሚሰጥ፣ በውርስ የሚተላለፍ፣ የተወሰነ ቀላድ መሬት:: |
| ሰዓተ ሌሊት | የጨለማው ክፍል፣ ከምሽቱ ዓሥራ ሁለት እስከ ንጋቱ ዓሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ የሚደረግ ጸሎት:: |
| ሱባዔ | ለጸሎት ከሰው መለየት ነው:: ሱባዔ ሰባት ቀን ነው፣ ሊበዛም ይችላል:: (አመን) |
| ሰዓታት | ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሊት በየሰዓቱ በዜማ የሚያደርሱት ጸሎት:: ጸሎቱ የተደረሰው በጋስጫው አባ ጊዮርጊስ ነው:: |
| ስርጥ | በገደልና ገደል መሃል ያለ ጠባብ መተላለፊያ:: |
| ስብሐተ ነግህ | የንጋት ምስጋና ማለት ነው:: ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አነጋግ ላይ በዜማ የሚያደርሱት ጸሎት:: |
| ስንክሳር | ቃሉ ግሪክ ሲሆን ትርጓሜው አስተጋቡዕ (ስብስብ) ማለት ነው:: በዓመት ውስጥ በሚገኙት ቀናት የተደረጉ የቅዱሳንን ታሪክ (ገድል) በመተረክ የቤተ ክርስቲያንን በዓላት ያሳውቃል:: የተተረጎመው በ14ኛው ምዕት አባ ሰላማ (1340-1380) በጵጵስና ማዕርግ ላይ በነበሩበት ዘመን ነው:: |
| ቀለምሲስ | ራዕየ ዮሐንስ፣ ከምዕራፍ 1 እስከ 21 ድረስ ያለው:: |
| ቀላድ | 150 ክንድ በሆነ ገመድ ተሰፍሮ ተለክቶ ርዝመቱ ዓሥራ ሁለት ቁመቱ ዘጠኝ ገመድ የሆነ መሬት:: |
| ቀላጤ ማዘዣ | የማስገደጃና የማዘዣ ደብዳቤ:: |
| ቀጣና | ሸንጡ ቀጠን ብሎ የረዘመ መሬት:: |
| ቍራኛ | ከዳኛ ዘንድ እስኪደርስ ወይም እስኪፈረድ ድረስ እግሩ ወይም እጁ ከጠላቱ እግር ወይም እጅ ጋር እንዲጣመር ተደርጎ ከጠላቱ ጋር በአንድነት ይታሰር የነበረ ሰው:: |
| ቍልልታ | ጉብታ፣ ከአካባቢው ተለይቶ እንደ ኮረብታ ከፍ ያለ መሬት:: |



| | |
|---|---|
| ባሕረ ሐሳብ | ባሕር ማለት ዘመን፣ ሐሳብ ደግሞ ቍጥር ማለት ነው:: ባሕረ ሐሳብ ማለት እንግዲህ የዘመን ቍጥር ማለት ነው:: ባሕረ ሐሳብ የተቀመረው በአጼ ሱስንዮስ ሦስተኛ ዓመት ማለት በ1600 ዓ.ም. ላይ ነው:: ባሕረ ሐሳብ የዓመቱን፣ የዕለቱን፣ የአጽዋማቱንና የበዓላቱን ቀመር (ቍጥር) የሚያወጡበት ነው:: |
| ባዘቶ ጥጥ | ፍሬው የወጣለት፣ ለንድፍ የተዘጋጀ ጥጥ:: |
| ተወራጅ | ፊደል እንዲያስቈጥሩ (እንዲያስተምሩ) ከተመደቡት መካከል አንዱ ተረኛ:: |
| ተጋኘነት | ተከራይ:: |
| ትክለኛ | ለሚሰጠው የቤተ ክርስቲያን ቋሚ አገልግሎት ከመንግሥት የቋሚ ርስት ባለቤትነት መብት የተሰጠው:: |
| ቶፋ | ለባለ ርስት የመሬት ግብርን እየተቀበለ የሚገብር:: |
| ነፍጠኛ | ባለ ነፍጥ (ጠመንጃ) ወታደር፣ ነፍጥ ያለው የንጉሥ፣ የሻለቃ አሽከር:: |
| ናዝራዊ | ሰውነቱን ለእግዚአብሔር ስለት የሰጠ፣ ጠጕርን እያጐፈረ፣ ስንሰለትን በአንገቱ አጥልቆ በደረቱ እንደ አስኬማ የሚጠመጥም:: |
| ኖራ ግንብ | ኖራ ከኖራ ድንጋይ (limestone) ወይንም ከኖራ አፈር በእሳት ኃይል ይመረታል:: ኖራው ከተቦካ በኋላ ከአሸዋ ጋር ተለውሶ ግንብ ይገነባል:: በኋላ ዘመን ከሲሚንቶና ከአሸዋ ጋር ይደባለቅም ነበር:: በአሁኑ ዘመን ኖራን መጠቀም ቀርቶ ሲሚንቶ ከአሸዋ ጋር ብቻ እየተለወሰ ይገነባል:: |
| አረር | ጥይት |
| አራቱ ጉባኤያት | መጻሕፍተ ብሉያት፣ ሐዲሳት፣ ሊቃውንትና መነኮሳት:: |
| አርዌ ብርት (በትረ አርዌ) | በእባብ አምሳል የምትሠራ ጳጳሳት የሚይዟት በትር፣ አመጣጧ ከሙሴ ጋር የተያያዘ ነው፤ ዘጸአት ምዕ. 4 እና 7 እይ:: |
| አቀባይ ጥሪ | አፋፍ ላይ ተቁሞ በጩኸት የሚተላለፍ መልእክት:: |
| አቋቋም | መቋሚያ ጸናጽል የሚያዝበት የማኅሌት ዜማ:: |
| አበ ነፍስ | የነፍስ አባት:: |
| አቡሻክር | የቍጥር መጽሐፍ፤ የመዓልቱን፣ የሌሊቱን፣ የክረምቱን፣ የጾሙን፣ የዘመኑን፣ የበዓሉን አዋዋል የሚወስን:: |
| አቡቀዳዲ | ከመንግሥት ለሽልማት ይሰጥ የነበረ፣ ቀጭን ግንባር ላይ የሚታሰር መብሩቅ:: |
| አብደላከኒ ቀሚስ | የመንግሥት ባለሥልጣኖች የሚለብሱት ዥንጉርጉር የሹመት ቀሚስ:: |
| አነባበሮ | ሦስት እንጀራ ተነባብሮ ተጋግሮ በሁለቱም በኩል ዓይን ያለው:: ቅብዓ ኑግ፣ ቅቤ ወይም ዘይት በድልህ ይመታና አነባበሮው ላይ ይለቀለቃል እምጣዱ ላይ እንዳለ:: |
| አንካሴ | ጫፉ ላይ ሹል ብረት የተሰካበት ዘንግ:: |
| አንገርጋሪ | መሪው ከቃኘው በኋላ በቅብብሎሽ የሚዘመር ዜማ:: |
| አጋፋሪ/አጋፈሪ | የቃሉ ፍች አስተናባሪ፣ አስተናጋጅ ማለት ነው:: በቤተ መንግሥት ወይም በእልፍኝ ውስጥ እልፍኝ አስከልካይ |

| | |
|---|---|
| | የሚሠራውን ሥራ ከቤተ መንግሥት ወይም ከእልፍኝ ውጭ የሚሠራ አጋፋሪ ነው። ማን ከማን በላይ፣ በታች፣በቀኝ፣ በግራ እንደሚቆምና እንደሚቀመጥ የሚወስን ነው። |
| ኢላሎ | ኢላሎ ደንበኛ ወታደር ሳይሆን የአገርን ጸጥታ የሚጠብቅ ዘበኛ ማለት ነው። |
| ኢይወርድ | የማይወርድ |
| እልፍኝ | ነገሥታት ለታላላቅ ሰዎች መቀበያ ይገለገሉበት የነበረ ከዋናው ቤት በስተኋላ የሚገኝ ትንሽ ቤት። |
| እልፍኝ አስከልካይ | በቤተ መንግሥት ውስጥ የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ። የእልፍኝ ሥርዓትና ክብር እንዲጠበቅ የሚያደርግ ሹም ነው። እስከ አምስት ሺህ የሚደርስ ጭፍራ ይኖረዋል። |
| እልፍኝ አሽከር | በእልፍኝ አስከልካይ የሚታዘዝና በቤተ መንግሥት ውስጥ ያልተፈቀደለት ሰው ወደ እልፍኝ እንዳይገባ የሚጠብቅ፣ በማስተናገድ፣ በማጽዳት፣ ወዘተ የሚያገለግል። |
| እምቢልታ | በአፍ የሚነፋ፣ ወፍራምና ቀጭን ድምጽ ማውጣት የሚችል፣ ከቀርከሀ እና ከብረት የሚሠራ እንደ ዋሽንት ያለ የሙዚቃ መሣሪያ። |
| እርታታ | የሙግት ፍጻሜ፣ ድል። |
| እስመ ለዓለም | ከምልጣኑ በፊት በተረኛ መዘምራን የሚቃኝና መላው ካህናት እየተቀባበሉ የሚያዜሙት ዜማ። |
| እጣነ ሞገር | ከቅዳሴ በኋላ የሚነገር ቅኔ። |
| ካባ ላንቃ | ባለወርቅ ጌጥ ካባ፤ ከግራና ከቀኙ ዘርፍ (ክንፍ) ያለበት ካባ። |
| ክስተት አርያም | የሰማይ መከፈት፣ የዜማ ስም። በታላቅ በዓል ቀን እንዲሁም ታላላቅ ሰዎች ሲሞቱ የሚዘመር ነው። |
| ክብር ይእቲ | ክብር ይእቲ በዕለቱ ቅኔ እንዲሰጥ የተፈቀደለት ሰው ካህናቱ ድርገት ከመውረዳቸው በፊት ብቻውን እያዜመ የሚያቀርበው የዜማ ክፍል ነው። |
| ወምበር | ዳኛ። |
| ወረንጦ | እሾህ ሲወጋ ለመንቀያ የሚያገለግል መቆንጠጫ። |
| ወር ተራ | በየወሩ በመተካከት ሥራ የሚሠራበት ወይም ጥበቃ የሚደረግበት ወረፋ። |
| ወፍ አራሽ | ወፍ ፍሬውን አርቶት ወይም በውሐም በንፋስም ኃይል ሄዶ በዱር የበቀለ። |
| ዋዜማ | አምስት ቤት ቅኔ። አጭር ዋዜማ ሁለት ቤት አለው። |
| ውሎ | ሰው ሞቶ ዘመድ፣ ወዳጅ ተሰብስቦ የሥራውን ውለታና ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ አስለቃሽ በኀዘንተኞቹ መሃል ቆሞ እያሟሸ ማስለቀስ። |
| ውዳሴ ማርያም | የሦርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም ድርሰት። ዜማው በቅዱስ ያሬድ የተደረሰ ነው። |
| ዐውደ ምሕረት | በቤተ መቅደስ ፊት ለፊት ስብከት የሚሰጥበት ቦታ። |
| ዑደት | በክብረ በዓላት ቀን ታቦት አጅቦ ቤተ ክርስቲያንን የመዞር ሥነ ሥርዓት። |



| | |
|---|---|
| ዓምደ ወርቅ | በስተቅድስት በኩል በሁለት በሮች መካከል የቆመ ዓምድ (ምሰሶ)። |
| ዕድሞ | በኖራ ወይንም በጭቃ የተገነባ የቤተ ክርስቲያን አጥር። |
| ዘረፋ (ቅኔ | ዘረፋ ማለት ስለ አንድ ድርጊት ወይም ታሪክ ለብዙ ጊዜ ባለማሰብ ወይም ባለማሰላሰል በፍጥነት የግዕዝ ቅኔ መቀኘት ማለት ነው። የሌላውን ንብረት የሚዘርፍ ኃይለኛ ሳያስጠነቅቅ በፍጥነት ዘርፎ እንደሚወስድ ሁሉ ቅኔ ዐዋቂ ለተባለው ሰው ያለማስጠንቀቅ ቅኔ የመቀኛው ሰዓት ሲደርስ «ቅረብና ዘርፈህ ተቀኝ» ይባላል። አንድ ደቀ መዝሙር የቅኔ መምህር ሆነ የሚባለው በዚህ ዓይነት መንገድ በፍጥነት መቀኘት ሲችል ነው። - መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ። |
| ዘብጥ | ጉድጓዳ፣ ረባዳ መሬት። |
| ዘብጥያ | ወህኒ ቤት |
| ዘአምላኪየ | ሦስት ቤት ቅኔ። |
| ዘይእዜ | አምስት ቤት ቅኔ። |
| ዝማሜ | ዝማሜ ከሰውነትና ከመቋሚያ ውዝዋዜ ጋር እየተቀናጀ የሚዜም የአቋቋም የዜማ ስልት። |
| ደጀ ሰላም | በቤተ ክርስቲያን በስተምዕራብ የሚገኝ መዳረሻ፣ መሳለሚያ። |
| ደጅ ጥናት | ጉዳይን ለማስፈጸም ወደሚመለከተው ባለሥልጣን ለልመና መመላለስ። |
| ዳረጎት | ለተሰጠው አገልግሎት የሚሰጥ አበል። |
| ዳባ | ከከብት ቆዳ የሚሠራ የመናንያን ካባ። |
| ዳቦት | ችቦ መብራት። |
| ዳውላ | ትልቅ ስልቻ። |
| ድርብ ቀሚስ | ጨርቁ በእጥፉ ሆኖ የተሰፋ ቀሚስ፣ የሹመት ልብስ። |
| ድርገት መውረጃ | የቤተ መቅደሱ ዋና መውጫ በር። |
| ድርገት ወረደ | በቅዳሴ ሥነ ሥርዓት ማብቂያ ላይ ቀዳሾች ምዕመናኑን ለማቊረብ በአንድነት መሥዋዕቱን ይዘው የሚቀርቡበት ጊዜ። |
| ድባብ | ለታቦት ወይንም ለንጉሥ የሚያዝ የተለየ ትልቅ ጃንጥላ። |
| ድጓ | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዜማ መሠረት የሆነ መጽሐፍ። መሠረቱ የያሬድ ሲሆን ሊቃውንት ሲቀዱት ሥርዋጽ (እንደ ማስረጃ ሆኖ በነገር መካከል የሚገባ) አስገብተውበታል። ድጓ በ4ቱ የዓመት ክፍሎች በሐጋይ (በጋ)፣ በፀደይ (በልግ)፣ በክረምት፣ በመፀው (የመኸር ወራት) ይከፈላል። |
| ገረገራ | የገጠር ቤተ ክርስቲያን አጥር። |
| ገቦተ ሐዋርያ | ወይንም ገቦተዋርያ። ከፊደል ቀጥሎ ንባብ የሚጠናበት ትምህርት። |
| ጉባኤ | ደቀ መዛሙርት ተሰብስበው የሚማሩት የብሉይ፣ የሐዲስ፣ የሊቃውንት፣ የመጽሐፈ መነኮሳት ትርጓሜ። |
| ጉባኤ ቃና | ቅኔ ጀማሪ የቅኔ ትምህርት የሚጀምርበት፤ ሁለት ግጥሞች ሆነው አራት ስንኞች ያሉት። |

| | |
|---|---|
| ጕዞ ፍትሐት | አስከሬኑ ከቤት ወደ ቤተክርስቲያን በሚሄድበት ወቅት በመንገድ ላይ እያረፈ ለሟቹ የሚጸለይ ጸሎት። ይህ ጸሎት በአንድ ቦታ ከሚደረግ ፍታት የላቀና የሚደረገውም ለተከበሩ ሰዎች ነው። |
| ግሥ | የአንዱን ባሕርይ ወይም ግብር ለሌላው በማወራረስ የሚባል የቅኔ ጥቅስ። |
| ግንድ አለቃ | ዋና አለቃ። |
| ንሳ | በደጋማ አካባቢ ችምችም ብሎ የሚበቅል የሣር ዘር። |
| ጦም ቆሎ | በጾም ጊዜ ምዕመናን ለካህናት የሚሰጡት ቆሎ። |
| ጭሰኛ | ከዋናው ባለ ርስት ተዋውሎ የሚቀመጥ። የርስትነት መብት የሌለው ስለሆነ ቤት ሠርቶ በሚያጨሰው ይጠራል። ከሰብሉ አንድ እጅ ለባለርስቱ ሰጥቶ ሁለት እጅ ለራሱ ያስቀራል። ባለ ርስቱ ተነሣ ባለው ጊዜ ይነሣል፣ እስኪሄድ ድረስ ግን በግዴታ ቀን ይሰጠዋል። |
| ጭቃ ግንብ | ግንብ ሲገነባ እንደ ሲሚንቶ አድርገው የሚጠቀሙበት ጭቃን ነበር። ቀይ ወይንም ጥቁር አፈር ከጭድ፣ ጭድ ከሌለም ከስንዴና ከገብስ ገለባ ጋር ተደባልቆ ከአራት እስከ ስምንት ሳምንታት በተወሰነ ቀን እየተገላበጠ፣ እየተረገጠ ይቦካል። ከዚያም ግንቡ በድንጋይና በተቦካው ጭቃ ይገነባል፣ የእንጨት ቤት ከሆነም በግድግዳው ላይ ይለጠፋል፣ ሲደርቅም ይለሰናል። |
| ጽና | ከሸክላ ወይም ከብረት የሚሠራ የዕጣን ማጠኛ። በቅዳሴ ጊዜ ወይም ጸሎት ሲደረስ ቄሱ መንበሩንና ሕዝቡን ያጥናል። |
| ጾመ ድጓ | በዓቢይ ጾምና በሕማማት የሚደረስ የዜማ ጸሎት። |
| ፍታት (ፍትሐት) | ለሞተ ሰው የሚደረግ ጸሎት። |

## ምንጭ


1. ባሕሩ ዘርጋው፣ *ዘርጋው የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1994 ዓ.ም.
2. ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ *ዝክረ ነገር*፣ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም.
3. ተሰማ ሀብተ ሚካኤል፣ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም.
5. ተፈሪ ወርቅ አርምዴ፣ *የአማርኛ ሥነ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1947 ዓ.ም.
6. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም.
7. ይላቅ ኃይለ ማርያም፣ *ሐበሻ የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፣ 1995 ዓ.ም.
8. ደስታ ተክለ ወልድ፣ *አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም.
9. ዳንኤል ክብረት፣ «የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች»፣ አዲስ አበባ፤ ማኅበረ ቅዱሳን (1999) ዓ.ም.
10. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ.ም.
11. አቶ ዘውገ ገድሉ።
12. አቶ ቀለመ ወርቅ ጀምበር።


# አባሪ ረ

## የገዳምና የደብር አስተዳዳሪዎች የክብር ስም

| | |
|---|---|
| ሊቀ ካህናት | ዲያቆናትና ቀሳውስትን ማለት በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉትን ካህናት የሚያዝ። ሹመቱ የተጀመረው በ11ኛው ምዕት መጨረሻ በአጼ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ይነገራል። ዛሬም በየአድባራቱ ይህ ሹመት ይሰጣል። |
| ሊቀ ዲያቆን | የዲያቆናት አለቃ። |
| ሊቀ ጠበብት | በቤተ ክርስቲያን ከአለቃ በታች ያለ ማዕርግ። |
| ሊቀ ጳጳስ | የጳጳሳት አለቃ። |
| መልአከ ሰላም | ለአዲስ አበባ እስጢፋኖስ ደብር አለቃ የሚሰጥ የማዕርግ ስም። |
| መልአከ ብርሃን | ለአዲስ አበባ ሥላሴ ደብር አለቃ የሚሰጥ የማዕርግ ስም። |
| መልአከ ገነት | ለአራዳ ጊዮርጊስ ደብር አለቃ የሚሰጥ የማዕርግ ስም። |
| መልአከ ፀሐይ | ለእንጦጦ ማርያም ደብር አለቃ የሚሰጥ የማዕርግ ስም። |
| መምህር | በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታላላቅ ገዳማት ለሚያስተዳድሩ የሚሰጥ ሹመት። እንዲሁም ለታወቁ መምህራን የክብር ስም ይሆናል። |
| መምሬ | የካህን የክብር ስም። |
| መሪጌታ | የዜማ፣ የቅኔ፣ የአቋቋም መምህር። |
| ርእሰ ደብር | የቤተ ክህነት የክብር ስም በተለይ ዜማ ለሚያስተምር ሰው የሚሰጥ። ሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የገጠር ቤተ ክርስቲያን የሚያስተዳድር መሪጌታ ይባላል። |
| ቀኝ ጌታ | የቤተ ክህነት ሹመት፣ ከደብሩ አስተዳዳሪ ለጥቆ ያለ፣ የደብሩ ሁለተኛ ሰው። በአንዳንድ ጽሑፎች እንደሚነበበው ይህና ሌሎችም ብዙ የቤተ ክህነት የማዕርግ ስሞች የተሰጡት በአጼ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት ሳይሆን አልቀረም። |
| ቄሰ ገበዝ | የቤተ ክርስቲያን ሀብት፣ ንብረት ጠባቂ። |
| ቆሞስ | በኤጲስ ቆጶስና በቄስ ወይም በመነኩሴ መካከል ያለውን ማዕርግ የተቀበለ ነው፣ የቆሞሱም ሥራ አዲስ ታቦት፣ ሜሮን፣ የቤተ ክርስቲያን አልባሳትና ንዋየ ቅድሳትን መባረክ ነው። የረከሰ ታቦትን ቤተ ክርስቲያንና አልባሳትን ሁሉ ይባርካል፤ ምንኩስናም ይሰጣል። |
| ንቡረ እድ | ንቡረ እድ ለአክሱም ጽዮን አለቃና (አስተዳዳሪ) ለአክሱም አውራጃ (አካባቢ) ገዢ የሚሰጥ ሹመት ነው። በአጼ ምንሊክ ዘመን የአዲስ ዓለም ማርያም አለቃም የንቡረ እድነት ሹመት ተሰጥቶታል። |
| አለቃ | የደብር አስተዳዳሪ። |
| አበ ምኔት | የገዳም አስተዳዳሪ። |
| አጋፋሪ | የካህናት አስተናባሪ። |

**እጨጌ** — የደብረ ሊባኖስ አበ ምኔት፣ የመነኲሳቱ ሁሉ አለቃ:: የመጀመሪያው እጨጌ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ነበሩ::

**ዓቃቤ ሰዓት** — በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቈየ ሹመት እንደ ንቡረ እድም የአንዳንድ የቤተ ክህነት ሹመት ነበር:: የዚህ ሹመት ተግባር ንጉሡንና ሕዝቡን ማገናኘት ነበር:: ማንም ሰው ጉዳዩን ለንጉሡ የሚያቀርበው በዓቃቤ ሰዓቱ ሲሆን መልሱንም የሚያገኘው በዚሁ ሰው አማካይነት ነበር::

**ደብተራ** — የቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም ድንኳን ነው:: ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቅኔ ማኅሌት የያሬድን ዜማ የሚዘምር፣ የሚረግድ እንዲሁም ቅኔን የሚቀኝ ደብተራ ይባላል:: ደብተራ ሕዝባዊ ቀመስ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነው:: ለአገልግሎቱ ርስት ወይም ጉልት ይሰጠው ነበር:: ዛሬ እንደሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የወር ደሞዝ አለው::

**ግራ ጌታ** — በግራ የሚቆምና በግራ በኩል የሚደረገውን ስልትና የማኅሌቱን ሥርዓት የሚጠብቅ::

**ጸባቴ** — የደብረ ሊባኖስ ምክትል አስተዳዳሪ::

### ምንጭ


1. ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት*፣ አዲስ አበባ፣ 1971 ዓ.ም.
2. ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ *ዝክረ ነገር*፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም.
3. ዶክቶር ሥርግው ሀብለ ሥላሴ፣ *የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፣ 1971 ዓ.ም.
4. ደስታ ተክለ ወልድ፣ *አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም.


## አባሪ ሰ

## የማዕርግ ስሞች

**ሊቀ መኳስ** — ይህ ሹመት ከንጉሠ ነገሥት ለሁለት ሰዎች፣ ከንጉሥ ለአንድ ሰው ብቻ ይሰጣል:: ሥራው ንጉሥ በነጋሡና ጉባኤ ባደረገ ጊዜ ታላቅ ማዕርግና ግርማ ያለው ልብስ ለብሶ ግራና ቀኝ መቆም ነው::

**ሊጋባ** — ከእልፍኝ አስከልካይ በላይ የሆነ የቤተ መንግሥት ሹም (ማዕርግ) ነው:: ሥራው ከጦር ሚኒስትሩ በታች ሆኖ ሰው ማስገባትና ማስወጣት፤ ማናቸውንም የጦር አለቃ እያዘዘ የመንግሥቱን ሥራ ማሠራት ነው:: ወታደር ተበደልኩ ብሎ አቤቱታ ሲያቀርብም ማንኛውንም የጦር አለቃ ይዳኛል:: በጦርነት ወቅት ደግሞ የመሃል ሰፋሪን ጦር የበላይ ሆኖ ያዘምታል::

**ልጅ** — ይህ ስም የመኳንንት ልጆች የሚጠሩበት ነው፤ ቀድሞ ግን የሚሰጠው ለመሳፍንት ልጆች ብቻ ነበር::

**ራስ** — ከልዑል በታች ከቢትወደድ በላይ የሆነ ታላቅ የማዕርግ ስም::

**ራስ ቢትወደድ** — የራስ አገር የሚገዛ፣ በባለሟልነቱና በአማካሪነቱ በተለይ ንጉሠ ነገሥቱ ራስ ቢትወደድ ብሎ ከራሶች ከፍ ያለ ማዕርግ የሚሰጠው የክብር ስም ነው::

**ቀኛዝማች*** — በንጉሡ ቀኝ ጭፍራውን የሚያዘምት የጦር አለቃ::

**ቢትወደድ** — እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ያለ ባለሙሉ ሥልጣን ጉዳይ ፈጻሚና ባለሟል ነው፣ ማዕርጉ ከደጃዝማች በላይ ሆኖ ልብሱና ክብሩ ከራስ ወርቅ በቀር እንደ ራሶች ነው::

**ባላምባራስ*** — የሹመት ስም፣ ከቀኛዝማችና ከግራዝማች በታች::

**ሞሻ** — በቱርክ ቋንቋ ባሽነት የጦር አለቃ፣ የሺ አንበልነት፣ የመቶ አለቃ፣ የሃምሳ አለቃ ማለት ነው::

**ብላታ** — በቤተ መንግሥት ውስጥ ለሚያገለግልና ለንጉሡ ዋና ጉዳይ ፈጻሚ ለሆነ ሰው ይሰጥ የነበረ፣ ከብላቴን ጌታ ዝቅ የሚል የማዕርግ ስም::

**ብላቴን ጌታ** — ለቤተ መንግሥት አገልጋዮች ወገን የሚሰጥ ስም ወይም የንጉሥ ዋና ጉዳይ ፈጻሚ::

**ነጋድራስ** — የነጋዴዎች ሹም፣ የንግድ ግብርን ሰብሳቢ፣ የነጋዴ አለቃ::

**አቤቶ** — አልጋ ወራሽ ለሆኑ ወይንም መዕርግ ሳይሰጣቸው የንጉሥ አገር ለሚገዙ የነገሥታት ልጆች የሚሰጥ ስም ነው::

**አዛዥ** — ገዥ፣ አስተዳዳሪ:: የእንኮበር ገዥ፣ የወህኒ ቤት አዛዥ ይባላል::

**አጋፋሪ** — ለሊጋባው ምክትል ሆኖ የመንግሥትን ገንዘብና ዕቃ የሚያስቀምጥና የሚይዝ ነው::

**አፈ ንጉሥ** — በንጉሠ ነገሥቱ ስም በፍርድ ሥራ ላይ ተቀምጦ ከንጉሦች ጀምሮ የፍርድ ይግባኝ የሚያይ የፍርድ ሚኒስትር ነው::

የሻላ — የቀድሞ ማዕርግ ስም፣ የሻለቃ ክፊል፤ ባለ ግምጃ ሱሪ።

ደጃዝማች* — በቀድሞ ጊዜ የጦር የበላይ ሹም የማዕርግ ስም፤ ከራስና ከቢትወደድ በታች ያለ።

ግራዝማች* — በንጉሡ ግራ ጭፍራውን የሚያዘምት የጦር አለቃ።

ጸሐፌ ትእዛዝ — ጸሐፌ ትእዛዝ ማለት ቀጥታ ትርጓሜው «ትእዛዝን የሚጽፍ» ማለት ሲሆን ደንበኛ ሥራው የንጉሡን ማኅተም መያዝና መጠበቅ፣ ማተም፤ ትእዛዙን ማስተላለፍ ነው።

ፊታውራሪ* — የጦር አበጋዝ፣ ማዕርጉ ከራስ እኩል ነው።

* እነኚህ የማዕርግ ስሞች ለጦር አለቆች የሚሰጡ ነበሩ። በኋላ ዘመን ግን የጦር አለቆች ላልሆኑ ሰዎችም ይሰጡ ነበር።

## ምንጭ


1. ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ *ዝክረ ነገር*፣ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም.
2. ከሣቴ ብርሃን ተሰማ፣ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1951 ዓ.ም.
3. ደስታ ተክለ ወልድ፣ *አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም.
4. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም.
5. ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ስለ ጸሐፌ ትእዛዝ ሹመት አመጣጥ፣ ያልታተመ ጽሑፍ።


# የስሞች ፊደላዊ ማውጫ

### ሀ


ሀሪንግቶን 254
ሀብተ ሚካኤል ይናዱ (ደጃዝማች) 110
ሀብተ ማርያም ሽገን (አቶ) 31
ሀብተ ማርያም ዘጅሑር 71 72
ሀብተ ማርያም ዘግሬት (አባ) 50
ሀብተ ማርያም ገብረ መድኅን 49 101 103 105 114 148
ሀብተ ማርያም (ቀኜ በጉንጬ) 92
ሀብተ ወልድ ዘእንጀራ 125
ሀብተ ገብርኤል (መምህር) 106
ሀብተ ጊዮርጊስ ዘሥዕል ቤት 156
ሀብተ ጊዮርጊስ ዘጅሑር 71 72
ሀብተ ጊዮርጊስ (ፊታውራሪ) 61 87 88 96 98 126 127
ሀብቱ (መምህር) 10 137
ሁለት ልደት 39 98 111 112
ሁኚ እንዳሻሽ (ወይዘሮ) 39 40 235 236
ሁዳዴ 56 74 92 94 119 133 151
ሁዳዴ ጾም 56 69 96
ሃርዲንግ (ፕሬዜዳንት) 144
ሃዋርድ ዩኒቨርሲቲ 144
ሃይማኖተ አበው 133 134 143 244 248 257
ሄሮድያዳ 155
ሄይስ (ጆ) 4
ህንድ 122 144 253 254 256
ህንድ ውቅያኖስ 207
ሆለታ 94
ሆለታ ቤተ መንግሥት 94
ሆለታ ጦር ትምህርት ቤት 40
ሆላንድ 215
ሆሳዕና በዓል 56 60 61 114


### ለ


ለማ ኃይሉ (አለቃ) 39 92 121 140 142
ለማ ወልደ ታሪክ (አለቃ) 247
ለማ ፈለቀ (አቶ) 51 237
ለየሀ (ደጃዝማች) 43 63
ለጥ ይበሉ ገብሬ (ግራዝማች) 187
ሉሉ መርሻ (አቶ) 4
ሉል ሰገድ ተ/ ሃይማኖት (አጼ) 113
ሊቃውንት 41 129
ሊቅ (መጽሐፍ) 247
ሊጦን 225
ላሊበላ 39
ላሐ (ወይዘሮ) 39 236
ላምቤ (ዶክቶር) 182
ላምዋሻ 15 38 39 40 68 69 73 125 151
ላምዋሻ አቦ 23 38 41 151
ላስታ 17
ላቀች ኪዳነ ማርያም 253
ላቀው (አቶ) 26
ላቡርዳሪ (ፖል) 171
ላይብረሪ ኦፍ ኮንግሬስ 4
ሊጋር 120 144 187
ሌቃ ወረዳ 199
ልሳነ ወርቅ (አቶ) 104 106
ልሳነ ወርቅ ንጉሤ 3 235
ልሳነ ዕፍረት 42
ልቤ ይርጋ (አቶ) 31
ልብሰ ወርቅ ሽፈራው 228
ልብነ ድንግል (አጼ) 39 136
ልዑል አልጋ ወራሽ (ራስ ተፈሪ) 10 81 122 127 129-132 134 137-142 144 145 151 157 158 162 164 165 167-169 171 172 174 175 177 178 185-188 190 247 248
ልዑል አልጋ ወራሽ ማተሚያ ቤት 12 162
ልዑል ራስ መኰንን ትምህርት ቤት 182 218
ሎሬንስ (ሜጀር) 206 207
ሎንዶን 182 253 256
ሎንግ የጅጅጋ ቆንስል (ካፕቴን) 198 199 214


### ሐ


ሐሲብ (መምህር) 10 137
ሐማሴን 44 137 146
ሐረማያ 120 125

ሐረር 117 120-125 131 139 140 142 151 157 196 197 201-204 209 215 219-221 229 247
ሐረርጌ 35 56 148 151 209 247
ሐረገ ወይን (ወይዘሮ) 238
ሐረግ ግርማ (ወይዘሮ) 3
ሐረራድ 207
ሐርጌሣ 206 222
ሐሳበ ኮከብ 153
ሐሳበ ጋብቻ 153
ሐበር አወል 203
ሐና ሰሊብ (መምህር) 145
ሐናዬ ወልደ ማርያም 41
ሐዋርያ 143
ሐዋርያ መልእክት 118
ሐዋርያ ትርጓሜ 148
ሐዋርያነ ክርስቶስ (መምህር) 10 137
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ 250
ሐዋዝ ዘሐረር (አለቃ) 122
ሐዋዝ ዘአዲስ ዓለም (ደብተራ) 82
ሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ 1 7 38 47 60 109 125 147 168 204
ሐዲሳት (መጽሐፈ) 109-111 119 129 133 138 139 144 244 245 259
ሐዲስ 39 41 110 115 124-127 131 133 136 137 143 145 261
ሐዲስ መምህር 110
ሐዲስ ትምህርት ቤት 109 110
ሐዲስ ትርጉም 94 111
ሐዲስ ኪዳን 145 155 225
ሐዲስጌ 18
ሐሊ (ኮሜት) 77
ሕሰተ ወርቅ አሸቴ 98 99
ሕማማት 262
ሕንጺሃ 243
ሕዝቅኤል 124
ሕዝብ ጤና ሚኒስቴር 224
ሕገ መንግሥት 218 219
ሕገ መንግሥት በዓል 211 218 219
ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት 117 176 224


## መ


መሃል ሰፋሪ 47 265
መሃል ሰፋሪ አድማ 47
መላክ ሰገድ (አጼ) 17
መልእኩ በያን (ልጅ) 144 181
መልእኩ ወንድም (አቶ) 127
መልእክተ አረጋዊ 136
መልከ ጼዴቅ (አቡነ) 2 6 226
መልዛ 17
መሐለቅ 35 125 258
መሐመድ ዓሊ ኩባንያ 201
መረግድ 84 242 245
መራቤቴ 17 18 39 41 50 51 161
መሬት መንቀጥቀጥ 56 57
መርሐ ዕውር ትምህርት 126 257
መርሐ ጽድቅ ፈለቀ (ደብተራ) 93
መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ (አቶ፣ ብላታ) 1 5-12 15 38 40 41 47 50 60 85 90 103 109 112 114 125 131 132 138 142 143 145-147 150 152 153 168 171 173 174 176 180 182 183 199 202 206 209 212 222 223-231 236-238 244 245 256
መርስዔ ኀዘን ወርቄ 142
መርሻ ወልዴ (አቶ) 149
መርሻ ዘቤተልሔም 42 117 148
መርሻ ዘጎንት 248
መርሻ ድጓ ፈረሱ (አለቃ) 106 107 114
መርዓዊ (አለቃ) 118
መርድ (ኢጋፋሪ) 65
መርጦ 131
መስቀለ ክርስቶስ 26
መስቀሰሰስ 16 25 26 27 28 31 32 33 69
መስቀሌ (ወይዘሮ) 39 236 237
መስተብቍዕ 225
መስተጋብእ 56 257
መስፍን ሸንቁጥ (አቶ) 3
መስፍን ቀለመ ወርቅ (ልጅ፣ ግራዝማች) 181 187 196 200 221
መሸሻ ተወንድ በላይ (አዛዥ) 93
መሸሻ ገብረ ማርያም (ደብተራ) 77
መሻገሪያ ሲሳይ 32 51 69 149 157 238
መቀሌ 23
መቃርስ 136
መቃኞ 40 88 92 93 103 105 247 257
መቂት 42
መቅደላ 253
መቅደላ ጦርነት 254
መቅድመ ወንጌል 119 124 125 142
መብራቱ (ግራዝማች) 103
መተማ 41
መታፈሪያ ፍሬው (አቶ) 125
መትረየስ በር (ጀድሌ) 219 220
መነን (እቴጌ) 226
መና ወልደ ጊዮርጊስ 238
መናገሻ 89 90
መናገሻ ማርቆስ 79





መናገሻ ተራራ 89
መንበረ ያየህ ይራድ 201
መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ 90 117 123
መንክር ወሰፁብ 156
መንዝ 17 18 46 47 74 140 152 161
መንገሻ ኃይሌ (አቶ) 199 210 216
መንገሻ ከፈላ 171
መንገሻ ውቤ (ሊቀ መቋስ) 191
መንግሥቱ (አቶ) 142
መንግሥቱ ንዋይ (ጀኔራል) 123
መንግሥቱ ወልደ ማርያም (አቶ) 100
መንፈሳዊ ጉባኤ ምክር ቤት 40
መንፌቆ ወልደ ሃይማኖት 10 137
መከኒሳ 203
መኩሪያ (መምሬ ዘሐረር) 221
መኩሪያ (ሻቃ) 104
መኩሪያ ዘጅሩ (መምሬ) 103 107 149 150
መካለያ ወሰን (ወይዘሮ) 50 51 238
መካነ ሥላሴ (አዲስ አበባ) 40 90 94
መክሊት መርስዔ ኀዘን 231 235
መክብብ አጥናው (መጋቤ አእላፍ) 4
መኰንን ተወንድ በላይ 33
መኰንን ኃይለ ሥላሴ (ልዑል) 212
መኰንን ወልደ ሚካኤል (ልዑል ራስ) 56 93 195 198 199 203 221
መወድስ 39 57 69 70 71 75 83 243 257
መዋሥዕት 98 242 245
መዓዛ 235
መዓዛ ወልደ ሕይወት (አቶ) 198 201 212 216 221
መድኃኔ ዓለም (ቀጨኔ) 78 87 88 93 116
መድኃኔ ዓለም (እንኮበር) 199
መድኃኔ ዓለም (ደብረ ሰላም) 144
መድኃኔ ዓለም (ድሬ) 174 180
መድኃኔ ዓለም (ጅሩ) 70 72 73 149 151
መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ (ልዕልት) 3 227 228
መዘምር ዘመርሐቤቴ 41 237
መዝለቂያ (ወይዘሮ) 122
መዝለቂያ ዘጅሩ (አለቃ) 73
